፩፻፹ ብር ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ፍርድና ፡ በአሁኑ ፡ ፍርድ ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላው ፡ አቶ ፡ ትርፌ ፡ የሚከፍሉት ፡ ፱፻ ፡ ብር ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ሕፃኗ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላት ፡ ድረስ ፡ አቶ ፡ ትርፌ ፡ በየወሩ ፡ ፲፭ ፡ ብር ፡ እንዲሰጡ፡ ታዘዋል ።

የሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ክርክር ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችንና ፡ ሕጉን ፡ ከመረመ ርን ፡ በኋላ ፡ እንደሚከተለው ፡ ፈርደናል ።

<u>ፍርድ</u> ፡

ሐምሌ ፡ ፳፭/፸፱ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፲/፸፱ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ውን ፡ ፍርድ ፡ የሚከተለውን ፡ ማሻሻያ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ አጽድቀነዋል ።

ሀ/ ከሚያዝያ ፡ ፲፫/፸፱ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ጋብቻ ፡ ፈርሷል ፡

ለ/ የተባለው ፡ ዕዳና ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ስምምነት ፡ ሁኔ ታ ፡ በሽማግሌዎች ፡ እንዲወሰን ፤

ሐ/ ተንቀሳቃሽም ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረታቸው ፡ መጠን ፡ በሽማግ ሌዎች ፡ እንዲወሰን ፤

መ/ ሕጻኗ፡አምስት፡ዓመት ፡ እስኪሞላት ፡ ድረስ ፡ በየወሩ ፡ ፲፭ ብር ፡ ለወይዘሮ፡ አብረኸት ፡ እንዲከፈላቸው ።

ሠ/ አቶ ፡ ትርፌ ፡ ፱፻ ፡ ብር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመክፈል ፡ አለመቻላቸውን ፡ ተገንዝበናል ። ስለዚህ ፡ ከኅዳር ፡ ፴/፷ ፡ ጀምሮ ፡ በየወሩ ፡ ፴፭ ፡ ብር ፡ እየ ከፈሉ ፡ እንዲጨርሱ ፡ ወስነናል ።

ረ/ እያንዳንዱ ፡ ተከራካሪ ፡ ያወጣውን ፡ ወጭ ፡ ይቻል ።

ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ባሉበት ፡ ዛሬ ፡ ጥቅምት ፡ ፴/፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተነበበ ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Asmara

Justices:

Dr. Yohannes Berhane
Fitawrari Tsegay Tefferi
Grazmach Yohannes Aman

TIRFE MEASHO v. ABREHET GEBREMESKEL

Civil Appeal No. 149/59

Family law—Divorce—Divorce for non-serious cause—Common debts—Maintenauce allowance for children—Civil Code Arts. 659, 660, 673(2), 667, 679-82, 694.

An appeal from the decision of the High Court granting divorce between the parties, custody of the child and maintenance allowance for the child to the mother, and settling common debts and property.

Held: Decision affirmed with modifications.

1. Although religious authorities have not given any decision on divorce, the marriage may be dissolved in accordance with the law if the family arbitrators cannot reconcile the spouses.

2. The family arbitrators shall decide whether the debts incurred by the husband were personal or common debts incurred in the interest of both spouses, and the manner of partition of common property.

3. Custody of the child is entrusted to her mother until the age of 5, and the father shall pay a maintenance allowance.

JUDGMENT

The two parties are spouses; they were formally married. They could not continue living together in peace. A dispute arose which was first dealt with by family arbitrators and then by a committee of religious authorities. Finally the case was taken to the Awradja Court, and, on appeal, to the High Court. Besides the declaration of divorce, the following decisions were made on the case.

(a) The female child born to the spouses shall be entrusted to her mother until she becomes five years of age; she shall be given E $ 15 per month as a maintenance allowance.

(b) Ato Tirfe shall pay E $ 720 to Woz. Abrehet for the expenses she incurred in the past to support the child, and for other matters.

(c) Each party shall bear the expenses it incurred during the litigation.

Ato Tirfe lodged an appeal from this decision. The grounds of appeal are, briefly, the following:

(a) That the marriage should not be dissolved, according to Articles 647, 664 and 665 of the Civil Code.

(b) That the order requiring him to pay E $ 720 was contrary to law.

(c) That Articles 669 - 670, 677, 679, 736 require that evidence be produced.

(d) That he was unlawfully denied the right to produce competent witnesses and documentary evidence.

The respondent briefly replies as follows:

(a) The provisions cited are irrelevant to the case.

(b) During the meeting with religious authorities the appellant had stated that the debts do not concern his wife, and that they were incurred on behalf of his mother.

(c) The facts established by the family arbitrators were found to be true by the courts.

(d) There is enough cause for divorce.

In her complaint filed to the Awradja Court, the respondent claimed only E $ 519.25, which is the value of the furniture of the house; it was decided (by the Awradja Court) that she receive only half of her claim. On appeal the High Court decided the matter should first be referred to family arbitrators in accordance with the proper procedure. The family arbitrators passed a decision on the case. The provisions cited by the appellant do not invalidate the decision passed by the family arbitrators. Certainly, in their decision of April 21, 1967 the family arbitrators did not deal with the interests of the child as a separate issue. But there is no doubt that both in their decision of February 16, 1967 and that of April 21 the family arbitrators treated that issue in a general manner.

Hence, this court has to pass judgment regarding the following four points:

(a) The divorce.

(b) The debts, and the agreements entered into by the parties.

(c) Property and its ownership.

(d) The conditions of the child and its maintenance.

(a) On the divorce

As stated by the committee of religious authorities and as the appellant pointed out by citing Articles 664-665 of the Civil Code, marriage, a serious bond as it is, cannot be dissolved unless there is a serious cause. The main purpose of marriage is to keep a husband and wife together with honest love. Hence, when love and smooth relationship disappear and hatred and avoidance prevail among the spouses, divorce becomes essential and justifiable. Other than the serious causes mentioned in Articles 667-670, under Articles 673(2), 677, 694, 606 of Civil Code the family arbitrators and the courts have the power to declare divorce.

The family arbitrators found out what kind of relationship existed among the spouses. After examining the case, the family arbitrators indicated that in their opinion divorce was the only solution. This court also made further findings regarding the relationship of the parties. We do not think that the parties could live together as a good and loving couple. First, they agreed, with the help of arbitrators, to continue to live peacefully; but they failed. Again, the arbitrators tried, but in vain, to have the parties agree to live together in peace; the hatred was not limited to the parties — it extended to their respective families; this fact is admitted by both parties. In view of the above facts, we think that, despite the fact that divorce may not be granted by the religious authorities, there is a ground to dissolve such a marriage in law and reason.

(b) On the debts and the agreement between the parties

When a dispute arose between the spouses, a compromise was reached with the help of arbitrators. According to that compromise, Ato Tirfe was to pay his debts, and both the spouses were to continue living in peaceful wedlock. However, after the compromise, Ato Tirfe erred and Woz. Abrehet was offended. There was no peaceful marital relationship. Rather a bad atmosphere was created. Woz. Abrehet alleges that the debts concern only Ato Tirfe and that Ato Tirfe, in order to satisfy his debt, sold their common property. Although Ato Tirfe claims that he bought the property before marriage, he does not deny that he unlawfully sold cattle and was consequently brought to court.

There is no sufficient evidence to prove that the property in dispute i.e., one cupboard and another pedestal or bedside cupboard, four chairs, and one big table, was bought before the marriage. Furthermore, we do not have sufficient evidence to decide whether or not, according to the agreement entered into during the wedding ceremony, all the property that existed before the marriage was to be included in the common property.

Debts incurred in the interest of the spouses are deemed to be joint debts. (Articles 658 (c), 659 - 660 of the Civil Code). We could not get clear explanations with respect to the amount of the debt, to whom it was owed, when it was entered into and for what purpose, nor as to how the borrowed money was spent. In addition we could not get clear information with respect to the contents of the first and second contracts. Before the facts are clarified and decided upon by family arbitrators concerning the above two points, the courts cannot pass any judgment.

(c) On property and ownership

Now we would like to deal with the question of the ownership of the property under dispute.

Article 647 of the Civil Code explains that property acquired before marriage is personal property and not common property. But, any property acquired after marriage is presumed to be common property, until it is proved that one of the spouses is the sole owner.

As we stated earlier, since a marriage has to be supported by both the spouses, any debt incurred in the interest of the household is deemed to be a joint debt; each spouse has the obligation to satisfy the debt. Furthermore, the spouses can agree and include personal property in the common property; (Article 652(3) of the Civil Code.) They can also modify the terms of the contract regarding their relationship (Articles 629, 632, 658 of the Civil Code). All this can be done only when there is a good relationship between them. When the spouses become hostile to each other, divorce is granted. If it is ascertained that one of the spouses is at fault, the family arbitrators can award all the common property to the other; they can even award one spouse the personal property of the other spouse who was at fault (Article 692 of the Civil Code).

Furthermore, the family arbitrators can order that the spouses or one spouse restitute such presents and matrimonial benefits received to those persons who gave them (Article 691 Civil Code).

It is true that the family arbitrators, not having clear information, decided that he spouses make a fair decision or settlement regarding the property they received

as matrimonial gifts, the property they received for the purpose of setting up their economic autonomy, and their general common property. The Awradja Court, although it was not clear as to who was the owner of the furniture on which Woz. Abrehet sued, decided that since they are spouses, the two parties share, with the help of elders, the debt of E $ 519.25. This judgment was affirmed by the High Court. This decision we think was fair.

The courts cannot pass a judgment until the arbitrators get the necessary clarification on the previous relationship of the spouses, the property the spouses acquired after marriage, if any, and its value.

(d) On the situation of the child and its maintenance

It is clear that the female child born in October, 1966 was up to now living with and maintained by her mother, Woz. Abrehet Gebremeskel. Within this expanse of time, Ato Tirfe never offered any amount of money to aid or maintain his daughter. In view of this situation the family arbitrators decided that Ato Tirfe pay E $ 30 for every past month, E $ 720 all in all (from the time of birth up to the time of decision by arbitrators). But the family arbitrators did not make any decision regarding the future of the child. On appeal, the High Court decided that the child be entrusted to her mother until she becomes 5 years of age, up to which time Ato Tirfe shall pay E $ 15 every month as a maintenance allowance. We affirm this decision, not only because it is just, but also because it is supported by the law, (Articles 679, 682 of Civil Code). Furthermore, the mother and the child have not been receiving any maintenance allowance from Ato Tirfe from the time the family arbitrators gave their decision up to now. Although we did not receive any report regarding the expenses incurred by the mother and the child, we hereby decide, following the approximation made by the family arbitrators, that Ato Tirfe pay for May to October 1967 the amount determined by the High Court plus E $ 15 which is E $ 30 per month altogether. Totally for the said expanse of time Ato Tirfe shall pay E $ 180, but we affirm the High Court's decision that Ato Tirfe shall pay E $ 15 per month until the child becomes 5 years of age. So the payments which Ato Tirfe has to make are: E $ 720, that which was determined by the family arbitrators; E $ 180 for the time between the decision of the arbitrators up to now. Totally he shall pay E $ 900. In addition to all these, he has to pay a maintenance allowance of E $ 15 every month until the child becomes 5 years of age.

Hence, considering the arguments of the parties, the various documents and the laws, we decide as follows:

The High Court judgment given on July 1 is affirmed but amended as follows:

(a) The two parties are divorced as from April 21, 1967.

(b) The question of the debts and the agreements entered between the spouses shall be decided upon by arbitrators.

(c) The movables and immovables they owned shall be ascertained and decided upon by family arbitrators.

(d) Ato Tirfe shall pay E $ 720 plus E $ 180 (E $ 900) to Woz. Abrehet. In addition, he shall pay E $ 15 every month until the child is 5 years old.

(e) We understand that this amount of money ($900) is too much for Ato Tirfe to pay at once. We therefore decide that Ato Tirfe pay, starting from the end of the Month of November 1967, E $ 35 (from the $ 900) and the E $ 15 (monthly allowance) - all in all E $ 50 every month.

(f) Each party shall be responsible for the court fees and other expenses incurred in the litigation.

November 9, 1967

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ፤ ፫ኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤
ም/አፈ ፡ ንጉሥ ፡ አበጀ ፡ ደባልቅ ፤
አቶ ፡ ውቤ ፡ ወልደየስ ፤
አቶ ፡ ዳምጠው ፡ ፈንታ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ከተማ ፡ ኃይሌ ፡ ቀረበ ፡

መልስ ፡ ሰጭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴/፶፱

ስለ ፡ ውሎች ፦ ዋስትና ፡ የውል ፡ ፎርም ፡ የዋስትናው ፡ መጠን ፡ መወሰን ፦ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፩ሺ፯፻፲፱ ፤ ፩ሺ፯፻፳ ፤ ፩ሺ፯፻፳፫ ፤ ፩ሺ፰፻፺፮ ፤ ፩ሺ፱፻፳ ፤ ፩ሺ፱፻፳፪ ፤ ፩ሺ፱፻፳፭ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፤ የሕግ ፡ ትርጉም ፡ አስገዳጅ ፡ ደንቦች ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ (፩) ፤ ፩ሺ፯፻፲፫ ።

ተያዥ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ተያዥ ፡ የሆነበት ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ በተያዥነቱ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ሳይጠቀስ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተያዡ ፡ በገባበት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ እንዲከፍል ፡ ስለፈረደ ፡ ፍርዱን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፦ ፍርዱ ፡ ተገልብጧል ።

፩/ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ በመሆኑ ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩ ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ከሌሉ ፡ የተሠረዙ ፡ ናቸው ።

፪/ ተያዥነት ፡ የሚባለው ፡ የዋስትና ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የሆነ ፡ ልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ በዋስትና ፡ ሥር፡ ተጠቃሏል ።

፫/ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በኋላ ፡ የተደረጉ ፡ ውሎችም ፡ ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆኑበት የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ ካልተጠቀሰ ፡ ውድቅ ፡ ናቸው ። ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪(፫) ።

፬/ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆኑበት ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ መጠቀስ ፡ አለበት፡ የሚለው ፡ ድንጋጌ ፡ የማይለወጥና ፡ አዛዥ ፡ ስለሆነ ፡ ሕጉ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በተደረጉ ፡ ውሎች ፡ በሚነሳ ፡ ክር ክር ፡ ሕጉ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ተመሳሳይ ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ መጥቀስ ፡ አያስፈልገውም፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ አይጠቅምም ።

፭/ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የማይለወጡና ፡ አዛዥ ፡ የሆኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ መከተል ፡ አለባቸው ። ሕጉ ፡ የያዘው ፡ ፎርም ፡ ተሟልቶ ፡ ካልተገኘ ፡ የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ለውሉ ፡ ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይሆንም ።

፮/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ (፫) እና ፡ ፩ሺ፱፻፳፭ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ተቃራኒነት ፡ የለም ። ለወደፊት ፡ ስለሚሆኑ ፡ ግዴታዎች ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ፤ እነዚህም ፡ የዋስትና ፡ ውሎች ፡ እንደ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የዋስትናን ፡ ውል ፡ አጻጻፍ ፡ ደንብ ፡ መከተል ፡ አለባቸው ።

ፍርድ ።

በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ የቀረበው ፡ ፩ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ አቶ ፡ ገብረየስ፡ ወልድ ፡ በመብራት ፡ ኃይል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሲሠራ ፡ የገቢ ፡ ካርኔ ፡ ቀሪና ፡ በራሪ፡

* (የአዘጋጁ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፯፻፳፭ ፡ እና ፡ ፩ሺ፯፻፳፯(፪) ፡ ተጨማሪ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ ውል አጻጻፍ ፡ ደንብ ፡ ይደነግጋሉ ። እንቀጾቹ ፡ እንደሚሉት ፡ የዋስትና ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መስፈርና ፡ በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ። በአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ እንደምንረዳው ፡ ይህ ዋስትና ፡ በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ የተረጋገጠ ፡ ይመስላል ።)

በማበላለጥና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ፺ሺ፯፻፵፫ ፡ ብር ፡ ስላጐደለ ፡ በተያዡ ፡ በ፪ኛው፡ ተከሳሽ ፡ አማካይነት ፡ እንዲከፍል ፡ በማለት ፡ ነው ፡፡

፩ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ የለም ፡፡ ይኸውም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ጥፋቱንና ፡ በገንዘቡም ፡ መጠቀሙን ፡ አምኖ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ የተፈረደበት ፡ መሆኑን ፡ የወንጀሉ ፡ መዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ በማስረጃነት ፡ ተያይዞ ፡ ቀርቧል ፡፡

በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ እንዲከራከር ፡ ተጠርቶ ፡ ለመቅረብና ፡ ለመከራከር ፡ አለመፍቀዱ ፡ በመዝገቡ ፡ ተጠቅሷል ፡፡ ፪ኛው ፡ ተከሳሽም ፡ ተያዥነቱን ፡ ሳይክድ ፡ ተያዥ ፡ የሆንኩት ፡ ለጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡፡ ገንዘብ ፡ ያዥ ፡ ሲያደርጉት ፡ ተያዥ ፡ አልሆንኩም ፡፡ ዋስትናውም ፡ በታወቀ ፡ ሂሳብ ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፤ ዋጋ ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ የጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ለታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈቅደውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ተያዥነት ፡ የሚናገር ፡ አይደለምና ፡ የ፩ኛው፡ ተከሳሽ ፡ ዕዳ ፡ በተያዡ ፡ በ፪ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ አማካይነት ፡ ሊከፈል ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ፈርዷል ፡፡

ይህ ፡ ይግባኝ ፡ የቀረበልን ፡ ይኸንን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ ሲሆን ፤ ይግባኝ ፡ ያለውም ፡ ተያዡ ፡ ፪ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡ ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ይግባኝ ፡ አላለም ፡፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ስለ ፡ ይግባኙ ፡ ያቀረበውም ፡ ክርክር ፡ በመሠረቱ ፡ ተያዥነቴ፡ ለገንዘብ ፡ ተቀባይነትና ፡ የግምጃ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ሳይሆን ፡ ለጸሐፊነት ፡ ነው ፡፡ ለጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ ተያዥ ፡ የሆንኩበት ፡ የተያዥነት ፡ ጽሑፍም ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ አኳኋን፡ ነው ፡፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፳፪ ፡ (፫) የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ በዋስትናው ፡ ላይ ፡ ካልተገለጸ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ አኳኋን ፡ የፈረምኩት ፡ ግዴታ ፡ ባለዕዳ ፡ ሊያደርገኝ ፡ ስለማይገባ ፡ ፍርዱ ፡ ይሻርልኝ ፡ በማለት ፡ ነው ፡፡

የመልስ ፡ ሰጭ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ስለ ፡ መልሱ ፡ የጻፈውም ፡ ማመልከቻ ፡— ይግባኝ፡ ባዩ ፡ ፩ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ አቶ ፡ ገብረየስ ፡ ወልድ ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት፡ ተቀጥሮ ፡ በሚሠራበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በሚያጠፋውና ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ጥፋት ቢገኝበት ፡ ለጥፋቱ ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ተጠያቂ ፡ እሆናለሁ ፡ ብሎ ፡ ፈርሟል ፡፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፴፱ ፡ ፩ሺ፯፻፹ ፡ ፩ሺ፯፻፲፫ ፡ ፩ሺ፰፻፹፮ ፡ ፩ሺ፱፻፳ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደው ፡ በሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርዱ ፡ ይጽናልኝ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይነበብበታል ፡፡

ይህ ፡ ነገር ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ አለበት ፡፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ሕግ ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ ብቻ ፡ ዋስትና፡ እንዳለ ፡ አይቆጠርም ፤ ዋስትና ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ እንዲሁም ፡ ከተደረገው፡ ውል ፡ ወሰን ፡ ለማለፍ ፡ አይችልም ፤ ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆነበት ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ካልተገለጸ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፤ ማለትን ፡ ያስረዳል ፡፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ተያዥ ፡ የሆነው ፡ በሰኔ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከወጣ ፡ ከ፩ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ የተያዥነቱ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ገልጿል ፡፡ የመልስ ፡ ሰጭውም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በበኩሉ ፡ የጠቀሳቸውንም ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ መርምረናል ፡፡ ፩ኛ ፡— በቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፴፱ ፡ እና ፡ ፩ሺ፯፻፹ ፡ የተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ውልን ፡ ፈቅዶ ፡ ስለመዋዋልና ፡ ስለ ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ ይናገራል ፡፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አድርጐ ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ፡ ተያዥነት ፡ በስጠሁት ፡ መተማመኛ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የገንዘቡ ፡ መጠን ፡ በተያዥነቱ ፡ ጽሑፍ ፡

ላይ ፡ ካልተገለጸ ፡ ሕጉ ፡ ያፈርሰዋልና ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ አልሆንም ፡ በማለት ፡ ነው ። በክርክሩ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ያልተመሠረቱ ፡ ወይም ፡ ያልተ ቋቋሙ ፡ ውሎችን ፡ ፈቅዶ ፡ መዋዋሉ ፡ ብቻ ፡ ውሉን ፡ የሚያጸናው ፡ ስላልሆነ ፡ እነዚህ፡ በመልስ ፡ ሰጪው ፡ በኩል ፡ የተጠቀሱት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ለዚህ ፡ ክርክር ፡ ጠቃሚ ነት ፡ አይኖራቸውም ። ይኸውም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊዋዋል ፡ የሚገባው ፡ በውል ፡ የማ ይለወጡ ፡ አዛዥ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ቃሎችን ፡ ጠብቆ ፡ መሆን ፡ ስላለበት ፡ ነው ።

፪ኛው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፫፻፺፯ ፡ «ተዋዋዮቹ ፡ በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ከአቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኃይል ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢቀርም ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ለሚያመጣው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ አላፊነታቸውን ፡ አስፋፍተው ፡ ለመዋዋል ፡ ይች ላሉ” ፡ ይላል ።

ውሉ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ ከአቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ የሚል፡ ባለመኖሩ ፡ ይህም ፡ ቁጥር ፡ ለዚህ ፡ ክርክር ፡ ተገቢነት ፡ የለውም ።

፫ኛው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፲፫ ፡ ውሎች ፡ አስገዳጅነታቸው ፡ በውሉ ፡ በተነገረው ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ልማድ ፡ ፍትህ ፡ ቅን ፡ ልቦና ፡ የውለታው ፡ ዓይነት ፡ በሚያስ ከትሏቸው ፡ ነገሮች ፡ ጭምር ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ።

፬ኛው፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፡“ለግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ሰው፡ባለዕዳው፡ ግዴታውን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ይፈጽማል” ፡ ይላል። የክርክሩም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በጠቀሰው ፡ ቁጥር፡ ፩ሺ፱፻፳ ፡ እና ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለዚህም፡ ሕጉን ፡ መመርመርና ፡ በነገሩ ፡ መድረስ ፡ ያለብን ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ ስለ ፡ ዋስ ትና ፡ በተጻፈው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፡ ውስጥ ፡ መገኘት ፡ ያለመገኘ ቱን ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ወደፊት ፡ ስለሚሆን ፡ ጉዳይ ወይም ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ለሚመጣ ፡ ግዴታ ፡ ዋስ ፡ ለመሆን ፡ መቻሉን ፡ ይናገራል ፤ ይኸም ፡ ማለት ፡ ተያዥ ፡ የሚሆነው ፡ ሰው ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባው ፡ ተያዥ ፡ ሰጭውና ፡ ተያዥ ፡ ተቀባዩ ፡ ወደፊት ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ስምምነት፡ ተጨማሪ ፡ አላፊ ፡ ለመሆን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ተያዥ ፡ ሰጭውና ፡ ተቀባዩ ፡ ባደረ ጉት፡ስምምነት፡መሠረት ፡ ያልፈጸሙ ፡ እንደሆነ ፡ ለአፈጻጸሙ፡ተግባር፡አማካይ ፡ ለማድረ ግና ፡ ስምምነቱን ፡ ለማስፈጸም ፡ ነው ። ስምምነቱን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ከፈጸሙት፡ ግን ፡ በተያዡ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነትና ፡ ተጠያቂነት ፡ አይመጣበትም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ተያዥ ፡ ማለት ፡ በገደብ ፡ ያለ ፡ ዋስትና ፡ ማለት ፡ ነው። አዲሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በተያዥነቱ ፡ ግዴታ ፡ ላይ፡ የገንዘቡ ፡ መጠን ፡ ባይጠቀስም ፡ ተያዥ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ማናቸውም ፡ ተያዥ ፡ ሁሉ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ እንደሚሆን ፡ የጊዜው ፡ አሠራርና ፡ የሀገር ፡ ልማድ ፡ ያስገድደው ፡ እን ደነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ ያለበትም ፡ ሰው ፡ በተከሰሰ ፡ ጊዜ ፡ የሚ ያቀርበው ፡ ክርክር ፡ ተያዥነቴ ፡ ለዚህ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፡ ወይም ፡ ተያዥ ፡ አይደለሁም ፡ በማለት ፡ ነበር ።

አሁን ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ግን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በተያዥነቱ ፡ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ የገንዘቡ ፡ መጠን ፡ ካልተጠቀሰ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ አልሆንም ፡ የሚለው ፡ ክር ክር ፡ የተፈጠረው ፡ ከአዲሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መውጣት ፡ ወዲህ ፡ ለመሆኑ ፡ ተረጋግጧል ። ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ ይህንኑ ፡ ክርክር ፡ ያቀረበው ፡ በዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ተመርቶ ፡ ነው ።

ቁጥሩን ፡ እላይ ፡ በጠቀስነው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከጥንት ፡ ተያይዞ ፡ በመ ጣው ፡ ባሕልና ፡ ልማድ ፡ ዋስ ፡ ማለት ፡ ለታወቀ ፡ ነገር ፡ የተዋሰ ፡ ሲሆን ፡ ተጨ

ማሪ ፡ የመጠሪያ ፡ ስሙም ፡ የበሰላ ፡ ዋስ ፡ ይባል ፡ እንደነበረና ፡ ተያዥ ፡ ማለትም ፡ ልኩ ፡ ላልታወቀና ፡ ላልተገለጸ ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ የሚቆጠር ፡ እንደነበረ ፡ አረጋግጠናል።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፫ ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒነት ፡ ወይም ፡ ተስማሚነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ መመርመር ፡ ሊያስፈልገን ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆነበት ፡ የገንዘቡ ፡ መጠን፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ካልተገለጸ ፡ ዋስትናው ፡ ፈራሽ ፡ መሆኑን ፡ ሲያረጋግጥ ፤ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፫ ፡ ደግሞ ፡ ወደፊት ፡ ለሚሆን ፡ ግዴታ ፡ ዋስ ፡ መሆን ፡ መቻሉን ፡ ቢናገርም ፡ መብቱ ፡ ከምን ፡ ድረስ ፡ እንደሆነ ፡ ቀደም ፡ ባለው ፡ ንግግራችን ፡ የገለጽነው ፡ ስለሆነ ፡ የሁለቱም ፡ መንፈስ ፡ በገንዘብ ፡ አገላለጽ ፡ ረገድ ፡ ተደጋጋፊና ፡ ተባባሪ ፡ ተከታታይም ፡ ቃላት ፡ መሆናቸውን ፡ ተረድተናል ። ከዚህም ፡ ስናልፍ ፡ አንድ ፡ የምንገልጸው ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ ስለ፡ ተያዥነት ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ የሚገባ ፡ ሰውና ፡ ዋስትና ፡ ቀጣሪ ፡ የሆነው ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡ በመከተል ፡ የገንዘቡን ፡ መጠን ፡ በመለየት ፡ ሊዋዋሉ ፡ ሲገባ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ተዋውለው ፡ ቢገኙ ፡ ግን፡ የሥራ ፡ ውጤታቸው ፡ ይህን ፡ ክርክር ፡ ሊያስከትል ፡ መቻሉን ፡ ነው ። በተያዥነት ፡ ስም ፡ አጠራር ፡ ብቻ ፡ ጥንተ ፡ ልማድን ፡ በመከተል ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ ገብተሃልና ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ ትሆናለህ ፡ በማለት ፡ በደፈናው ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ። ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ባሕልና ፡ ልማድ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተሳታፊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ጐጂ ፡ የሚሆነውና ፡ የማይጠቅመው ፡ ደግሞ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ስምና ፡ ስፍራ ፡ እንዳልተሰጠው ፡ የታወቀ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ ሊሰጠውም ፡ እንደማይገባ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ባላወቀውና ፡ ባልተረዳው ፡ ነገር ፡ ባለዕዳ ፡ ለማድረግ ፡ ሕሊናው ፡ ስለማይቀበለውና ፡ ከክፉ፡ አድራጎትም ፡ የሚቆጥረው ፡ ስለሆነና ፡ ሕጉም ፡ ይህንኑ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የማይጠቅመውንና ፡ ጐጂውን ፡ ልማድ ፡ ስፍራ ፡ አሳጥቶት ፡ በመገኘቱ ፡ ሕግ ፡ ማለትም ፡ በትክክለኛነቱ ፡ የሰው ፡ ሕሊና ፡ አምኖ ፡ የሚከተለው ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በዚህ ፡ ግዴታ ፡ ተጠያቂነት ፡ የለበትም ፡ እንላለን ፤ ምክንያቱም ፡ ስለሕጐቹ ፡ አተረጓጐም ፡ ቀደም ፡ አድርገን ፡ የዘረዘርነው ፡ ቢሆንም ፡ ለፍርዳችን ፡ ማጠቃለያ ፡ በማድረግ ፡ በተጨማሪ ፡ የምንጠቅሰው ፡ ቀድሞ ፡ በልማድ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፶፯ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተሻረ ፡ ስለሆነ ፡ በተሻረ ፡ ልማድ ፡ መገልገል ፡ ስለማይቻል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዘረዘርነውና ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ ካልተገለጸ ፡ ፈራሽ፡ መሆኑ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፳፪ ፡ እና ፡ ሺ፱፻፳፫ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥሮች ፡ በተባባሪነት፡ ስለሚያስረዱና ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ከሕጉ ፡ መንፈስ ፡ ውጭ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡ ፍርዱን ፡ ሽረን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ።

ይኸውም ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተደረጉትን ፡ የተያዥ ፡ ግዴታዎች ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ አይነካቸውም ፡ ብለናል ። ፍርዱ ፡ መለወጡን ፡ እንዲያውቀው ፡ ግልባጩ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይተላለፍ ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፫ኛ ፡ ችሎት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ተሰጠ ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 3

Justices:

Vice Afenegus Abeje Debalke
Ato Wobe Woldeyes
Ato Damte Fanta

KETEMA HAILE v. ETHIOPIAN ELECTRIC LIGHT & POWER AUTHORITY

Civil Appeal No. 230/59

Contracts—Suretyship—Form of contract—Specification of amount of guarantee—Civil Code Arts. 1679, 1690, 1713, 1887, 1920, 1922, 1925.*

Application of Civil Code—Interpretation—Mandatory provisions—Civil Code Arts. 3347(1), 1731(3).

An appeal from the decision of the High Court ordering the guarantor to pay the guarantee, where the amount of the guarantee was not specified in the contract.

Held: Decision reversed.

1. Since the Civil Code provides for all civil matters, all rules whether written or customary concerning matters provided in the Code are repealed.

2. A guarantee, customarily a special part of suretyship, now comes under the suretyship provisions of the Code.

3. Contracts entered into since the coming into force of the Civil Code must specify the amount guaranteed. Civ. Code Art. 1922(3).

4 Since Art. 1922(3) is a mandatory provision, an argument based on pre-Code contract law is of no avail where the disputed contract was made subsequent to the coming into force of the Code.

5. Consent of both parties is not enough to render a contract enforceable where mandatory provisions of the law have not been adhered to.

6. Arts. 1922(3) and 1925 do not conflict. A future debt can be guaranteed, when it is in the form required for other contracts of guarantee.

The appellant and one Ghebreyes Wolde were sued jointly in the High Court in an action to recover E $ 7, 643 which sum was the amount the latter embezzled from the EELPA. The appellant was joined in the suit as guarantor.

The first defendant submitted no statement of defense in this present civil case. Prior to this case he was prosecuted criminally and upon his admission that he had put the sum in question to his own use and his plea of guilty, he was sentenced to two years imprisonment. Furthermore, he stated that he was not willing to appear in or defend the present case.

The second defendant admitted that he was the first defendant's guarantor but only in so far as the latter was employed as a clerk. The latter's employment as a cashier, he argued, was beyond the scope of his guarantee. He further argued

**Eds. Note:* Arts. 1725 and 1727(2) provide for additional forms of contracts of guarantee. Under these articles a contract of guarantee must be in writing and attested by two witnesses. In this case it appears that the contract was attested by two witnesses.

that the guarantee was of no effect because it did not, as is required by Civil Code Article 1922 specify the amount for which it was given.

The High Court rejected this argument on the ground that the provision cited dealt with giving a guarantee for a specified amount and not with what was involved in the present case, namely "teyajinet." Hence, it ordered the teyaj, i.e., the second defendant, to pay off the debt incurred by the first defendant, wherefore this appeal.

The essence of the appeal is that the guarantee only covered the situation where the first defendant was employed as a clerk and not as a cashier or storekeeper. Moreover it would be of no effect because the amount it was given for was not specified in the instrument as is required by Civil Code Article 1922 (3). The appellant therefore requested that the High Court decision be reversed.

The respondent's representative pointed out that the appellant had undertaken to be held responsible for any delict committed by the first defendant while in the employment of the respondent. Civil Code Articles 1679, 1680, 1713, 1886 and 1920 he said, support the High Court decision, which decision ought to be affirmed.

This case raises several legal issues. Article 1922 cited by the appellant states that "a guarantee shall not be presumed, it shall be express and may not be extended beyond its contractual limits, and the contract of guarantee shall be of no effect unless it specifies the maximum amount for which the guarantee is given." The instrument profferred in evidence shows that the appellant undertook to act as a "teyaj" on June 10, 1962, i.e. two years after the coming into force of the Civil Code. We have also examined the provisions cited by respondent's representative.

Articles 1679 and 1680 talk about the consent and express agreement of the parties to a contract. As pointed out earlier the appellant's principal argument is that he ought not be ordered to discharge an obligation based on a legally ineffective contract. The provisions cited by respondent are irrelevant to this case because the contracting parties' consent to conclude a contract cannot validate a contract which does not observe the requirements laid down by the law. This is so because mandatory provisions of the law must be adhered to by contracting parties.

Secondly, Article 1886 states that the parties may extend their liability under the contract and provide that they will be liable for non-performance notwithstanding that performance is prevented by force majeure.

Since there is nothing here to show that the contract was not performed because of force majeure this Article too is irrelevant.

Thirdly, Article 1920 states that "whosoever guarantees an obligation shall undertake towards the creditor to discharge the obligation, should the debtor fail to discharge it." And this case revolves around Articles 1920 and 1922 cited by respondent and appellant respectively. We will examine these provisions to decide whether or not the concept of guarantee embraces that of "teyajinet".

Article 1925 provides that there could be a future and conditional guarantee. This means that the "teyaj" would have to be held responsible as regards any future agreement that may be concluded between the person who produced the "teyaj" and the one who demanded it.

In other words, the "teyaj" is there to ensure the execution of the agreement should one of the parties fail to discharge his obligation. Thus, "teyajinet" connotes

a limited form of guarantee. Before the coming into force of the Civil Code, it was obvious that a "teyaj" would be held liable regardless of whether or not the exact amount for which he stood "teyaj" was specified. And when such a "teyaj" was sued, he would argue that this "teyajinet" did not cover the situation in question or that he was not "teyaj" at all.

The present case of "teyajinet" though, falls within the purview of the Civil Code. Under pre-code law a guarantor or "wass" undertook to guarantee an unspecified debt.

We will now proceed to consider whether Article 1925 clashes with Article 1922 or is consistent with it. While Article 1922 requires that the maximum amount be stated in the instrument of guarantee, Article 1925 deals with the possibility of giving a guarantee merely for a future obligation. Bearing in mind what we said earlier with respect to the latter, we come to the conclusion that these two provisions are consistent when it comes to specifying the amount the guarantee is given for.

It was the failure of the guarantor and the concerned department to specify the maximum amount of the guarantee, as is required by the Civil Code, which gave rise to the present dispute. The court cannot accept the argument that one could be held liable as a "teyaj" in accordance with the old customary rules. Past practices which are found to be useful are included in the new law, while harmful ones are rejected. A person should not be bound by a contract of guarantee which does not specify the maximum amount the guarantee is given for. To impose such an obligation on a person is unjust. It is for this reason that the concept of "teyajinet" was rejected by the Civil Code. The law must be fair and acceptable to the sense of justice of the community.

As we said earlier, a contract of guarantee is of no effect unless the maximum amount of the guarantee is specified. According to Article 3347(1) of the Civil Code, customary rules previously in force have been repealed.

We find that the High Court's judgment is contrary to the law. We therefore reverse the judgment of the High Court and hold that the appellant is not bound by the contract of guarantee. However, this judgment does not affect contracts of guarantee entered into before the Civil Code was promulgated. A copy of this judgment shall be forwarded to the High Court.

This judgment is given by a majority.

June 28, 1968

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፯ኛ ፡ ችሎት ፡፡

ዳኞች ፤

አቶ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ትንሣኤ ፤

አቶ ፡ ከበደ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡፡

ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡

መልስ ፡ ሰጭ ፤ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፶፱/፷

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፶፱/፷ ስለ ፡ ንብረት — በቀዳሚነት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት፡ መብት — የጋራ ፡ ባለሀብትነት — አለቃ ፡ እና ፡ ምንዝር ፡— ስለ ፡ ወለድ ፡ አገድ ፡— የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፫፻፹፰ ፡ ፩ሺ፫፻፺፯—፩ሺ፫፻፺፰ ፡፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡— ፍርድ ፡— ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለመሆኑ ፡— የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩/፩ ፡ ፪፻፲፭ ፡ ፪፻፵፪ — ፪፻፵፰ ፡፡

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሳሽ ፡ አንደኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ለሁለተኛው ፡ ተከሳሽ ፡ በወለድ ፡ አገድ ፡ ውል መሠረት ፡ ያስረከበውን ፡ መሬት ፡ በቀዳሚነት ፡ እንድገዛ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ሲል ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ውድቅ ፡ አድርጎ ፤ ሁለተኛው ፡ ተከሳሽ ፡ የወለድ ፡ አገዱ ፡ ውል ፡ እንዲደረግ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብሎ ፡ የወሰደውን ፡ መሬት ፡ ለአንደኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ይመልስ ፡ ሲል ፡ ስለፈረደ ፤ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ ሁለተኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ያቀረበው ፡ ይግባኝ ፡፡

ውሳኔ ፡— ፍርዱ ፡ ተሽሯል ፡፡

፩/ የመሬቱ ፡ ባለሀብትነት ፡ የተላለፈው ፡ ባለዕዳው ፡ እዳውን ፡ ሳይከፈል ፡ ቀርቶ ፡ በወለድ ፡ አገድ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ በቀዳሚነት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ አይኖርም ፡፡

፪/ የአለቃና ፡ ምንዝር ፡ ሁኔቴ ፡ መኖር ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ሁኔቴ ፡ መኖሩን ፡ አያስረዳም ፡፡

፫/ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክስ ፡ ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ አይችልም ፡፡ ስለሆነም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ተከስው ፡ ሲገኙ ፡ አንደኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ክስ ፡ ሳያቀርብ ፡ ሁለቱም ፡ የተከሰሱበትን ፡ ክስ ፡ መከታ ፡ በማድረግ ፡ በሁለተኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ላይ ፡ ሲያስፈርድ ፡ አይችልም፡፡

ፍርድ ፡፡

የክሱ ፡ መሠረት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ነው ፡፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ ባይ ፡ የስር፡ ከሳሽ ፡ ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ ነው ፡፡ የስር ፡ ተከሳሾች ፡ አቶ ፡ ያደቴ ፡ ሮቢና ፡አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ነበሩ ፡፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የተባለበትን ፡ መሬት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የገዛው ፡ ወይንም ፡ በወለድ ፡ አገድ ፡ የያዘው ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡፡ አቶ ፡ ያደቴ ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ ተብሎ ፡ ክርክር ፡ ለቀረበበት ፡ መሬት ፡ ባለሃብት ፡ ነው ፡፡ አቶ ፡ ያደቴ ፡ ክርክር፡ ከተነሳበት ፡ መሬት ፡ ከፊል ፡ አድርጎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በወለድ ፡ አገድ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ተቀብሎ ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ሰጥቶታል ፡፡ ያደቴን ፡ የወለድ ፡ አገዱ ፡ ዘመን ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ወልደማርያም ፡ ገንዘቤን ፡ መልስ ፡

ብሎ ፡ ስላስጨነቀው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፤ ስልሳ ፡ ብር ፡ ጨምሮ ፡ ሊከፍል ፡ ፩፻፷ ፡ ብር ፡ ለመክፈል ፡ ባይችል ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ ሊለቅ ፡ ስምምነት ፡ አድርጓል ። ያደቴ ፡ ፩፻፷ ፡ ብር ፡ ለመክፈል ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይከፍል ፡ ስለቀረ ፡ ክርክር ፡ የተነሳበት ፡ መሬት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሚያወጣ ፡ መሆኑ ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ ተላልፎለት ፡ ለመሬት ፡ አለቃው ፡ ግብር ፡ ከፍሎበታል ይባላል ። ወልደ ፡ ማርያም ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ሁኔታ ፡ በይዞታው ፡ ስር፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፤ ያሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የስር ፡ ከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ በያደቴና ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ ላይ ፡ የግዥ ፡ መብት ፡ ለኔ ፡ በቅድሚያ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ ከሷል ። ሁለቱም ፡ የስር ፡ ተከሳሾች ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የነገሩን ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጠው ፡ ጠቅሰው ፡ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ አልሸጥኩም ፡ ሳላይ ፡ ሳልሰማ ፡ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠበት ፡ ሲል ፤ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ደግሞ ፡ ግዥው ፡ ለኔ ፡ ይጸናል ፡ ሲል ፡ ተከራክሯል።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ ገዝቷል ፡ የተባለው ፡ ገዥ ፡ የገዛበትን ፡ ውል ፡ ወይንም ፡ ሰነድ ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ፤ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ በስር ፡ ከሳሹ ፡ በያደቴና ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ ግዥ ፡ ተፈጽሟል ፡ ሲል ፡ ያቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ የእርቅ ፡ ድርድርን ፡ የሚያሳይ ፡ እንጂ ፡ የግዥ ፡ ውል ፡ መፈጸሙን ፡ ስለማያሳይ ፡ ክሱን ፡ ይለቃል ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ክስ ፡ ባልቀረበበት ፡ ጭብጥ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ከያደቴ ፡ የወሰደውን ፡ መሬት ፡ ለወለድ ፡ አግድ ፡ የሰጠውን ፡ ፩፻፷ ፡ ብር ፡ ተቀብሎ ፡ ይመልሳል ፡ ሲል ፡ ፈርዷል ። በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ያሉት ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁንና ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ናቸው ። የአቶ ፡ ታደሰ ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ይህ ፡ ቁጥሩ ፡ ፪፻፶፱/፷ ፡ ሲሆን፡ የአቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ደግሞ ፡ ፫፻፶፱/፷ ፡ ነው ። የሁለቱ ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ዓላማ ፡ ምንም ፡ የተለያየ ፡ ቢሆን ፡ የጭብጡ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ስለሆነ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ (፩) ፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ ቁጥሩ ፡ ፪፻፶፱/፷ ፡ በሆነው ፡ መዝገብ ፡ የወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ይግባኝ ፡ ተጣምሮ ፡ እንዲታይ ፡ አድርገናል ።

በይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፱ /፷ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የሆነው ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ያቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ቅሬታ ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ በገደብም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ ለአቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በውል ፡ ማሳለፉ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ግዥ ፡ አይገባህም ፡ የተባልኩት ፡ በትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፶፱/፷ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የሆነው ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ደግሞ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ በግል፡ ፈቃዱ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ አስይዞኝ ፡ የነበረውን ፡ መሬት ፡ በገደብ ፡ ርስትነቱን ፡ አስተላልፎልኝ ፡ ባለሁበት ፡ ሆኜ ፡ ከገበርኩበት ፡ በኋላ ፡ ውል ፡ ይፍረስልኝ ፡ ብሎ ፡ ክስ ፡ ሳያቀርብብኝ ፡ መሬቱን ፡ እንድለቅለት ፡ የተፈረደው ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ነው ።

መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ እንደተረዳነው ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ የሚለውን ፡ ክስ ፡ ያቀረበው ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ በያደቴ ፡ ሮቢና ፡ በአቶ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ላይ ፡ ነው ። ያደቴ ፡ ሮቢም ፡ ሆነ ፡ ወልደማርያም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽ ፡ ሆነው ፡ የታደሰን ፡ ክስ ፡ ከመከላከል ፡ በቀር ፡ የተከሳሽ ፡ ከሽሳ ፡ ሆነው ፡ ያቀረቡት ፡ ክስ ፡ እንደሌለ ፡ መዝገቡ ፡ ይገልጻል ። የግዥ ፡ ይገባኛል፡ ባዩን ፡ ይግባኝ ፡ እንመረምራለን ።

፩ኛ/ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ ክስ ፡ ለቀረበበት ፡ ነገር ፡ ይጠቅሙኛል ፡ ሲል ፡ የጠቀሳቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ ፩ሺ፯፻፲፪ ፡ ፩ሺ፯፻፲፫፡ ፩ሺ፯፻፲፱ ፡ ናቸው ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ አቶ ፡ ታደሰን ፡ የሚደግፉት ፡ ወይም ፡ የማይደግፉት ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ያስፈለገው ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ በአቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያምና ፡ በአቶ ፡ ያደቴ ፡ መካከል ፡ ሽያጭና ፡ ግዥን ፡ የሚያቋቁም ፡ ውል ፡ ባለ ፡ መቅረቡ ፡ ይመስላል ። በያደቴ ፡ ሮቢና ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ የሚመለከቱት ፡ የግዥ ወይም ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ አልተቋቋመም ። አቶ ፡ ታደሰ ፡ በያደቴና ፡ በወልደ ፡ ማርያም፡ መካከል ፡ ግዥ ፡ ወይንም ፡ ሽያጭ ፡ ተቋቁሟል ፡ ብሎ ፡ ያቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ የሚያሳየው ፡ ያደቴ ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ያስያዘውን ፡ መሬት ፡ የወለድ ፡ አግዱን ፡ ገንዘብ ፡ ለመመለስ ፡ ባለመቻሉ ፡ መሬቱን ፡ የለቀቀለት ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ይህ ፡ የሀብትነት ፡ ማስተላለፍያ ፡ መተማመኛ ፡ ስጦታ ፡ ወይንም ፡ ግዥ ፡ አለዚያም ፡ አደራ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ስለሆነ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ፡ከጠቀሳቸው፡ ቁጥሮች ፡ ጋር ፡ ተባባሪነትን ፡ አያገኝም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ን ፡ ብንመለከት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ ባዩ ፡ ለተሸጠው ፡ ነገር ፡ የጋራ፡ ባለሀብት ፡ እንዲሆን ፡ ያስገድዳል ። በያደቴና ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ የግዥ፡ ውል ፡ አልተገኘም ፡ እንጂ ፡ ተገኝቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ በጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ግዥ ፡ ይገባኛል ፡ ለማለት ፡ ለተሸጠው ፡ ነገር ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ አለው ፡ ወይ ? አቶ ፡ ታደሰ ፡ ግዥው ፡ ይገባኛል ፡ ለማለት ፡ መግቢያ ፡ ያደረገው ፡ ወራሽ ፡ ያደረገችኝ ፡ እሙት ፡ እህተ ፡ ማርያምና ፡ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ አለቃና ፡ ምንዝር ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ፡ ይላል ። አለቃና ፡ ምንዝር ፡ መሆን ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ እንደተጻፈው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ያሳያል ፡ ወይ ? የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ያልተከፈለ ፡ ንብረት ፡ በብዙ ፡ ባለድርሻዎች ፡ ስም ፡ በህብረት ፡ የተያዘና ፡ ክፍያን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድርሻውን ፡ ለይቶ ፡ መብቱን ፡ አረጋግጦ ፡ በስሙ ፡ የሚገብረውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ለመጠየቅ ፡ አይደለም ። በእነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ፩ኛ ፡ በያደቴ፡ ሮቢና ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ ስለግገር ፡ የተቋቋመ ፡ ውል ፡ አለመኖሩን ፡ አይተን ፤

፪ኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ የጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ በያደቴና ፡ በወልደ፡ማርያም ፡ መካከል ፡ የተቋቋመ ፡ የግዥ ፡ ውል ፡ ኖሮ ፡ እንኳን፡ ቢሆን ፡ የግዥ ፡ ቀደምትነት ፡ ለማግኘት ፡ የማይደግፈው ፡ መሆኑን ፡ አስተውለን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ የግዥ ፡ መብት ፡ የለውም ፡ ሲል፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አጽንተናል ። በተሸጠ ፡ ጊዜ ፡ የግዥው ፡ ቀደምትነት ፡ ለአሁኑ ፡ ከሳሽ ፡ እንዲሆን ፡ መብታቸውን ፡ ጠብቀናል ፡ ያለውን ፡ አልተቀበልነውም ።

ከዚህ፡ቀጥለን ፡ የአቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያምን ፡ ይግባኝ ፡ እንመለከታለን ። የአቶ ፡ ወልደ ማርያም ፡ ጥያቄ ፡ ሳልከሰስ ፡ ሳልወቀስ ፡ በእርቅ ፡ የጨረስኩትን ፡ መሬት ፡ እንድለቅ፡ ተፈረደብኝ ፡ ባይ ፡ ነው ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪፻፵፮ ፡ ፪፻፵፪ ፡ ፪፻፵፫ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ሳይመራ ፡ አቶ ፡ ወልደ ማርያም ፡ ይግባኝ ፡ ያለበትን ፡ ፍርድ ፡ ስለሰጠ ፡ ይግባኙን ፡ ተቀብለነዋል ። አንድ ፡ ሰው ፡ የፍርድ ፡ ባለቤት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፰ ፡ መሠረት ፡ የተጻፈውን ፡ አከናውኖ ፡ ክስና ፡ ጭብጥ ፡ የመመሥረት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ። ዳኝነት ፡ ያልከፈለ ፡ ጭብጥ ፡ ያልመሠረተ ፡ ሰው ፡ የፍርድ ፡ ባለ ቤት ፡ ለመሆን ፡ እንደማይችል ፡ በሕጉ ፡ የተገለጠ ፡ ነው ። ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ በከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቁጥሩ ፡ ፩፻፴፩/፶፪ ፡ በሆነው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሽ ፡ ነበር ። ያደቴ፡ ሮቢ ፡ የአቶ ፡ ታደሰ ፡ ካሣሁንን ፡ ክስ ፡ ሲከላከል ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሕገ ፡ ወጥ፡

በሆነ ፡ መንገድ ፡ መሬቱን ፡ የወሰደበት ፡ መሆኑን ፡ ገልጿል ። የያደቴ ፡ ሮቢ ፡ አገላለጥ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ስሜት ፡ ስለነካው ፡ ከጭብጡ ፡ ውጪ ፡ ከሳሽ ፡ ባልተነሳበት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጡ ። ይህም ፡ ውሳኔ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ከያደቴ፡ በ፩፻፳፡ ብር፡ የወሰደው ፡ መሬት ፡ ፫ሺ ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ፫ሺ ፡ ብር፡ የሚያወጣውን ፡ መሬት ፡ በ፩፻፳ ፡ ብር ፡ እርቅ፡ወልደ፡ማርያም፡ የወሰደው፡የያደቴን፡ደካማነት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ፡ስለሆነ፡፩፻፳፡ብር ፡ ከያደቴ፡ተቀብሎ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ለያደቴ፡ መሬቱን ፡ ይመልሳል ፡ የሚል ፡ ነው ። ይህ ፡ ውሳኔ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን፡ የተከተለ፡ ባለመሆኑ ፡ አልተቀበልነውም ። በያደቴና ፡ በወልደ ፡ ማርያም፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ነገር ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ጥሩ ፡ ተብሎ ፡ ተቀባይ ፡ ያገኝ ፡ የነበረው፡ ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተመርቶ ፡ ቢሆን ፡ ነበር ። ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ በታደሰ ፡ ካሣሁን ፡ ክስ ፡ ተጠርቶ ፡ ቀርቦ ፡ ጉዳቱን ፡ ቢያመለክት ፡ እንዴት ፡ ፍርድ ፡ ይሰጠዋል ? በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶፱/፳ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ቀን፡፲፱፻፳ ፡ ዓ፡ም ፡ “ከያደቴ፡ ሮቢ ፡ በ፩፻፳ ፡ ብር፡ግምት፡ወልደ፡ማርያም ፡ የወሰደውን ፡ መሬት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ ብሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ለያደቴ ፡ ሮቢ ፡ ይለቃል” ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፵፰ ፡ መሠረት ፡ ሽረነዋል ። ያደቴ ፡ ሮቢ ፡ በወልደ ፡ ማርያም ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 6

Justices:

Ato Gebre Michael Wolde Tensae

Ato Kebede Habte Mariam

TADESSE KASSAHUN v. YADETE ROBI

Civil Appeal No. 259/60.

Property—Joint ownership—Right of recovery—"Aleka" and "minzir"—Antichresis—Civil Code Arts. 1384, 1397, 1399.

Civil Procedure—Judgments—Filing a suit—Civ. Proc. Code. Arts. 11(1), 215, 246-48

An appeal by the second defendant from the the decision of the High Court rejecting plaintiff's claim to a right of recovery on the land transferred to the second defendant by the first defendant pursuant to a contract of antichresis, and ordering the second defendant to transfer the land back to the first defendant upon receipt of the money involved in the contract of antichresis.

Held: Decision reversed.

1. There is no right of recovery on land transferred to a creditor pursuant to a contract of antichresis upon the debtor's default of payment.

2. The existence of "aleka" and "minzir" relations does not prove joint ownership.

3. A court can only render judgment where a dispute has been argued before it. Where one defendant had no chance to argue his position, the plaintiff cannot obtain judgment as against that defendant.

JUDGMENT

Appellant's original cause of action was founded upon his claim that he was the person entitled to purchase the parcel of land involved in this dispute. Ato Yadete was the original owner of the land. Later on Ato Yadete delivered part of the land to Ato Wolde Mariam Wolde Michael after receiving one hundred dollars from the latter, thereby creating a contract of antichresis. Soon after, prior to the expiry of the contract, Ato Wolde Mariam urged Yadete to repay him the said sum of money. Consequently the latter agreed to raise the amount to E$ 160 and repay it within a fixed period of time. It was also included in this new agreement that Yadete would transfer the piece of land in question to Wolde Mariam if the money was not paid within the said time. The period fixed in the contract expired without Yadete paying back the money. Consequently, Wolde Mariam took over the ownership of the land and it is said that he thereafter paid land tax in his own name. This was done without taking into consideration the actual value of the land. Following this the present appellant brought suit against both Yadete and Wolde Mariam claiming that he was the person entitled to pre-empt the land in question. In the High Court, Yadete denied having sold the land to Wolde Mariam. Furthermore, he argued that the Awradja Court decided the issue without his slightest knowledge of the matter. On the other hand, Wolde Mariam argued that the sale was carried out properly.

The High Court reasoned that a person who alleges that a piece of land was sold to him, should produce documents to that effect. The document plaintiff introduced, the court said, proves the settlement of the differences between the two parties but does not prove the existence of the alleged sale. It therefore dismissed the suit which involved the present appellant and Wolde Mariam.

It then took up an issue that was not raised in the suit and decided that Wolde Mariam should receive E $160 and give the land back to Yadete. Both Ato Tadesse, original plaintiff, and Wolde Mariam appealed from this judgment in Civil Appeal No. 259/60 and 359/60 respectively. Although the purposes of the two appeals differ, the basic issues are the same in both. We have therefore consolidated them in accordance with Article 11(1) of the Civil Procedure Code.

The statement of appeal filed by Tadesse contained the argument that it was erroneous to dismiss his request once it was proved that the said land was transferred to Ato Wolde Mariam, be it because of time limit or any other way.

The other appellant, Ato Wolde Mariam, argued that he was ordered to give up his property without any suit being brought against him. He said he was denied his right to own land that was properly transferred to him.

An examination of the record of the lower court discloses that the original suit was brought by Ato Tadesse Kassahun against both Ato Wolde Mariam and Ato Yadete. Evidently the latter two were defendants throughout the suit and as such they never took opposite sides as plaintiff and defendant.

To start with, we shall deal with the issue raised by Ato Tadesse.

Firstly, Ato Tadesse cited Civil Code Articles 1388, 1397, 1398, 1399 as provisions of the law supporting his claim that he has the right to buy the piece of land. The High Court did not say whether or not the above provisions were relevant to the issue. This, it seems, was because the appellant himself did not prove the existence of a contract of sale. The document produced by Tadesse shows that the said land was transferred to Wolde Mariam because Yadete failed to pay the sum of money specified in their contract. This form of transferring ownership is neither a gift nor a sale nor a bailment. Consequently, the provisions of the code cited by Ato Tadesse are irrevelant to the case at hand. For instance, Article 1388 requires that the party who demands the recovery of a disposed piece of property be a joint-owner. Then the question arises whether Ato Tadesse was a joint-owner of the land he intends to buy. Ato Tadesse bases his claim on the ground that he was the heir to Woizero Ehte Mariam. Woz. Ehte Mariam and Ato Yadete were "Aleka and Minzir". Again the question should be asked whether being "Aleka" and "Minzir" establishes joint-ownership as required in Article 1388. Joint-ownership means owning a whole piece of property while awaiting its division among a number of people. It therefore excludes private exclusive ownership.

We have thus established that no contract of sale existed between Yadete and Wolde Mariam. Secondly , even if there was any such contract, Ato Tadesse does not satisfy the requirements of Article 1388. For all the above reasons we have reached the conclusion that Ato Tadesse does not have the exclusive right to buy the land in question. To that extent we affirm the decision of the High Court. Nevertheless we reject that part of the High Court's decision which recognized Tadesse's right of pre-empting the land if the owner decides to sell it.

We shall now consider the appeal filed by Ato Wolde Mariam. This Court has accepted the appeal because the High Court gave the judgment ordering this

appellant to give back the said land to Ato Yadete without paying any attention to Articles 246-248 of the Civil Procedure Code.

To have a cause of action against another, one must first satisfy Article 215 of the Civil Procedure Code. Moreover, he must bring a suit which establishes a cause of action. That one who fails to do so may not secure a judgment against another has been clearly stated by the law. In this case Yadete Robi was a defendant defending the charge brought against him by Tadesse Kassahun. During the course of the trial he mentioned that Wolde Mariam, who was also a defendant, took the land in an illegal manner. This complaint aroused the sympathy of the lower court as a result of which it ruled upon an issue that was not raised before it. Consequently, it was reasoned that Wolde Mariam took advantage of Yadete's weakness and took the land for only E $160 while its actual value was E $ 3000. Wolde Mariam was ordered to transfer the land back to Yadete after payment of E $160. This court rejects this decision since it was made without any regard to procedure. The judgment could have been approved if Yadete had brought suit against Wolde Mariam. For all the above reasons we quash the decision of the High Court which ordered the transfer of the land to Yadete Robi. Yadete's right to bring suit against Wolde Mariam is reserved.

May 16, 1968

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ፤ ፪ኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

አፈንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤

አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤

ቀኛዝማች ፡ ሙላት ፡ በየነ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፤

መልስ ፡ ሰጭ ፡ ዓለሙ ፡ ኡርጋ ፡ ዓለሙ ፡ ቦሩ ፡ ፍሬ ፡ ቦሩ ።

የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፴፮/፷

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡— በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ስለማቆየት ፡— የወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ ፶፱ ፡ ፩፻፱ ።

የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሽ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶፱ ፡ አይፈቅድም ፡ ሲል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

<u>ውሳኔ</u> ፡—   ትእዛዙ ፡ ተሽሯል ።

፩/ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ መሠረት ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ሲደርሰው ፡ ምርመራው ፡ በቂ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፱ ፡ እንደሚያዘው ፡ የምርመራው ፡ መዝገብ ፡ በደረሰው ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ተጨማሪ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

፪/ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ እና ፡ ፩፻፱ ፡ የተዘረዘረ ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ እንዲችል ፡ በተከሳሽ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ እስከወሰን ፡ ድረስ ፡ በቁጥር ፡ ፶፱ ፡ መሠረት ፡ ለፖሊስ ፡ የተሰጠው ፡ ተከሳሽ ፡ ማረ ፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ይህን ፡ ይግባኝ ፡ ያቀረበው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወንጀል፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፷፻፷፬/፷ ፡ የሰጠው ፡ ትዕዛዝ ፡ ይለወጥልኝ ፡ በማለት ፡ ነው ። ዐቃቤ፡ ሕግ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ያቀረበውን ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ መርምረን ፡ በከፍተኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወሰነውን ፡ ተመልክተን ፡ የነገሩን ፡ አመጣጥና ፡ በሕግም ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ካረጋገጥን ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥተናል ።

<u>ውሳኔ ።</u>

እነ ፡ ዓለሙ ፡ ኡርጋ ፡ ሰው ፡ ገድለዋል ፡ በመባል ፡ በፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ተይዘው ፡ ታስረው ፡ ጉዳዩ ፡ ከተመረመረ ፡ በኋላ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ የምርመራውን ፡ ውጤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሲያስተላልፍ ፡ ክሱ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ የተያዙት ፡ ሰዎች ፡ ስለሚቆዩበት ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፶፱ ፡

መሠረት ፡ ውሳኔ ፡ ይስጥበት ፡ በማለት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አመልክቷል ።
የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ያቀረበለትን ፡ ጥያቄ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ የተደነገገው ፡ የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ ያልተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ እስከዚያውም ፡ ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ የሚያስችል ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ የቀረበልንን ፡ ጥያቄ ፡ አይመለከትም ፡ ብሎ ፡ በማተት ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ይግባኝ ፡ ያለው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ የተደነገገውን ፡ በማጥበብ ፡ ተርጉሞታል ፡ በማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በትርጉም ፡ ተሳስቷል፡ ወይም ፡ አልተሳሳተም ፡ ለማለት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የደነገገውን ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንደደነገገው ፡ የወንጀልን ፡ ተግባር ፡ የሚከታተልና ፡ የሚመረምር ፡ ፖሊስ ፡ ነው ። ፖሊሱ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ በሚመረምርበት ፡ ጊዜ ፡ ወንጀሉን ፡ ሠርቷል ፡ የተባለውን፡ ሰው ፡ መያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ አለበለዚያም ፡ ሕጉ ፡ የሚፈቅድ ፡ ሲሆን ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ይዞ ፡ ወንጀሉን፡ ሊመረምር ፡ ይችላል ። ወንጀለኛው ፡ የተያዘው ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሆን ፡ ምርመራው ፡ ቢያልቅ ፡ ባያልቅም ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ በ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ወንጀለኛውም ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ላይ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የተያዘው ፡ ሰው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቆይ ፡ ወይም ፡ በዋስ ፡ ይለቀቅ ፡ ብሎ ፡ መወሰን፡ አለበት ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ አጠናቅቆ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠውና ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀለኛው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያዝለት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። በዚህ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈቅደው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ከአሥራ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ላይ ፡ የሚደነግገው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጠው ፡ ሲሆን ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ የሰጠው ፡ ትርጉም ፡ መርማሪ ፡ ፖሊስ ፡ በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቆይልኝ ፡ የማለት ፡ ጥያቄ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ ነው ። ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ትርጉም ፡ አይስማማም ፤ የማይስማማበትንም ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንገልጻለን ።

በመሠረቱ ፡ ማናቸውም ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ የሚመረመረው ፡ በፖሊስ ፡ አማካይነት ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ የሚሰማው ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በኩል ፡ ነው ። ፖሊስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚያዘውን ፡ ተከትሎ ፡ ተሠራ ፡ የተባለውን ፡ ወንጀል ፡ ከመረመረና ፡ ማስረጃውንም ፡ ካጠናቀቀ ፡ በኋላ ፡ የምርመራውን ፡ ውጤት ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ማስተላለፍ ፡ እንዳለበት ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፴፯ ፡ ተደንግጓል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ የፖሊሱ ፡ የምርመራ ፡ ውጤት ፡ ሲደርሰው ፡ በቁጥር ፡ ፴፰ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ወይም ፡ ምርመራው ፡ እንደገና ፡ ይጣራ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምርመራው ፡ በቂ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ የሚያቀርብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ደግሞ ፡ የምርመራው ፡ ውጤት ፡ በደረሰው ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ እንዳለበት ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፱ ፡ ላይ ፡ ይደነግጋል ። እንግዲህ ፡ የወንጀሉ ፡ ምርመራ ፡ በፖሊስ ፡ በኩል ፡ የተጣራ ፡ ነው ፡ ቢባልም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምርመራው ፡ እንደገና ፡ ይጣራ ፡ ብሎ ፡ ለማዘዝ ፡ ወይም ፡ ምርመራው፡ በቂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የምርመራው ፡ ውጤት ፡ በደረሰው ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ክስ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለማቅረብ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ከሆነ ፤ የሥነ ፡ ሥርዓት፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ላይ ፡ የደነገገው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የተሰጠውን ፡ ተግባር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚያስችለው ፡ መንገድ ፡ መተርጐም ፡ ይኖርበታል ። ከላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ፖሊስና ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በወንጀል ፡ ረገድ ፡ የተሰጣቸው ፡ ተግባርና ፡ ሥልጣን ፡ ተወራራሽ ፡ በመሆኑ ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ፡ በማረፊያ ፡ የሚቆይበትን ፡ ሁኔታ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማስወሰን ፡ የተሰጠው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግም ፡ የፖሊሱን ፡ ምርመራ ፡ በሚያጠናበት ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የፖሊስን ፡ ምርመራ ፡ መዝገብ ፡ አጥንቶ ፡ ክስ ፡ እስኪያቀርብ ፡ ድረስ ፡ ጉዳዩ ፡ በምርመራ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ስለሚቆጠርና ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሹ ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ሊቆይ ፡ ስለማይችል ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፵፱ ፡ መሠረት ፡ የፖሊሱን ፡ ምርመራ ፡ አጥንቶ ፡ ምርመራው ፡ ይጣራ ፡ ወይም፡ በተመረመረው ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ይቅረብ ፡ ለማለት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠው ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ ተግባሩን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚቆይበት ፡ ሁኔታ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ መወሰን ፡ ስላለበት ፡ የቁጥር ፡ ፺፱ን ፡ ድንጋጌ ፡ በሰፊው ፡ መተርጎም፡ ያስፈልጋል ። አለበለዚያ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፵፰ ፡ እና ፡ ፩፻፱ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠውን ፡ ተግባርና ፡ ሥልጣን ፡ ዋጋ ፡ ማሳጣት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ የፈጸመ ፡ ቢሆን ፡ የፖሊሱ ፡ ምርመራ ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መጠናት ፡ ስላለበት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚቆይበት ፡ ሁኔታ ፡ በቁጥር ፡ ፺፱ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መወሰን ፡ ስላለበት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፰፬/፰ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሽረን ፡ የቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ድንጋጌ ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራውን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ብለን ፡ ወስነናል ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 2

Justices:

Afenegus Teshome Haile Mariam
Ato Tadesse Tekle Giorghis
Kegnazmatch Mulat Beyene

PUBLIC PROSECUTOR v. ALEMU URGA, ALEMU BORU and FIRE BORU

Criminal Appeal No. 1136/60

Criminal Procedure—Remand—Crim. Proc. Code Arts. 38, 59, 109.

An appeal from the order of the High Court declaring that the Crim. Proc. Code Art. 59. does not authorize the detention of the accused after the police investigations are completed.

Held: Order reversed.

1. According to Crim. Proc. Code Art. 38, the public prosecutor should frame a charge under Art. 109 and institute proceedings within fifteen days of receipt of the police investigation, or, if necessary, order further investigations.

2. In order for the prosecutor to carry out these duties under Arts. 38 and 109 he must have the right to keep the accused in detention until he decides to prosecute.

The public prosecutor filed this appeal requesting the reversal of the order given by the High Court in File No. 864/60. We have rendered the decision given hereunder after examining the argument presented by the public prosecutor and the decision given by the High Court.

JUDGMENT

Alemu Urga and his friends were arrested on suspicion of homicide and kept in custody. The investigating police officer forwarded his report to the public prosecutor in accordance with Article 37 of the Criminal Procedure Code. Then, in accordance with Article 59 of the Criminal Procedure Code, he asked the High Court to determine the terms of detention of these individuals until a charge was filed against them. The High Court examined the application of the investigating police officer and ruled that Article 59 does not apply to such a case but rather to a case where the police investigation is not completed, as a result of which the investigating police officer may apply for a remand for a sufficient time to enable the investigation to be completed.

The public prosecutor appealed on the ground that the High Court interpreted Article 59 of the Criminal Procedure Code very narrowly. We deem it necessary to examine the provisions of the Criminal Procedure Code dealing with the present case to determine whether or not the High Court gave an erroneous interpretation.

The Criminal Procedure Code provides that the commission of an offence must be investigated by the police. The police may, for investigation purposes, detain the

person alleged to have committed the offence either by court order if deemed necessary, or without it if authorized by law. If the accused is detained without a court order, he has to be brought to court within 48 hours, whether the investigation is completed or not. The court to whom the offender has been brought has to decide on the basis of Article 59 whether he should be detained or be released on bail. Moreover, if the investigation is not completed, the investigating police officer could request the court for sufficient time and for an order that in the meantime the accused be detained. In this repect, the additional time awarded by the court shall not be more than 14 days.

The High Court interpreted this provision to mean that the investigating police officer could not ask for the detention of a person arrested for a criminal offence after completing his investigation. The Supreme Imperial Court does not agree with this interpretation for the following reasons:

In principle, any criminal offence is investigated by the police, but the charge is filed in court by the public prosecutor. The investigating police officer must submit his investigation report to the public prosecutor in accordance with Article 37. On receiving the report the public prosecutor may, in accordance with Article 38, prosecute the accused, order further investigation or refuse to institute proceedings.

If the public prosecutor deems the police investigation complete and decides to institute proceedings, he must file a charge within 15 days of the receipt of the police report as provided by Article 109. On the other hand, he could order that a further investigation be made where, unlike the police, he believes that this is in order. If this is so, the public prosecutor has to interpret Article 59 of the Criminal Procedure Code in such a way as to enable him to execute his duty. As stated above, the rights given to and the duty of the police and the public prosecutor are correlative, and the public prosecutor must be allowed to avail himself of the right given the police under Article 59. There are two reasons for this. One, the case is considered to be under investigation until a charge is filed. Two, in the meantime the accused could not be detained without a court order. If Article 59 is interpreted broadly in this manner, the purpose of Articles 38 and 109 would be deflated.

The investigation conducted by the police has to be studied by the public prosecutor, and the detention of the accused must be decided upon by the court as provided by Article 59. For the above reasons, we reverse the High Court's order given in File No. 864/60 and hold that Article 59 is applicable even after the completion of the police investigation.

June 17, 1968

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ አራተኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

ብላታ ፡ ማትያስ ፡ ሕለተወርቅ ፡ ም/ አፈንጉሥ ፤

አቶ ፡ ከበደ ፡ ገሠሠ ፤

አቶ ፡ ክፍሌ ፡ ጀማነህ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፤

መልስ ፡ ሰጭ ፡ አቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱሰመድ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፯/፺፱

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፯/፺፱ ስለ ፡ ውሎች ፡— ዋስትና — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ ፩ሺ፱፻፳፫ ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ ለዋናው ፡ ዋስ ፡ መያዣ ፡ ስለሰጠ ፡ እና ፡ ይህም ፡ አድራጐት ፡ የጠለፋ ፡ ዋስን ፡ ግዴታ ፡ ስለሚያብስበት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፱፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ የጠለፋ ፡ ዋሱ ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ፡ ሲል ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ስለወሰነ ፡ ይህንን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፡— ፍርዱ ፡ ተሽሯል ።

፩/ የመያዣው ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ የጠለፋ ፡ ዋስትናው ፡ ውል ፡ በተደረገበት ፡ ዕለት ፡ (ቀን) ነበር ።

፪/ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ለዋናው ፡ ዋስ ፡ ተጨማሪ ፡ መያዣ ፡ መስጠት ፡ የጠለፋ ፡ ዋሱን ፡ ግዴታ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አያብስበትም ፡ ወይም ፡ የዕዳውን ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ አያራዝምም ። እንዲያውም ፡ አድራጐቱ፡ ለጠለፋ ፡ ዋሱ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ የጠለፋ ፡ ዋሱ ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ አይሆንም ።

መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ የሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ ክርክር ፡ ሰምተን ፡ የሚከተለውን ፡ ፍርድ ፡ ሰጥተናል ።

ፍርድ ።

ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ የስር ፡ ከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አሌክዛንደር ፡ ፓፓዘአኮስ ፡ ፯ ፡ ሺ፡ ብር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ፡ ሲበደር፡ ሁለተኛው ፡ ተከሳሽ ፡ አቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱሰመድ ፡ ለዚሁ ፡ ብድር ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ ዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ ለከሳሽ ፡ ደምበኛ ፡ በመሆኑ ፡ ፯ሺ ፡ ብር ፡ ለባንክ ፡ኃላፊ ፡ ሆኖ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ ከባንክ ፡ አውጥቶ ፡ ለ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ አስተላልፎ ፡ ስለነበር ፡ ፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ለብድሩ ፡ ገንዘብ ፡ ዋና ፡ አላፊ ፡ የነበረው ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ባበዳሪው ፡ ባንክ ፡ ተጠይቆ ፡ ፯ሺ ፡ ብር ፡ የከፈለ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ ከነወለዱ ፡ የጠበቃ፡ አበል ፡ ጨምረህ ፡ ትከፍለኛለህ ፡ ሲል ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፬/፺፰ ፡ ክስ ፡ አቅርቧል ።

፩ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በጠበቃቸው ፡ በአቶ ፡ በረሄ ፡ ነቢያት ፡ አማካይነት ፡ በጊዜያዊ፡ መልስ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አጻጻፍ ፡ በመቃወም ፡ ሲከራከሩ ፡ ቆይተው ፡ በኋላ ፡ ሙሉ ፡ መከላከያ ፡ ለማቅረብ ፡ ደንበኛዬን ፡ ልፈልግ ፡ ብለው ፡ በተሰጣቸው ፡ ቀጠሮ ፡ ሳገ ኘው ፡ አልቻልኩም ፡ ከነገሩ ፡ ወጥቻለሁ ፡ ብለው ፡ ተሰናብተዋል ።

፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በነገረፈጃቸው ፡ አማካይነት ፡ በዋስትና ፡ መፈረማቸውን ፡ አም ነው ፡ ከሳሽና ፡ ፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻቸውን ፡ በመስማማት ፡ ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ግምት፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ ለመቀበልና ፡ ለመረከብ ፡ አዲስ ፡ ውል ፡ አድርገዋል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ፡ እኔን ፡ አልጠሩኝም ፡ በማለት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፯—፳፰ ፡ መሠረት ፡ ተሰርዟል ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ ተችተው ፡ሁለቱ፡ ዳኞች ፡ የሁለተኛ ፡ ተከሳሽን ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ክርክር ፡ በመቀበል ፡ ፪ኛውን ፡ ተከሳሽ ፡ ከገቡበት ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ አድርገው ፡ አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ በሌሉበት ፡ ፈር ደውባቸዋል ። ፩ኛው ፡ ዳኛ ፡ ምክንያቱን ፡ ገልጸው ፡ ፪ኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ለገቡት ፡ ግዴታ ፡ ኃላፊ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ፈርደውባቸዋል ።

የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ከፍተ ኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ቅሬታቸ ውን ፡ ገልጸው ፡ ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተጻፈ ፡ ማመልከቻ ፡ አሰናድ ተው ፡ ይህን ፡ ይግባኝ ፡ አቅርበዋል ።

የይግባኙም ፡ ፍሬ ፡ ቃል ፦

ይህን ፡ ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ግምት ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር፡ ይዞ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ባንክ ፡ አቶ ፡ አሌክዛንደር ፡ ፓፓዘአኰስ ፡ ለሚበደረው ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ዋስ ፡ እንዲሆነው ፡ ስለተጠየቀ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ፡ ካርታ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ስለተነገረው ፡ አቶ ፡ አብዱልሶመድ ፡ በተጨማሪ ፡ አላፊ ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ ለመሆናቸው ፡ በፈርማ ቸው ፡ ካረጋገጡ ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ በራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ዋስትና ፡ የተጠየቀ ውን ፡ ፶ሺ ብር ፡ ወስዶ ፡ በገባው ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ባንኩ ፡ ለማኅ በሩ ፡ ብርቱ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ስለጻፈ ፡ ማኅበሩም ፡ ለጠለፋው ፡ ዋስ ፡ ለአቶ ፡ አብዱል ሶመድ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ማኅበር ፡ ቀሪው ፡ ሒሳብ ፡ በ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እንዲከ ፈል ፡ ጽፎ ፡ ለነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ባለመከፈሉና ፡ መልስም ፡ ባለመጻፉ ፡ አበዳሪው ፡ ባንክ ፡ ከራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በመቀነስ ፡ ከነወለዱ ያበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ወስዷል ።

አቶ ፡ አብዱልሶመድ ፡ አዲስ ፡ ውል ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ከተበዳ ሪው ፡ ከአሌክዛንደር ፡ ፓፓዘአኰስ ፡ ጋር ፡ ስላደረገ ፡ ከዋስትናዬ ፡ ግዴታ ፡ ውጭ ፡ ነኝ፡ በማለት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጠቅሰው ፡ ለሚከራከሩት ፡ ፈጽሞ ፡ አዲስ ፡ ውል ፡ የለም ፤ ያንኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከአብዱል ሶመድ ፡ ዋስትና ፡ ጋር ፡ በተጨማሪ ፡ በመያዣ ፡ የተቆጠረ ፡ ንብረት ፡ ነው ። ለዚሁም፡ ይህ ፡ ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ከአቶ ፡ አብዱልሶመድ ፡ ዋስትና ፡ ጋር ፡ የተያዘ ፡ ለመሆኑ ፡ አቶ ፡ አብ ዱልሶመድ ፡ በፈረሙት ፡ ዋስትና ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ እማኞች ፡ ሊያረጋግጡ ፡ ይችላሉ ፡ በማለት ፡ ነው ። የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ጠበቃና ፡ ፈጅ ፡ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ጋረዴ ፡ ደንበኛዬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ በተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ለ፶ሺ ፡ ብር ፡ ዋስ ፡ ሆነው ፡ መፈረማቸው ፡ የታመነ ፡ ነው ፤ አልተካደም ። ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ዋስ ትና ፡ ከባንክ ፡ ለተበደሩት ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ የ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ግምት ፡ ያለውን ፡ ንብረታቸ

ውን ፡ ላሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ስለዋስትናቸው ፡ መያዣ ፡ በመስጠት ፡ የደንበኛዬን ፡ የጠለፋ ፡ ዋስትና ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በቃል ፡ ንግግር ፡ ተግባብተውና ፡ ተስማምተው ፡ በጽሑፍ ፡ ተፈራርመው ፡ አስወርደውላቸዋልና ፡ በአቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱልሰመድ ፡ ዋስትና ፡ ላይ ፡ የፈረሙት ፡ እማኞች ፡ ይመስክሩ ፡ ሲሉ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ የጠየቁት ፡ አላግባብ ፡ ስለሆነ ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አይቀበላቸውም ፡ በማለት ፡ ስላቀረቡት ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁኔታ ፡ በዚሁ፡ መስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተጻፈ ፡ የይግባኝ ፡ መልሳቸው ፡ ዘርዝረው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደው ፡ ትክክለኛ ፡ ስለሆነ ፡ ይጽናልኝ ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ክርክራችንን ፡ አበቃን ፡ ፍርድ ፡ ይሰጠን ፡ ብለው ፡ ስለጠየቁ ፡ መዝገቡን ፡ ስንመረምር ፡ ያልቀረቡ ፡ ማስረጃዎች ፡ ስላገኘንና ፡ በቃልም ፡ የማጣሪያ ፡ ጥያቄ ፡ ስላስፈለገ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተን ፡ ማስረጃዎቹም ፡ ቀርበውልን ፡ የማጣሪያ ፡ ጥያቄም ፡ ታኅሣሥ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ. ም. በዋለው ፡ ችሎት ፡ አቅርበን ፡ ከባንክ ፡ ጋር፡ዋናውን ፡ የ፺ሺ ፡ ብር ፡ ብድር ፡ ውል፡የተፈራረመው፡ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የኢንሹራንስ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶአል ። የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ጠበቃና ፡ ፈጅም ፡ ደንበኛዬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ከፈረሙት ፡ የዋስትና፡ ግዴታ ፡ ሰነድ ፡ በተቀር ፡ ሌላ ፡ የላቸውም ፡ ብለዋል ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ መያዣ ፡ በዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ ሙሴ ፡ ፓፓዘአኰስ፡ ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ የተፈራረሙት ፡ አብዱልሰመድ ፡ ለ፺ሺ ፡ ብር ፡ ለዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ ዋስትና ፡ ግዴታ ፡ የገቡትን ፡ ሊያስቀርላቸው ፡ ይችላል፡ አይችልምን ፡ አስቀድሞ ፡ መረዳት ፡ ይኖርብናል ።

ለዚሁም ፡ ስለቀረቡት ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁኔታ ፡ እንገልጻለን ። ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ይህን ፡ የ፩፻፹ሺ ፡ ብር፡ግምት ፡ ንብረት ፡ አስቀድሞ ፡ ለዚሁ ፡ ለ፺ሺ ፡ ብር ፡ ብድር ፡ ገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ሆኖ ፡ በተጨማሪ ፡ የጠለፋ ፡ ዋስ ፡ በማስፈለጉ ፡ አቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱልሰመድ ፡ በጠለፋ ፡ ዋስትና ፡ ግዴታ ፡ ገብተው ፡ ለመፈራረማቸው ፡ በዚሁ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፫/፶፯ ዓ ፡ ም ፡ በተፈረመው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ እማኞች ፡ ዋስትናው ፡ ሰነድ ፡ ላይም ፡ እማኝ ፡ ሆነው ፡ የፈረሙ ፡ እነሱው ፡ ስለሆኑ ፡ ይመስክሩ ፡ በማለትና ፡ ይህን፡ የመያዣ ፡ ስምምነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመዘገብ ፡ ማድረጋቸው ፡ ውሉ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሆነ ፡ የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ጠበቃ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፯ ፡ እና ፡ ፳፫ን ፡ በመጥቀስ ፡ ዋስትናው ፡ እንዲሰረዝላቸው ፡ ለጠየቁት ፡ ለደንበኛቸው ፡ ዋስትናውን ፡ የሚያብስ ፡ ውል ፡ አልተዋዋልንም ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፤ የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ጠበቃና ፡ ፈጅ ፡ ደግሞ ፡ የ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ግምት ፡ ንብረት ፡ የመያዣ ፡ ውል ፡ ከዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ ጋር ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሲያደርጉ ፡ አቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱልሰመድን ፡ ሳይይዝ ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ ፡ የተፈራረሙበት ፡ ደንበኛዬን ፡ በጠቀስኩት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነጻ ፡ ስላደረገው ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ምስክሮችም ፡ ቢሆኑ፡ ሊመሰክሩ ፡ አይገባቸውም ፡ በማለት ፡ በጽሑፍም ፡ በቃልም ፡ ተቃውመው ፡ ተሟግተዋል ።

ዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ አሌክዛንደር ፡ ፓፓዘአኰስ ፡ ይህንና ፡ ፺ሺ ፡ ብር ፡ ብድር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ ለማግኘት ፡ የዋስትና ፡ ቦንድ ፡ ግዴታ ፡ መግባት ፡ ውል ፡ ይስጡልኝ ፡ ብሎ ፡ ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሲጽፍ ፡ በበኩሌ ፡ የምገልጽልዎ ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዘርዝሮ ፡ የ፩፻፹ሺ ፡ ብር ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ገልጾዋል ።

ቀጥሎም ፡ ኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ ፓፓዘአኰስ፡ ከኢንሹራንስ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ የተበደርኩትን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍዬ ፡ እጨረስኩ ፡

ድረስ ፡ ሳልሸጥ ፡ ሳልለውጥ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ያስያዝኩ ፡ መሆኔን ፡ በተለ መደው ፡ ፊርማዬ ፡ አረጋግጣለሁ ፡ በማለት ፡ የተፈረመ ፡ ሰነድ ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ተከሳሽ ፡ የነበሩት ፡ ያሁን ፡ በይግባኝ ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ የገቡት ፡ የዋስትና፡ ግዴታ ፡ የተጻፈው ፡ በዚሁ ፡ ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሆኑ ፡ የተረጋ ገጠ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በሁለቱም ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ እማኝ ፡ ሆነው ፡ የፈረሙት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ አልተለወጡም ፡ እነኛው ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ።

የመያዣው ፡ ውል ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ የተባለውም ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ሰነድ ፡ ሳይሆን ፡ ያው ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረው ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ጠበቃ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ ፱፻፳፰ን ፡ በመጥቀስ ፡ ዋናው ፡ ተበዳሪና ፡ የራስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበር ፡ ለብቻቸው ፡ ውል ፡ ካደረጉ ፡ ዋስ ፡ የነበሩት ፡ ደንበኛዬ ፡ ነጻ ፡ ናቸው ፡ ለሚሉት ፡ በጠቀሷቸው ፡ ሕጎች ፡ አንዳች ፡ የሚደግፉዋቸው ፡ ምክንያቶች ፡ አይገኙም ።

ይህንም ፡ ያልንበት ፡ በይግባኝ ፡ ባይና ፡ በዋናው ፡ ተበዳሪ ፡ መካከል ፡ የተፈረ ሙት ፡ ሰነዶች ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ የተፈረሙ ፡ ሰነዶች ፡ ሆነው ፡ ካለመገኘታቸውም ፡ በላይ ፡ ዋሱን ፡ የሚጐዳ ፡ ወይም ፡ በዋሱ ፡ ላይ፡ ግዴታ ፡ የሚያብስ ፡ ወይም ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜን ፡ የሚያረዝም ፡ ሳይሆን ፡ እንዲያውም፡ ዋሱን ፡ የሚረዳ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዋናው ፡ ተበዳሪና ፡ በራስ ፡ አሹራንስ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ አዲስ ፡ ስምምነት ፡ እንደተደረገ ፡ ቆጥሮ ፡ እነኝህም ፡ ውሎች ፡ ዋሱን ፡ ጐድተውታል ፡ በማለት ፡ በተጠቀሱት ፡ ሕጎች ፡ ዋሱ ፡ እንዳልተ ደገፈ ፡ አድርጎ ፡ በመተቸት ፡ ግንቦት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ሽረን ፡ አነስተኛውን ፡ ድምፅ ፡ በመደገፍ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ አቶ ፡ አብደላ ፡ አብዱልሶመድ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኢንሹ ራንስ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ በገቡት ፡ ዋስትና ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ኃላፊ ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጠቅ ላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሁለቱም ፡ ወገኖችና ፡ ፈጆች ፡ ባሉበት ፡ ተሰ ጥቶ ፡ ተነቦ ፡ ተሰምቷል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የፍርዱ ፡ ግልባጭ ፡ ይላክለት ፡ ብለናል ።

የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ በዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰባቸውን ፡ ኪሣራ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፳፫-፬፻፳፬ ፡ እንደተደነገገው ፡ ዘርዝ ረው ፡ ያቅርቡና ፡ ለመልስ ፡ ሰጪም ፡ ይድረስና ፡ መልሱን ፡ ይዘው ፡ ይቅረቡ ፡ ብለናል ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Addis Ababa, Div. No. 4

Justices:

Blatta Matias Helete Work

Ato Tebebe Gessesse

Ato Kifle Gemaneh

RAS INSURANCE S. C. v. ABDUL SEMED

Civil Appeal No. 1486/59

Contracts—Suretyship—Civil Code Arts. 1927, 1928.

An appeal from the decision of the High Court releasing the counter-guarantor where the debtor had given security to the principal guarantor thereby allegedly increasing the liability of the counter guarantor.

Held: Decision reversed.

1. The contract pledging the security was made concurrently with the contract of guarantee.

2. Giving a security to the principal guarantor does not in any way increase the liability of the counter-guarantor, nor does it postpone the debt's due date.

Giving a security to the principal guarantor is actually advantageous to the conterguarantor, and does not release him from any obligations.

After examining the documents we have rendered the following judgment:

JUDGMENT

This is an appeal from the judgment of the High Court releasing the counter-guarantor of the principal debtor for a sum of E $50,000 lent to him by the Commercial Bank of Ethiopia under the guarantee of Ras Insurance Co., the appellant, on the ground that the principal debtor and the creditor (the appellant) have entered into a new contract which increased the liability of the counter-guarantor. The respondent, citing Articles 1927-28 of the Civil Code, contended that without his knowledge the creditor and the principal debtor had entered into a new contract of pledge whereby the debtor undertook to deliver property valued at E $180,000 as security for the performance of his obligation. The High Court released the counter-guarantor by a majority decision.

The relevant part of the memorandum of appeal is as follows:

The principal debtor, Mr. Papazakos, wanted to borrow E $50,000 from the Commercial Bank and, as the bank required him to obtain a guarantor, he asked Ras Insurance Co. to be his guarantor. The company agreed to be the guarantor to the extent of E $50,000, and the principal debtor also undertook to deliver property valued at E $ 180,000 as security for the performance of his obligation. In addition he was also required by the company to get a counter-guarantor. He therefore brought forward Ato Abdul Semed to counter-guarantee the performance

of his obligation toward the Ras Insurance Co. The bank then forwarded the loan of E $50,000 to Mr. Papazakos as agreed. When the date of payment arrived, the principal debtor failed to perform his obligation and the bank accordingly demanded that Ras Insurance Co. pay the E $ 50,000 with interest. The company, having paid off the loan from its account in the bank, demanded that the counter-guarantor, Ato Abdul Semed, pay it back the E $50,000 plus interest. To the contention of Ato Abdul Semed in the High Court that he was no longer bound because a new contract of pledge had been signed by the principal debtor and the insurance company, the said insurance company answered that it was not a new contract but the same contract of pledge signed on the same date as the contract of counter-guarantee and witnessed by the same witnesses. The company offered to introduce witnesses to this effect.

Counsel for the respondent argued that, since the contract of counter-guarantee released his client from his obligations, witnesses should not be introduced.

It has been proved that the contract of counter-guarantee was concluded on the same date as the contract of pledge, i.e., on January 6, 1966, and the same three witnesses attested both contracts.

It is also known that the contract of pledge submitted to the court was the same instrument signed on January 6, 1966. We do not find any reason why we should sustain the contention of counsel for the respondent since the contract of pledge does not in any way increase the liabilities of the counter-guarantor and does not allow time for payment to the debtor. In fact it works to the advantage of Ato Abdul Semed.

We have therefore reversed the majority opinion of the High Court and hold that the respondent, Ato Abdul Semed, is bound by the contract of counter-guarantee.

January 1, 1967

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አዲስ ፡ አበባ ፤ አንደኛ ፡ ችሎት ።

ዳኞች ፤

አቶ ፡ የሸዋወርቅ ፡ ኃይሉ ፤

አቶ ፡ ጕይቶም ፡ በይን ፤

ሻለቃ ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ።

ከሳሽ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፤ ተከሳሽ ፡ የሺጌታ ፡ አረጋ ።*

የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፶፱/፷ ፡

የወንጀል ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፶፱/፷ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፦ በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ ላይ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፦ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ (ለ) ።

ተከሳሽ ፡ የፖሊስ ፡ ሥራውን ፡ ሲያከናውን ፡ እጁ ፡ የገባውን ፡ የግል ፡ አቤት ፡ ባዩን ፡ ሽጉጥ ፡ ለራሱ ፡የማይገባውን ፡ የቅርስ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በማሰብ ፡ ሰውሯል ፡ በመባል ፡ በቁጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ (ለ) መሠረት ፡ ተከሰሰ።

<u>ውሳኔ</u> ፦ ተከሳሽ ፡ ተፈርዶበታል ።

፩/ ተከሳሽ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ (ለ) የተደነገገውን ፡ ተላልፏል ፡ የሚባለው ፦

ሀ/ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤

ለ/ ለራሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌላው ፡ የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገኘት ፡ አስቦ ፡ ተግባሩን ፡ የፈጸመ ፡ ሲሆን ፤

ሐ/ የተሠወረው ፡ ዕቃ ፡ እንዲጠብቅ ፡ በአደራ ፡ የተረከበው ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ አጋጣሚና ፡ ምክንያት ፡ በእጁ ፡ የገባ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

፪/ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ቢነሳም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፲ ፡ መሠረት ፡ በቁጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆኑበታል ።

፫/ ተከሳሽ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ እንኳን ፡ ከሰው ፡ የወሰደውን ፡ ዕቃ ፡ ይቅርና ፡ ወድቆ ፡ ያገኘውን ፡ ዕቃ ፡ ለባለሥልጣን ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

፬/ ተከሳሽ ፡ ግዴታውን ፡ አፍርሶ ፡ የራሱ ፡ ያልሆነውን ፡ ሽጉጥ ፡ ወስዶ ፡ ለተበደረው ፡ ብድር ፡ በመያዥ ፡ መስጠቱ ፡ የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ በማሰብ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙን ፡ ያስረዳል ።

፭/ ስለፖሊስ ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ. ም. በቁጥር ፡ ፯ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ በቁጥር ፡ ፲፫ ፡ (፪) መሠረት ፡ ማናቸውም ፡ የፖሊስ ፡ አባል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ይቆጠራል ።

፮/ ተከሳሽ ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ የግል ፡ አቤት ፡ ባዩም ፡ ለሽጉጡ ፡ ፈቃድ ፡ ስላልነበረው ፡ ተከሳሽም ፡ ሽጉጡን ፡ ከግል ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ በግድ ፡ (በኃይል) ሲወስድ ፡ የፖሊስነት ፡ ሥራውን ፡ በማከናወን ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ስላመነበት ፡ በኃይል ፡ መጠቀሙ ፡ ሕጋዊ ፡ ነው፡ ቢባልም ፡ ወይም ፡ ባይባልም ፤ ሽጉጡ ፡ እጁ ፡ ሊገባ ፡ የቻለው ፡ በሥራው ፡ አጋጣሚና ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ የሚከተለውን ፡ ፍርድ ፡ ሰጥተናል ።

<u>ፍርድ ።</u>

ተከሳሽ ፡ ወታደር ፡ የሺጌታ ፡ አረጋ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፳፪ (ለ) ፡ የተጻፈውን ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፡ ነሐሴ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሌሊቱ ፡ በግምት ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ቦዳሶ ፡ ተመስገን ፡ የተባለውን ፡ ሽጉጥ ፡ ያለ

* ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፪ኛ ፡ የወንጀል ፡ ችሎት ፡ በወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፴፪/፷ ፡ አጽንቶታል ።

ፈቃድ ፡ ይዘሃል ፡ ብሎ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ብልጽግና ፡ ለራሱ ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡
የሥራውን ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የግል ፡ ተበዳዩን ፡ ሽጉጥ ፡ ወስዷል ፡
ተብሎ ፡ ተከሶ ፡ ቀርቦ ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ከተነበበለት ፡ በኋላ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደ
ለሁም ፡ ብሏል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ተከሳሹ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ለመ
ፈጸሙ ፡ የሚያውቁ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ምስክሮች ፡ ቆጥሮ ፡ አስመስክሯል ።

የቀረቡት ፡ ምስክሮችም ፡ ተከሳሹ ፡ ወንጀል ፡ ተፈጸመ ፡ በተባለበት ፡ ዕለት ፡
ከግል ፡ ተበዳዩና ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ከአንድ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
አብረው ፡ መጠጥ ፡ ሲጠጡ ፡ አምሽተው ፡ ከመጠጥ ፡ ቤቱም ፡ ሲወጡ ፡ ተከሳሹና ፡
የግል ፡ ተበዳዩ ፡ አብረው ፡ መውጣታቸውን ፡ ሲመሰክሩ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ፩ኛው ፡
ምስክር ፡ የሆነው ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ ከተከሳሹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ከመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ ወጥቶ ፡
መንገድ ፡ እንደጀመሩ ፡ ተከሳሹ ፡ ለሽጉጡ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳለው ፡ እንዲያሳየው ፡ የጠየ
ቀው ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ እሱም ፡ እንዲምረው ፡ (እንዳይከሰው) ለምኖት ፡ እምቢ፡
በማለቱ ፡ ቤቱ ፡ አቅራቢያ ፡ ደርሶ ፡ ስለነበረ ፡ ሸሽቶ ፡ ለመግባት ፡ ሲል ፡ ተከሳሹ ፡
ተከታትሎ ፡ ይዞት ፡ ሲታገሉ ፡ ሽጉጡ ፡ መሬት ፡ መውደቁንና ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በመን
ገድ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ ፖሊሶች ፡ መጥተው ፡ እንደያዙትና ፤ ተከሳሹም ፡ ለየት ፡ ብሎ ፡
ሁለቱ ፡ ታግለውበት ፡ ከነበረበት ፡ ሥፍራ ፡ ሽጉጡን ፡ አንስቶ ፡ ለፖሊሶች ፡ እንደአ
ሳየ ፡ መስክሯል ። የደረሰበትንም ፡ ሁኔታ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ቀርቦ ፡ ማመልከቱንና ፡
ዋል ፡ አደር ፡ ብሎም ፡ ተከሳሹ ፡ አማላጅ ፡ ልኮበት ፡ ፫፻ ፡ ብር ፡ (ሦስት ፡ መቶ) ፡ ከፍ
ሎት ፡ ክሱን ፡ ከመቀጠል ፡ ያቋረጠ ፡ መሆኑንና ፡ አንደኛ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ማስረጃ ፡
የሆነው ፡ ሽጉጥም ፡ የራሱ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጦ ፡ አስረድቷል ።

ሶስተኛው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክር ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ (አንደኛው ፡ የዐቃቤ ፡
ሕግ ፡ ምስክር) ፡ መሣሪያዬን ፡ ሊቀሙኝ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሲናገር ፡ ሰምቶት ፡ ደጅ ፡
ወጥቶ ፡ ቢመለከት ፡ የግል ፡ ተበዳዩን ፡ አንድ ፡ የፖሊስ ፡ ዩኒፎርም ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡
ሲታገለውና ፡ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ፖሊሶች ፡ መጥተው ፡ የግል ፡ ተበዳዩን ፡ ይዘው ፡ ሲሄ
ዱ ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ የነበረው ፡ የፖሊስ ፡ ልብስ ፡ የለበሰው ፡ ሰው ፡
ከአንድ ፡ የሲቪል ፡ ልብስ ፡ ከለበሰ ፡ ጋር ፡ ትግል ፡ ተደርጎበት ፡ እነበረበት ፡ ስፍራ ፡
ተመልሰው ፡ በባትሪ ፡ ፈልገው ፡ ሽጉጥ ፡ አንስተው ፡ የወሰዱ ፡ ለመሆናቸው ፡ መስክ
ሯል ። አራተኛው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክር ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የገለ
ጸውን ፡ ሽጉጥ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበውን ፡ ተመልክቶ ፡ ተከሳሹ ፡
ይህንኑ ፡ ሽጉጥ ፡ የራሱ ፡ መሆኑን ፡ ነግሮት ፡ አስይዞ ፡ ፩፻ ፡ ብር ፡ (አንድ ፡ መቶ) ፡
እንዲበደርለት ፡ ጠይቆት ፡ እንደነበርና ፡ እሱም ፡ የተባለውን ፡ ሽጉጥ ፡ አስይዞ ፡
ገንዘብ ፡ የተበደረለት ፡ መሆኑን ፡ መስክሯል ።

ወንጀል ፡ ተፈጸመ ፡ በተባለበትም ፡ ዕለት ፡ ተከሳሹና ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ ወደ ፡
ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ሄደው ፡ ተከሳሹ ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ ሽጉጥ ፡ ተኰሰብኝ ፡ ብሎ ፡ ሲያ
መለክት ፡ የግል ፡ ተበዳዩ ፡ ደግሞ ፡ ተከሳሹ ፡ ከሌላው ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ሽጉ
ጡን ፡ የቀማው ፡ መሆኑን ፡ ያመለከቱ ፡ መሆናቸውንና ፡ ተከሳሹም ፡ ከጣቢያው ፡
ጠፍቶ ፡ ለመሄዱ ፡ ፪ኛው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክር ፡ መስክሯል ። የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡
ማስረጃ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ መከላከያ ፡ እንዳለው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ቢጠ
የቅ ፡ የለኝም ፡ ብሏል ።

በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፪ ፡
"(ሀ) የታወቀ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሹም ፤ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ ለራሱ ፡
ሆነ ፡ ለሌላው ፡ የማይገባውን ፡ የቅርስ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለማስገ
ኘት ፡ በማሰብ ።

(ለ) --- ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ በአደራ ፡ የተረከባቸውን ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ አጋጣሚና ፡ ምክንያት ፡ በእጁ ፡ ሊገቡ ፡ የቻሉትን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ባለዋጋ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የሰወረ ፡ እንደሆነ ፤ እስከ ፡ አስር ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እሥራትና ፡ እስከ ፡ አስር ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ፤" ይላል ።

የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ክስና ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሁም ፡ የተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ከዚህ ፡ በላይ፡ የተገለጹት ፡ ሲሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ መርምሮ ፡ መወሰን ፡ የሚገባው ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲጠብቅ ፡ በአደራ ፡ የተሰጠውን ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ምክንያትና ፡ አጋጣሚ ፡ እጁ ፡ ሊገባ ፡ የቻለውን ፡ ዕቃ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ብልጽግና ፡ ማግኘት ፡ አስቦ ፡ ወስዷልን ? የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ የሕጉን ፡ መንፈስ ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀጣ ፡ የሚችለው ፡ የሚከተሉት ፡ ነጥቦች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

(፩) ተከሳሹ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ፡ሲገኝ ፤

(፪) ተከሳሹ ፡ ወንጀል ፡ የፈጸመው ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የማይገባ፡ የቅርስ ፡ ጥቅም ፡ ለማስገኘት ፡ አስቦ ፡ እንደሆነ ፤

(፫) የተወሰደው ፡ ዕቃ ፡ ለተከሳሹ ፡ በእምነት ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ እጁ ፡ የገባ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

በመጀመሪያው ፡ ነጥብ ፡ የተመለከተውን ፡ አሳብ ፡ ለመመርመር ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፲(፩)ን ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፲(፩) ፡ "የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ኃይል ፡ አባሎች ፡ ሆነው ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ --- ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከተጻፈው ፡ አንዱን ፡ ወንጀል ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ፡" ስለሚል ፡ ተከሳሹ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ ስለሆነ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ቢነሳም ፡ እንኳ ፡ ሕጉ ፡ ይመለከተዋል ።

ሁለተኛ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ ሽጉጥ ፡ ወስዷል ፡ ተብሎ ፡ ሲሆን ፡ በክሱም ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ ጋር ፡ ታግሎ ፡ ሽጉጡን ፡ አስጥሎ ፡ ለመውሰዱ ፡ በ፩ኛው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክር ፡ በአካባቢ ፡ ምስክሮች ፡ ከመረጋገጡም ፡ በላይ ፡ ተወሰደ ፡ የተባለውን ፡ ሽጉጥ ፡ ተከሳሹ ፡ ገንዘብ ፡ ሲበደር ፡ አስይዞት ፡ ስለነበር ፡ ተይዞ ፡ ቀርቧል ። ተከሳሹ ፡ የራሱ ፡ ያልሆነውን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ሽጉጥ ፡ መውሰዱና ፡ ለጉዳዩም ፡ ማሚያ ፡ ይህንኑ ፡ ሽጉጥ ፡ አስይዞ ፡ ገንዘብ ፡ መበደሩ ፡ ወንጀሉን ፡ ሲፈጽም ፡ ለራሱ ፡ የማይገባውን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ ያደረገው ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ። ተከሳሽ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ እንኳንስ ፡ ከሰው ፡ የወሰደውን ፡ ዕቃ ፡ ይቅርና ፡ ወድቆ ፡ ያገኘውንም ፡ ቢሆን ፡ ለባለሥልጣን ፡ ማስረከብ ፡ የሥራ ፡ ግዴታው ፡ ስለሆነ ፡ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ማዋሉ ፡ የቅርስ ፡ (ማቴሪያል) ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙን ፡ የሚያሳይ ፡ ግልጽ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ሦስተኛ ፡ ተከሳሹ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ያዋለው ፡ ዕቃ ፡ እንዲጠብቅ ፡ በአደራ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ እጁ ፡ የገባ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ተከሳሹ ፡ በአደራ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕቃ ፡ ሰወረ ፡ ተብሎ ፡ አልተከሰሰም ። በዚሁ ፡ ሁኔታም ፡ አልተመሰከረም ። ስለ

ዚህ ፡ ሁለተኛውን ፡ ነጥብ ፡ እንመልከት ፡፡ ሽጉጡ ፡ በተከሳሹ ፡ እጅ ፡ ሊገባ ፡ የቻለው ፡ በሥራው ፡ አጋጣሚና ፡ ምክንያት ፡ ነውን ? ተከሳሹ ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ ጋር ፡ አብረው፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ አምሽተው ፡ ሲወጡ ፡ ለያዘው ፡ ሽጉጥ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳለው ፡ የግል ፡ ተበዳዩን ፡ መጠየቁ ፡ ያለፈቃድ ፡ ሽጉጥ ፡ መያዝ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ መሆኑን ፡ በማወቅና ፡ እሱም ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር፡ ሁሉ ፡ የማስከበር ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ በመገመት ፡ እንደሆነ ፡ ከአድራጎቱ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ፡፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ተከሳሹ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ነበርን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችል ፡ ይሆናል ፡፡ ስለፖሊስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፴፰ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ (፪) ፡ "ማናቸውም ፡ ዘበኛ ፡ ሁልጊዜም ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል --- ፡" ይላል ፡፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ የሥራ ፡ ጊዜው ፡ እንደሌላ ፡ ሠራተኛ ፡ የተወሰነ ፡ ስላልሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንደነበረ ፡ ይቆጠራል ፡፡ ተከሳሹ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ከሆነና ፡ የግል ፡ ተበዳዩም ፡ ሽጉጥ ፡ ለመያዝ ፡ ፈቃድ ፡ የሌለው ፡ ከሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ በኃይል ፡ በመጠቀም ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ ሽጉጥ ፡ መውሰዱ ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ ቢባልም ፡ ተከሳሹ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ሲፈጽም ፡ የፖሊስ ፡ ሥራውን ፡ እንደሚያከናውን ፡ እራሱን ፡ በመቁጠር ፡ የፈጸመው ፡ ስለሆነ ፡ ሽጉጡ ፡ እጁ ፡ የገባው ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡፡ ስለዚህ ፡ ተከሳሹ ፡ የሽጉጥ ፡ ፈቃድ ፡ በሚል ፡ ምክንያት ፡ ከግል ፡ ተበዳዩ ፡ እጅ ፡ የወሰደውን ፡ ሽጉጥ ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ አቅርቦ ፡ ሕጋዊ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድበት ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ ሽጉጡን ፡ እቤቱ ፡ ወስዶ ፡ ለችግሩ ፡ መዋያም ፡ ይህንኑ ፡ ሽጉጥ ፡ አስይዞ ፡ ለገንዘብ ፡ መበደሪያ ፡ ማድረጉ ፡ ለራሱ ፡ የቅርስ ፡ (ማቴሪያል) ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ አስቦ ፡ የፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ስለሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፳፱ (ለ) ፡ መሠረት ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ፡፡

ቅጣት ፡፡

ተከሳሹ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ወንጀል ፡ የፈጸመው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ብልጽግናን ፡ ለራሱ፡ ለማግኘትና ፡ የሥራውን ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለመሆኑ ፡ ተረጋግጦ ፡ ተመስክሮበታል ፡፡ ስለዚህ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፯፫ ፡ እና ፡ በአንቀጽ ፡ ፮፻፳፱ (ለ) ፡ የተመለከተውን ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ እጁ ፡ ከተያዘበት ፡ ከኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እስራትና ፡ በ፪ሺ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ እንዲቀጣ ፤ ተከሳሽ ፡ ሁለቱን ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ ባይከፍል፡ ስለገንዘቡ ፡ ለውጥ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተጨምሮ ፡ በጠቅላላው ፡ በሰባት ፡ ዓመት ፡ ጽኑ፡ እስራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ወስነናል ፡፡

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ መጋቢት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሰጠ ፡፡

ተከሳሽ ፡ ይግባኝ ፡ ጠይቋል ፡፡

HIGH COURT

Addis Ababa, Div. No. 1

Judges:

Ato Yeshewa Work Hailu
Ato Goitom Beyen
Major Tadesse Abdi

PUBLIC PROSECUTOR v. YESHIGETA AREGA*

Criminal Case No. 359/60.

Criminal law—Offences committed by police officer in discharge of duties—Penal Code Art. 422(b).

Defendant was charged with retaining possession of the private complainant's pistol, seized in the course of his police duties, with intent to obtain unlawful enrichment thereby.

Held: Defendant convicted.

1. Defendant has violated Pen. Code Art. 422(b) if he as a public servant, commits the act with intent to obtain an unlawful enrichment for himself or another, and the object retained by him came into his possession in the discharge of his official duties.
2. Even if it could be argued that he is not a public servant, Art. 422 applies to him pursuant to Pen. Code Art. 410.
3. As a policeman the defendant had a duty to deliver to the authorities any object seized on duty.
4. Defendant's use of the pistol as a pledge to borrow money showed his intent to obtain unlawful enrichment.
5. Under Art. 13(2) of the Police Proclamation of 1942, policemen are deemed to be on duty at all times.
6. Regardless of the propriety of seizing the pistol by force, the defendant gained possession of the pistol in the discharge of his duties.

JUDGMENT

The defendant, Private Yeshigeta, was charged with the offence under Article 422 of the Penal Code. The charge stated that defendant in order to obtain for himself an undue material advantage misappropriated the pistol of Bedase Temesgen, the private complainant, which came into his hand, while he (the defendant) was executing his duty as a policeman, on August 30, 1967, around 1 a. m.

The defendant pleaded not guilty to the charge. Witnesses for the prosecution were heard.

The witnesses testified that they saw the defendant and the private complainant leaving a bar together on the night of the alleged crime. The private complainant testified to the effect that he left the bar with the defendant on the night in question and shortly afterwards the defendant asked him to show him his permit for the pistol which he (the private complainant) was carrying at the time. He then asked the defendant not to report the matter to the authorities, but the defendant insisted on reporting it. When they came near the private complainant's house, he tried to escape. But the defendant caught him and while they were struggling the pistol fell down. At this point two policemen arrived at the scene and caught the private complainant. The defendant picked the pistol up and showed it to the

* Affirmed, Criminal Appeal No. 1032/60, Supreme Imperial Court, Div. No. 2.

policemen. The private complainant reported the incident to the police. After a few days the defendant sent him E $300.00 through mediators, and he dropped the charge against the defendant.

This was the testimony of the private complainant. The third witness testified that he heard the private complainant shouting that some people were trying to take away his pistol. He said he saw the private complainant struggling with a man in a police uniform. According to Witness No. 3, two other policemen then arrived at the scene and went away with the private complainant. The person who was struggling with the complainant returned to the place of the fight with a light and, after searching for some time, picked up a pistol from the ground. Witness No. 4 identified the pistol which was produced as an exhibit by the prosecution, as the one which the defendant had shown him. He testified that the defendant had asked him to find him a loan of E $100.00 using the pistol as a pledge. He said that the defendant told him that the pistol belonged to him. He testified that he gave the pistol as a pledge and borrowed some money for the defendant. Witness No. 2 testified that on the date of the commission of the alleged crime the defendant and the private complainant had gone to the police station and, when the defendant complained that the private complainant fired a shot at him, the private complainant reported that the defendant together with his friend took his pistol from him. He further testified that the defendant disappeared from the police station. After the case for the prosecution was concluded, the accused was called upon to proffer his defence. But the accused stated that he had no evidence to put forth.

Article 422, the violation of which the defendant is charged with, states:

(a) Any public servant who, with intent to procure for himself or another an undue material advantage:

(b) misappropriates such objects or securities which have been entrusted to him or which come into his hands by virtue of or in the course of his duties, is punishable with rigorous imprisonment not exceeding ten years, and fine not exceeding ten thousand dollars.

We have seen the charge and the law cited as well as the case of the prosecution. The court should now answer the question of whether or not the defendant misappropriated an object which had been entrusted to him or which had come into his hands in the course of his duties, with intent to provide for himself an undue material advantage.

In order to answer this question, one has to examine the requirements of the law.

A man is guilty of the offence under Article 422 only if the following requirements are satisfied:

(1) the defendant must be a public servant;

(2) the defendant must have committed the alleged crime with intent to procure for himself or another an undue material advantage;

(3) the misappropriated object must have come into the hands of the defendant or must have been entrusted to him by virtue of or in the course of his duties.

In examining the first requirement one has to refer to Article 410 (1) of the Penal Code which says, "...members of the armed or police forces are subject to the punitive provisions which follow where, in the discharge of their office, duties or employment, they commit any of the offences under this chapter." Therefore,

since the defendant is a member of the police force, the law applies to him even if an argument could be raised to the effect that the defendant is not a public servant. Second, the charge against the defendant is that he misappropriated the pistol of the private complainant. The testimony of Witness No. 1 and the other prosecution witnesses show that the defendant took the pistol from the private complainant. The pistol was seized by force and was given as a pledge by the defendant for the loan he took. The facts that the defendant took a pistol which did not belong to him and that he gave the pistol as a pledge for the loan show that he committed the offence with intent to procure for himself an undue advantage.

The defendant, as a member of the police force, has the duty to hand over to the authorities every object which he finds, let alone an object which he has seized from another person. The fact that he ignored his duty and that he used the object for his own purposes shows that he has acted with intent to procure for himself an undue material advantage and thereby committed an offence. Thirdly, we must examine the issue of whether or not the object was entrusted to the defendant (a public servant), or came into his hands by virtue of or in the course of his duties.

The defendant is not accused of misappropriating an object which has been entrusted to him; no evidence was produced to this effect. So, let us look at the second requirement. Did the pistol come into the hands of the defendant by virtue of or in the course of his duty? The fact the defendant asked the private complainant to show him his licence to carry the pistol shows us that the defendant knew that carrying a pistol without authorization is illegal and that it was his duty as a member of the police force to enforce the law. At this point a question may be posed as to whether or not the defendant was on duty at that particular time. Article 13 (2) of the Police Proclamation, No. 6 of 1942 states that "every police officer shall be deemed to be on duty at all times...." Therefore, since the defendant is a member of the police force and since he is on duty at all times, he is deemed to be on duty when he committed the offence with which he is charged.

Therefore, since the defendant was on duty at the time of the commission of the crime, and the private complainant had no licence to carry the pistol and since the defendant believed that he was exercising his duty as a policeman when he took the pistol by force from the private complainant, we conclude that the pistol came into his hands in the course of his duty irrespective of the fact that use of force by the defendant to obtain the pistol may or may not be legal.

The defendant failed to hand over to the authorities the pistol he took from the private complainant. Instead he took the pistol home and afterwards gave it to a creditor as a pledge for the money he borrowed. This shows that the defendant committed an offence in that he misappropriated the pistol with intent to procure for himself an undue material advantage. We have, therefore, found him guilty of the offence under Article 422 (b) of the Penal Code.

SENTENCE

It has been proved that the defendant, with intent to procure for himself an undue material advantage, misappropriated an object which came into his hands in the course of his duty. After considering the provisions of Articles 83 and 422 (b), we hereby sentence the defendant to 5 years rigorous imprisonment starting from the day of his arrest, December 7, 1967 and to a pay fine in the sum of E $ 2000. If the defendant fails to pay the fine he shall serve two more years of rigorous imprisonment instead, which brings the total to seven years of rigorous imprisonment.

April 1, 1969.

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ።

ዳኞች ፡

አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ አወቅ ፤

አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፤

አቶ ፡ መሐመድ ፡ ብርሃን ፡ ኑርሁሴን ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አርቢስ ፡ የንግድና ፡ ቴክኒክ ፡ ክፍል ፡ ማኀበር ፡

መልስ ፡ ሰጭ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፰/፶፱ ፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፰/፶፱ ፡ ስለ ፡ ታክስ ፡— በሽያጭ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ የሚከፈል ፡ ታክስ ፡—የሻጩ ፡ ግዴታ ፡— ከታክስ ፡ ነፃ ፡ ስለመሆን ፡ (ታክስ ፡ የማይከፈልበት ፡ ጊዜ) ፡— በጠቅላላው ፡ ወይም ፡ በጅምላ ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ፡ (የጅምላ ፡ ሽያጭ) ፡— የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ ይግባኝ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ታክስ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ ስለመኖሩ ፡— ለግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ የማለት ፡ መብት ፡ ታክስ ፡ ሳይከፈልም ፡ ስለመኖሩ ፡— የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ ታክስ ፡ ከፋዩ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ስለመሆኑ ፡— የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷ ፡ እና ፡ (የታረመው) ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ የ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፫ ፤ አንቀጽ ፡ ፳፩ ።

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሸጣቸው ፡ የመኪናዎች ፡ ሽያጭ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ ሲል ፡ የወሰነውን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

<u>ውሳኔ</u> ፡— ፍርዱ ፡ ጸንቷል ።

፩/ ታርሞ ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ ሻጭ ፡ በሽያጭ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ታክስ ፡ እንዲከፍል ፡ ይደነግጋል ። ገዢው ፡ ከታክስ ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ቢሆንም ፡ ሻጭ ፡ ታክሱን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

፪/ አንድ ፡ ሽያጭ ፡ እንደ ፡ ጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከታክስ ፡ ነፃ ፡ የሚሆነው ፡ ታርሞ ፡ በወጣው ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ (ሀ) የተደነገጉት ፡ ሁለት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ። እነኚህም ፡— አንደኛ ፡ ዕቃዎቹ ፡ የተሸጡት ፡ በጠቅላላው ፡ ወይም ፡ በጅምላ ፡ ሲሆንና ፡ ሁለተኛ ፡ ገዢው ፡ ነጋዴ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

፫/ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ መሠረት ፡ (ማለት ፡— በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ሳንመለከት ፡ ስንተረጉመው) ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ቢኖርም ፤ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልታገደ ፡ በስተቀር ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ታክስ ፡ የመሰብሰብ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

፬/ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ ታክስ ፡ ባይከፈልም ፡ ውሳኔውን ፡ በመቃወም ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ።

፭/ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ ለግብር ፡ ከፋዩ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

፮/ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷ ፡ በአንቀጽ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ "ሰዎች" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ትርጓሜ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ አይጨምርም ፡ ሆኖም ፡ የዚህ ፡ ቃል ፡ ትርጉም ለአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ አግባብ ፡ የለውም ።

<u>ፍርድ ።</u>

የክርክሩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ ለግ ቢ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለኤምባሲዎች ፡ ለፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ለብሔራዊ ፡ ጦርና ፡ ለሌሎችም ፡

መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ አድርጎ ፡ በሸጣቸው ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ በሽያጩ ፡ ጠቅላላ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ እንዲከፍል ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባዔ ፡ ውሳኔ ፡ ስለሰጠበት ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ አድርጌ ፡ እንድሸጥ ፡ ከተፈቀደልኝ ፡ የተርን ፡ ኦቨር፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የማይገባ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ይህንኑ ፡ ቀረጥ ፡ እንድከፍል ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የሕግ ፡ ስህተት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ። የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ ላቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ የሚከተለውን ፡ ሕጋዊ ፡ ክርክር ፡ አቅርቧል ።

አንደኛ ፡ መኪና ፡ የሸጥሁላቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ከቀረጥ ፡ ሁሉ ፡ እና ፡ ከሽያጭ ፡ ገቢ ፡ ቀረጥም ፡ ነጻ ፡ የሆኑበትን ፡ የጠቅላላውን ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የቀረጥ ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከቁጥር ፡ አላስገባቸውም ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፤

ሁለተኛ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔውን ፡ የመሠረተበትን ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፰/፲፱፻፶፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ የሚጠቅሰው ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ የተፈቀደውን ፡ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ መሆንን ፡ ቢሆንም ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ በተባለው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፰ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በሚገቡት ፡ ዕቃዎች ፡ የጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ ስለመሆን ፡ ያሉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከቁጥር ፡ ሳያስገባ ፡ ቀርቷል ። መኪናዎች ፡ በደርዘን ፡ ወይም ፡ በችርቻሮ ፡ ስለማይሸጡ ፡ የመኪና ፡ ሽያጭ፡ እንደጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ መቆጠር ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ነው ።

የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ጠበቃ ፡ በበኩሉ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላቀረበው ፡ ክርክር ፡ የሚከተለውን ፡ መልስ ፡ ሰጥቷል ። አንደኛ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፰/፲፱፻፶፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ ማናቸውም ፡ ነጋዴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ በሚሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ በሽያጭ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ የሚከፈለውን ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ ሲል ፡ ስለደነገገው ፡ እና ፡ የዚሁ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፲፮ ፡ (ሀ) ፡ ታክሱም ፡ የሚመደበውና ፡ የሚወሰነው ፡ ነጋዴው ፡ ዕቃ ፡ በመሸጥ ፡ ካገኘው ፡ ወይም ፡ ሊያገኝ ፡ ከሚገባው ፡ ጠቅላላ ፡ ገቢ ፡ እየታሰበ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፤ በተጨማሪም ፡ ገዥዎች ፡ መንግሥት ፡ ወይም፡ ኤምባሲዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ነጋዴው ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግብር ፡ ነጻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ እና ፡ ግብር ፡ ከፋዩም ፡ ሻጩ ፡ ስለሆነ ፤—

ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፰/፲፱፻፶፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ መሠረት ፡ መኪናዎቹን ፡ የሸጥሁት ፡ በጅምላ ፡ ነውና ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ነኝ ፡ ለሚለው ፡ አንድ ፡ መኪና ፡ መሸጥ ፡ ነጠላ ፡ ሽያጭ ፡ እንጂ ፡ ጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ስላይደለ ፡ እና ፡ ጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ የሚባለው ፡ በጠቅላላ ፡ ወይም ፡ በነጠላ ፡ ሊሸጥና ፡ ሊያገለግል ፡ ለሚችል ፡ ዕቃ ፡ ስለሆነ ፤ የመኪና ፡ ሽያጭ ፡ የጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ አይደለም ፤ የአንድ ፡ መኪና ፡ ሽያጭ ፡ የጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ነው ፡ ቢባልም ፡ እንኳን ፡ መኪናዎቹ ፡ የተሸጡት ፡ ለተጠቃሚ ፡ እንጂ ፡ መልሶ ፡ ለሚሸጥ ፡ ነጋዴ ፡ ስላልሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ኩባንያ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲከፍል ፡ የወሰነበት ፡ በትክክል ፡ ስለሆነ ፡ የጉባኤው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲጸናልኝ ፤ እንዲሁም ፡ የጠበቃ ፡ አበልና ፡ ኪሣራ ፡ ጭምር ፡ እንዲከፈለኝ ፡ ሲል ፡ ጠይቋል ።

በተጨማሪ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነበትን ፡ ገንዘብ ፡ ይግባኙ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ሊከፍል ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ ከሣሽነት ፡ ሕጋዊ ፡ ክርክር ፡ አቅርቧል ።

የግራ ፡ ቀኙን ፡ ክርክር ፡ እንደመረመርነው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በይግባኝ ፡ ሊወሰኑ ፡ የሚገባቸው ፡ ጭብጦች ፡ ሁለት ፡ ናቸው ።

አንደኛው ፡ ቀረጥ ፡ ወይም ፡ ማንኛቸውንም ፡ ግብር ፡ የማይከፍሉ ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መኪና ፡ ሲገዙ ፡ ሻጩ ፡ ለእነዚህ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሸጣቸው ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ መሆን ፡ አለመሆኑ ፡ ሲሆን ፤

ሁለተኛው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነበትን ፡ ገንዘብ ፡ ይግባኙ ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ የሌለበት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።—

እንግዲህ ፡ አንደኛውን ፡ ጭብጥ ፡ እንመርምር ፤ በዚህ ፡ ጭብጥ ፡ የቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ኩባንያ ፡ አንደኛ ፡ ክርክር ፡ መኪናዎቹን ፡ የሸጥሁት ፡ ከቀረጥ ፡ ሁሉ ፡ ነጻ ፡ ለሆኑ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለሆነ ፤ ለእነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ በሸጥኋቸው ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ የሚለው ፡ ነው ። የአዋጅ ፡ ቁጥር፡ ፻፷፭/፲፱፻፶፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ "ማናቸውም ፡ በሽያጭ ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ የሚከፈለውን ፡ ታክስ ፡ ማናቸውም ፡ ነጋዴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃ ፡ በሚሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡" ሲል ፡ ይደነግጋል ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ይግባኝ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ይህን ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ ሊከፍል ፡ የማይገደድበትን ፡ ምክንያት ፡ ቢገልጽም ፡ በሐምሌ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጻፈው ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ፪ ፡ (ሀ) ላይ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ድርጅቶች ፡ ከሽያጭ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ነጻ ፡ የሆነበትን ፡ የጠቅላላውን ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከቁጥር ፡ አላገባውም ፡ ብሎ ፡ ከማመልከቱ ፡ በስተቀር ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ በዝርዝር ፡ ለተገለጹት ፡ ድርጅቶች ፡ መኪና ፡ ሲሸጥ ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ መኖሩን ፡ አላስረዳም ። ሁለተኛም ፡ በዚሁ ፡ ማመልከቻ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፪ (ለ) ፡ እና ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ ሲገልጽ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፭ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያቀረበው ፡ ክርክር ፡ የመኪና ፡ ሽያጭ ፡ የጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረትም ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ነው ። የይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ኩባንያ ፡ ክርክርና ፡ በጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ገቢ ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ፡ የሚለውን ፡ የአንቀጽ ፡ ፲፰ትን ፡ ፊደል ፡ (ሀ)ን ፡ አጣምረን ፡ ስንመረምረው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የአንቀጹን ፡ ትክክለኛ ፡ ሃሣብ ፡ የተረዱት ፡ አልመሰለንም ። በአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ ብሎ ፡ ሊከራከር ፡ የሚችል ፡ ነጋዴ ፡-

ሀ/ ዕቃውን ፡ የሸጠው ፡ በጅምላ ፡ ሲሆን ፡ እና ፡-

ለ/ ዕቃውን ፡ የሸጠው ፡ በቀጥታ ፡ ለተጠቃሚ ፡ ክፍል ፡ ሳይሆን ፡ ለሌላ ፡ ነጋዴ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ክርክር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የጅምላ ፡ ሽያጭ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ቢከራከርም ፡ መኪናውን ፡ የሸጡት ፡ ለሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ሳይሆን ፡ ለመንግሥታዊ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለሆነ ፤ አንቀጹ ፡ ተጠቃሽነት ፡ እንዲኖረው ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ አንደኛው ፡ ተሟልቷል ፡ ቢባልም ፡ እንኳን ፡ ሁለተኛው ፡ ስለጐደለ ፡ ይህ ፡ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፭/፲፱፻፶፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ተጠቃሽነት ፡ የለውም ።

የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ነገረፈጅ ፡ በኅዳር ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጻፈው ፡ የመልስ ፡ መልሱ ፡ ላይም ፡ የተርን ፡ ኦቨር ፡ ታክሱን ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ በማለት ፡ ተደግፎ ፡ የተከራከረው ፡ የዚህኑ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ነው ፤ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ "ሰው ፡" ማለት ፡ ማናቸውም ፡ ግዙፋዊ ፡ ሰውና ፡ ሽርክና ፡ ስለሆነ ፤ ሰው ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ መኪና ፡ የሸጥኩላቸውን ፡ ድርጅቶች ፡ አይመለከትም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ እነሱ ፡ የማይከፍሉትን ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ ሲል ፡ ተከራክሯል ።—

በአንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ ውስጥ ፡ የተርን ፡ አቨር ፡ ታክስ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ሻጩ ፡ ነጋዴ ፡ መሆኑ ፡ ስለተደነገገ ፤ የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ነገረፈጅ ፡ እንደሚከራከረው፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ ታክስ ፡ ሰብሳቢ ፡ ሳይሆን ፡ ታክስ ፡ ከፋይ ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ንም ፡ ክርክር ፡ አልተቀበልነውም ።

ስለሁለተኛው ፡ ጭብጥ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፫/፲፱፻፶፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፩ ፡ እንደተ ዘረዘረው ፡ ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ቢቆይም ፡ የግ ብር ፡ አከፋፈል ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚቴ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፡ ግብሩ ፡ ይከፈላል ፡ ስለ ሚል ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ የተወሰነበትን ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ነበረበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኙን ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ የግብር ፡ ይግ ባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለይግ ባኝ ፡ ባዩ ፡ እንዲሰጥ ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢታዘዝ ፡ ትእዛዙን ፡ ባለመፈጸም ፡ የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ጠበቃ ፡ ጉባኤው ፡ የሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ታግዶ ፡ ክርክሩ ፡ እንዲሰማ፡ ይታዘዝልኝ ፡ ብለው ፡ ያመለከቱትን ፡ ተቀብለን ፡ ግንቦት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዋለው ፡ ችሎት ፡ ለቀረበው ፡ ክርክር ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እስክንሰጥ ፡ ድረስ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ታግዶ ፡ እንዲቆይ ፡ ስላዘዝን ፤ የተወሰነበትን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፍል ፡ ይግባኙ ፡ አይታ ይም ፡ በማለት ፡ መወሰን ፡ አላስፈለገም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለወደፊቱ ፡ በአንዳንድ ፡ ምክ ንያት ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ካልታገደ ፡ በተጠቀሰው ፡ አዋጅ ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፩ ፡ መሠረት ፡ የተወሰነበትን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚደነግግ ፡ ማስከፈል ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፋንታ ፡ ቢሆንም ፡ ገንዘቡን ፡ ካልከፈለ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙ ፡ አይሰማም ፡ በማለት ፡ ሕጉ ፡ ስላልደነ ገገ ፡ በይግባኝ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የተወሰነበትን ፡ ገንዘብ ፡ ካልከፈለ ፡ ይግባኙ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ የለበትም ፡ የማለቱን ፡ ክርክር ፡ አልተቀበልነውም ።

አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ በፍርድ ፡ ስለተወሰነ ፡ ማገጃው ፡ ተነስቷል ። ለወደ ፊቱ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ የይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነውን ፡ ግልባጭ ፡ መከልከል ፡ የሌ ለበት ፡ መሆኑን ፡ እናስጠነቅቃለን ። ስለዋናው ፡ ክርክር ፡ ከላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ምክ ንያቶች ፡ ሁሉ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ በኅዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሰጠ ውን ፡ ውሳኔ ፡ አጽድቀን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ በ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፰/፲፱፻፶፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ መሠረት ፡ የተጠየቀውን ፡ የተርን ፡ አቨ ር ፡ ታክስ ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርደናል ።

ኪሳራው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፳፫ ፡ እና ፡ ፬፻፳፬፡ መሠረት ፡ ዝርዝሩ ፡ ሲቀርብልን ፡ የሚወሰን ፡ ነው ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ በንባብ ፡ ተሰጠ ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Commercial Division

Judges:

Ato Nigussie Fitawake

Ato Assefa Liban

Ato Mohammed Berhan Nurhussen

ORBIS COMPANY, INDUSTRIAL & TECHNICAL SECTION v. THE INLAND REVENUE DEPARTMENT.

Civil Case No. 708/59

Taxation—Turnover tax—Tax exemption—Wholesale selling—Obligation to pay tax while appeal is pending in High Court—Right to appeal to High Court from Tax Appeal Comm. before paying tax—Right of taxpayer to be supplied with copy of Tax Appeal Comm. decision—Arts. 3, 16, 18 *of Proc. No.* 205 *of* 1963*; Art.* 61 *of Proc. No.* 173 *of* 1961.

An appeal from the decision of the Tax Appeal Commission holding that the appellant should pay turnover tax on cars sold to government departments.

Held: Decision affirmed.

1 Art. 16 of Proc. No. 205 of 1963 provides for payment of turnover tax by sellers regardless of the fact that the buyer is a government department.

2. According to Art. 18 of the same proclamation, payment of tax is exempted only when the goods are sold wholesale, and the buyer is a trader.

3. Under Art. 61 of Proc. No. 173 of 1961 (construed separately from Proc. No. 205 of 1963) the Inland Revenue Department has the duty to collect taxes despite appeals pending in the High Court, unless a stay is issued by the court.

4. An appeal against the Tax Appeal Comm. decision can be lodged in the High Court even if tax has not been paid.

5. A copy of the Tax Appeal Comm. decision must be given to the taxpayer upon request.

6. The word "persons" in Art. 3 of Proc. 205 of 1963 does not include government departments.

JUDGMENT

This is an appeal from the decision of the Tax Appeal Commission requiring the appellant company to pay turnover tax on the total income received from the sale of cars, sold free of tax, to the Ministry of the Imperial Court, various embassies, the Police Force, the Territorial Army and other departments. The appellant alleges that this decision contains an error of law. It claims that it should not be required to pay turnover tax because it was authorized to sell the cars in question free of tax in the first place. The advocate for the appellant company raised the following legal arguments on appeal:

1. The decision of the Tax Appeal Commission failed to consider provisions of the general law which exempt the department to which the cars were sold from the payment of all kinds of taxes, including turnover tax.

2. Although the Tax Appeal Commission based its decision on the rules which exempt certain sales from the payment of turnover tax (found at Article 16 of Proclamation No. 205 of 1963, according to the terms of Article 18 of thye same Proclamation), it failed to consider the rules which exempt wholesale sales of imported goods from turnover tax.

The advocate argued that cars are not sold in dozens or retailed and therefore the sale of cars should be considered as a wholesale operation.

The advocate for the respondent submitted the following reply to rebut the appellant's arguments.

1. Article 16 of Proclamation No. 205 of 1963 states that turnover tax shall be paid by all traders selling any movable goods in Ethiopia. Article 17 (a) of the same Proclamation provides that turnover tax shall be charged, levied, collected and paid on gross revenues from sales received or due to traders for sale of goods. There is no law which exempts the seller from the payment of turnover tax where the purchaser is a government agency or an embassy; it is the seller that pays the turnover tax.

2. The appellant company alleges that it sold the cars on a wholesale basis according to Article 18 of Proclamation No. 205 of 1963 and therefore is exempt from the payment of turnover tax; but the sale of one car is a retail sale, not a wholesale operation. A wholesale operation refers to things which can be used and sold either on a wholesale or retail basis. Even if it were said that the sale of one car is a wholesale sale, the Tax Appeal Commission was correct in deciding that the appellant company pay the turnover tax, as the cars in question were sold to consumers and not to a retail trader.

The advocate for the respondent prayed the court to affirm the decision of the Commission and to order the appellant company to pay damages and advocate fees.

In addition the respondent raised a cross-objection wherein he contended that the appellant company should pay the tax determined by the Commission before the appellate court decided on the appeal.

After examining the arguments of both parties, we have found that there are two issues to be determined.

The first issue is whether a seller is exempted from the payment of turnover taa when he makes sales to government agencies which are exempt from all taxes.

The second issue is whether or not the appellant company should pay the tax determined by the Commission before the appeal is heard.

Let us consider the first issue. As regards this issue, the appellant company argues that it should be exempted from the payment of turnover tax on the ground that the cars in question were sold to agencies which are exempted from all taxes. Article 16 of Proclamation No. 205 of 1963 states that "turnover tax shall be paid by all traders selling any movable goods in Ethiopia." The appellant company under No. 2 (a) of its memorandum of appeal of July 29, 1967, stated that the Tax Appeal Commission failed to consider the general provisions which exempt agencies from payment of turnover tax, but the appellant failed to cite any law which exempts a seller from paying turnover tax when he sells goods to the aforesaid agencies. The second argument found under No. 2 (a) and 4 of the same

memorandum is that the company should not pay turnover tax because the sale of cars is a wholesale operation as defined in Article 18 of Proclamation No. 205 of 1963.

After considering the appellant's argument and Article 18 (a) of Proclamation No. 205 of 1963 which exempts wholesale sales from the payment of turnover tax, we are of the opinion that the appellant has failed to grasp the thrust of this provision. A trader may claim exemption from the payment of turnover tax under Article 18 (a) when:

(a) he sells goods on a wholesale basis; and

(b) the sale is made to traders and not to consumers.

In the present case, even if we say the sale is a wholesale operation and that one of the requirements of Article 18 (a) is satisfied, the second requirement would not be satisfied, because the cars were sold to government agencies and not to traders. Therefore the appellant cannot avail himself of Article 18 of Proclamation No. 205 of 1963.

In his reply of September 28, the advocate for the appellant company cited Article 3 of the same Proclamation in support of his argument that the company should not pay turnover tax. He argued that the term "person" in Article 3 means a natural person and any associations of persons whether incorporated or not, but does not include the agencies the company sold the cars to. Therefore the company should not pay the tax which the purchasers are not required to pay.

Since, according to Article 16 of the Proclamation, it is the seller who pays turnover tax and since the appellant company is a tax payer and not a tax collector, the court does not accept this argument.

And now for the second issue, Article 61 of Proclamation No. 173 of 1961 states that notwithstanding any appeal taken thereunder the tax payer shall pay the tax in accordance with the decision of the Tax Appeal Commission, and the appellant company should have paid the assessed amount. However, after the appellant brought this appeal to this court, this court ordered the Inland Revenue Department to give the appellant a copy of the decision of the Tax Appeal Commission, but the order was not carried out. Consequently, this court, at the request of the advocate for the appellant, ordered that the decision of the Tax Appeal Commission be stayed until the court gave a final decision on the matter. Therefore, in this case it is not necessary to rule that the appeal cannot be heard unless the assessed amount is paid. However, in the future, unless the decision of the Tax Appeal Commission is barred by the court for any reason, it is the duty of the Inland Revenue Department to collect the tax according to Article 61 of Proclamation No. 173 of 1961. But, since the law does not provide that the appeal shall not be heard unless the tax is paid, we do not accept the argument that the court cannot hear the appeal unless the tax is paid in accordance with the decision of the Tax Appeal Commission. But now, as the case has been finally disposed of, the bar is lifted. We warn the Inland Revenue Department not to refuse to give to appellants copies of the decisions of the Tax Appeal Commission in the future. For the above reasons we have decided that the appellant company shall pay the turnover tax assessed by the Tax Appeal Commission on November 15, 1966 in accordance with Article 16 of Proclamation No. 205 of 1963, year 22, No. 18.

The costs shall be determined when we receive the details in accordance with Articles 463 and 464 of the Civil Procedure Code.

January 8, 1968

የምርምር ፡ ጽሑፎች ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብና ፡ ስለ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፡-

ከቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፡*

"ባንዳንዱ ፡ የሰሜኑ ፡ ክፍል ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ 'መሬት ፡ አለህ ?' የሚ ለው ፡ ተራ ፡ የሚመስለው ፡ ጥያቄ ፤ በቀላሉ ፡ እንደስድብ ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ። ጥያ ቄው ፡ የተሠነዘረለትም ፡ ኩሩ ፡ ሰው ፡ ትሁት ፡ ለመሆን ፡ ከመረጠ ፤ ፈገግ ፡ በማለት ፡ 'ድሃም ፡ ብሆን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ እኮ ፡' ሲል ፡ ይመልስ ፡ ይሆናል ። ማንም ፡ ሰው፡ ቢሆን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ---መሬት ፡ ይኖረዋል ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ይህም የማንም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ያለው ፡ መሠረ ታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይህ ፡ ነው ። የመሬት ፡ ባለቤትነትም ፡ የሚፈለገው ፡ ለሚያስከ ትለው ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለባለቤቱና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሊያስገኝለ ትም ፡ ስለሚችለው ፡ ስምና ፡ ክብር ፡ ጭምር ፡ ነው ። መሬት ፡ መያዝም ፡ የመከበር ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የክብርና ፡ የኩራት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ስለዚህም ፤ በመሬት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ባላቸውና ፡ ---በሌላቸው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ አይወሰንም ። መሬት ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ የሰው ፡ የበታች ፡ መሆን ፡ ነው።"[1]

መግቢያ ፤

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ዓላማችን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፣ የሚመለከቱትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፤ ማለት ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱-፩ሺ፬፻፺፫ ፡ ያሉትን ፤ በዝርዝር ፡ ለማብራራት ፡ ሲሆን ፤ ይህንንም ፡ የምናደርገው ፡ ቁጥ ሮቹ ፡ በወጡበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ሁኔታና ፡ አቋም ፡ በመመራት፡ ነው ። እንዲያውም ፡ ሊያስተዳድሩ ፡ የታቀዱትን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ ሁኔታና፡ ሊያስወግዱ ፡ የታሰቡትንም ፡ ችግር ፡ ላላወቀ ፡ የተባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ምንም ፡ ስሜት፡ የሚሰጡ ፡ አይመስልም ።

መግቢያ ፡ ቁጥሩን ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ን[2] ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያነበበ ፡ ሊረዳው ፡ እንደሚችለው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ምዕራፍ ፡ ባህልንና ፤ ልማድን ፡ የሚ

---

* ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩ. ፲፱፻፷፩ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከፍተኛ ፡ የጥናት ፡ ጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ለፕሮፌሰር ፡ ሃሪስን ፡ ዳኒንግ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ።

1. መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ ሳም ፡ አስፔክትስ ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ አውነርሺፕ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (ለኢት ዮጵያ ፡ ጥናቶች ፡ ስብሰባ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በቅድሚያ ፡ የቀረበ ፡ ጽሑፍ ፤ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ- ም-) (ያልታተመ) በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ ገጽ ፡ ፩ ።
2. "ሀብትነታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ (የደሽ) ፡ እንደ ፡ ጕሣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅ ብረት ፡ መሠራታቸው ፡ የኅብረቱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የተከተሉ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚሠሩ ፡ ይሆናሉ ።"

ጠብቅ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ምዕራፉ ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ አዲስ ፡ ሐሳብን ፡ ያዘለ ፡ ሳይሆን ፤ የነበረውን ፡ ባህል ፡ በግልጽ ፡ የሚወስንና ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለተባለው ፡ ባህል ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ የጥንቱ ፡ ረቂቅ[3] ፡ ሊያስተዳድራቸው ፡ አቅዶ ፡ የነበረው ፡ ሁለት ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የተከፈሉት ፡ በሃይማኖትና ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገርም ፡ "የሕዝቡ ፡ የአኗኗር ፡ ዘዴ ፡"[4] በሚሉት ፡ መንታ ፡ መመሪያዎች ፡ ነበር ።

በረቂቁ ፡ እንዲተዳደር ፡ የታቀደው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፤ ማለት ፡ በአክለ ፡ ጉዛይ ፤ በሰራዬና ፡ በሐማሴን ፡ ያለው ፡ ክርስቲያንና ፡ በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘላን ፡ ያልሆነ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፡ ሲሆን ፤ የሚበዛው ፡ መሬትን ፡ እንደ ፡ "ቤተ ፡ ሰብ ፡" ወይም ፡ "መንደር ፡" ንብረት ፡ የሚገምት ፡ ነው ።

በረቂቁ ፡ እንዲተዳደር ፡ የታቀደው ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ በአዳልና ፡ በሱማሌ ፤ እንዲሁም ፡ ቆላ ፡ በሆነው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ ውስጥ ፡ ተበታትኖ ፡ የሚገኘው ፡ ክርስቲያን ፡ ያልሆነው ፡ ዘላኑ ፡ ሕዝብ ፡ ነበር ።[5] ይህ ፡ ሕዝብ ፡ መሬትን ፡ እንደ ፡ "ጎሣ ፡" ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ክፍሎች ፡ ባንዱ ፡ በሚመደበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ እንኳ፡ በየቀበሌው ፡ በባህልና ፡ ልማድ ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ አርቃቂው ፡ ቢያውቁም ፤ ሁለቱን ፡ ዓይነት ፡ ሕዝብ ፡ የሚያስተሳስር ፡ በቂ ፡ ተመሳሳይ ፡ ልማድ ፡ መኖሩን ፡ በማመን ፡ ዘላኑንና ፡ በእርሻ ፡ የሚኖረውን ፡ ሕዝብ ፡ በአንድ ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ በሆነ፡ ምዕራፍ ፡ ስር ፡ ሊያስተዳድሯቸው ፡ ወስነው ፡ ነበር ።[6]

"አግሪካልቸራል ፡ ኮሚውኒቲስ ፡" (በፈረንሣይኛው ፡ "ሌ ፡ ኮሙናውቴ ፡ አግሬር ፡") የሚለው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ በተለመደ ፡ ትርጉሙ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፤ ዘላን ፡ ያልሆነን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያመለክት ፡ ቢሆንም ፤ የምንመረምረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በእንግሊዝኛው ፡ "አግሪካልቸራል ፡ ኮሚውኒቲስ ፡" ሲል ፡ ከላይ ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ሁለቱንም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ በማጠቃለል ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ተርጉመን ፡ የምንጠቀምበት ፡ በዚሁ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ከታቀዱት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ

3. አር ፡ ዳቪድ ፤ ደ ፡ ሌክስፕሎይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡ ዲዚመብል ፤ ቻርትር ፡ ፕረምየር ፤ ዱ ፡ ኮሙናውቴ ፡ አግሬር ፤ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፩ ፤ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ።

4. አር ፡ ዳቪድ ፤ ኤክስፖዜ ፡ ዴ ፡ ሞቲፍ ፡ ኤ ፡ ከማንቴር ፡ ዱ ፡ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፱ ፡ ኤ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፩ ፡ ሬለቲፍ ፡ ደሜን ፡ ፑብሉክ ፤ አ ፡ ሌ ፡ ክስፕሮፕሪያሲዮን ፡ ኤታ ፡ አሌክስፕሎይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡ ዴ ፡ ቢያን ፤ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፷፫ ፤ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ ፤ ገጽ ፡ ፪) ፡

5. ለክቡር ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንትና፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባል ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተደረገ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ።

6. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።

የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደ ፡ መመሪያ ፡ የተጠቀሙባቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ሁኔታ[7] ፡ በዝርዝር፡ እንመረምራለን ። በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች፥ ፡ የሚገኙ ፡ ሕዝቦችን ፡ ባህል ፡ በዝርዝር ፡ ለመመርመር ፡ የተገደድነውም ፤ ረቂቅ ፡ አውጪው ፡ ለሚያዘጋጁት ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ ያደረጉት ፡ የእነዚህን ፡ ባህል ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎችን ፡ ስለነበር ፡ ነው[8] ። ስለነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ ባህል ፡ የሚገልጹ ፡ ጽሑፎች ፡ እጅግ፡ ጥቂት ፡ ቢሆኑም ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የልማዳዊ ፡ ሕጎቻቸውን ፡ ግልባጮች በማግኘቱ ፡ ጥናቱን ፡ የተሟላ ፡ ሊያደርግለት ፡ ችሏል ። የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የሚገኙባቸውን ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ ዓይነተኛ ፡ መልክ ፡ አስቀድመን ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፣ ቀጥለን ፡ የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ እንመለከታለን ። የጥንቱ ፡ ረቂቅ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ባይኖረውም ፣ ደራሲው ፡ ረቂቁን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ በመግለጫ፡ መልክ ፡ የጻፉትን ፡ ሐተታ ፡ ያህል ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የወጣውን ፡ ቃል ፡ ለማስረዳት ፡ እጅግ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ለማንኛውም ፡ የሕግ ፡ ረቂቅና ፡ የሕግ ፡ ቃል ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ቢሆንም ፣ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ የጥንቱ ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ ብቻና ፡ የተቆራረጠ ፤ ለመረዳትም ፡ የሚያዳግት ፡ መሆኑን ፡ ስንመለከት ፡ የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ ጠቃሚነት ፡ ይበልጥ ፡ እንገነዘበዋለን ።

የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ትርጉም ፡ የሌላቸው ፣ አስቸጋሪ ፡ መስለው ፡ ከሚታዩት ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱—፩ሺ፭፻፪ ፡ ካሉት ፡ ቃሎች ፡ አብዛኞቹን ፡ አንባቢው ፡ ሊረዳ ፡ ስለሚችል ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፡ የምንሰጥበት ፡ ሕጉን ፡ በመመርመር ፡ ልንጠይቃቸው ፡ ስለምንችል ፡ አንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ነው ፤ ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የሚመስለው ፡ አለመስማማት ፡ አለመኖሩን ፡ ለማሳየት ፡ እንሞክራለን ።

ደራሲው ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ሳለ ፣ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክፍል ፡ ጉድለት ፡ ሳይኖርበት ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ አድሮበት ፡ ነበር ። ሕጉ ፡ በአንዳንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ "በኅብረት ፡ (ማለት ፡ በተራድዖ ፡) የሚታረስ ፡" መሬት ፡ አለ ፤ በሚል ፡ አስተያየት ፡ የተመራ ፡ ስለመሰለው ፣ ሕጉ ፡ እንዲያስተዳድራቸው ፡ ስለታቀዱት ፡ አንዳንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ለመረዳት፡ ባደረገው ፡ ጥናት ፡ ስለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ መረጃ ፡ አጋጥሞታል ። ይህም መረጃ ፡ በቀላሉ ፡ የማይገኝ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጽሑፍም ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ ቦታውን ፡ ይዞ ፡ መገኘት ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ ደራሲው ፡ ጨምሮት ፡ ይገኛል ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ መረጃ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ና ፡ ተከታዮቹ ፡ ሊሻሻሉ ይገባል ፤ ሲል ፡ በጽሑፉ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ደራሲው ፡ ለሚያቀርበው ፡ አስተያየት ፡ እጅግ ፡ የሚጠቅም ፡ ስለሆነ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ።

ከላይ ፡ እንደተናገርነውም ፡ ሁሉ ፣ በአንዳንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ የሚገኘውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ ሁኔታ ፡ ላላወቀ ፡

---

7. ከዚያው ።
8. እነዚህም ፡ ኤፍ ፡ አስቲኒ ፣ ዲሪቶ ፡ ኮንሲዌቱዲናሪዮ ፡ ዴል ፡ ኤሪትሪያ ፡ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.) ፡ እና ፡ ሲ ፡ ሮሲኒ ፣ ዲሪቶ ፡ ኮንሱዌቱዲናሪዮ ፡ ዴል ፡ ኤርትሪያ ፡ (፲፱፻፲፮ ፡ ዓ. ም.) ናቸው ።

ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፶፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ ትርጉም ፡ የማይሰጡ ፡ በመሆናቸው[9] ፤ ይህ ን ፡ ሁኔታ ፡ አስቀድሞ መመልከት ፡ ይገባል ።

ክፍል ፩

የኀብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብ ፡ ዓይነተኛ ፡ ባህል ፤

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የምንመረምረው ፤ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የኀብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ከሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ የዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ሕዝቦች ፤ ማለትም ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ በሰራዬ ፤ በሐማሴንና ፡ በአክለ ፡ ጉዛይ ፡ የሚኖሩ ፤ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ክርስቲያኖችንና ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በስተምሥራቅና ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኙ ፤ ክርስቲያን ፡ ያልሆኑ ፡ ዘላኖችን ፤ ባህል ፡ ዓይነተኛ ፡ መልክ ፡ ነው ። በየመንደሩ ፡ ሊኖር ፡ የሚችለውን ፡ የባህል ፡ መለያየት ፡ ወደጐን ፡ ጥለን ፤ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮችን ፡ ብቻ ፡ እንገልጣለን ።

የኤርትራ ፡ መልክዓ ፡ ምድርና ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ ሁኔታ ፡ ጥንት ፡ ከላይ ፡ በጠቀስናቸው ፡ በዘላኖቹና ፡ ሰፍረው ፡ በሚኖሩት ፡ የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ የወሰን ፡ ክልል ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ "— ተመሳሳይ ፡ መልክዓ ፡ ምድር ፡ ባላቸውና ፡ በእምነታቸው ፡ በለጥ ፡ ብለው ፡ በሚታዩት ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሰፈረው ፤ የጋራ ፡ ቋንቋ ፡ (ትግርኛ) የተስፋፋ ፡ ሃይማኖት ፡ (አርቶዶክስ ፡) እና ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለው ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። በስተምሥራቅና ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኙት ፡ በረሀ ፡ ቀመስ ፡ ቀበሌዎች ፡ ግን፡ በብዛትና ፡ በአቋቋም ፡ ቢለያዩም ፡ ዘላንነትና ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ በሆነው ፡ ኑሯቸውና ፡ በጋራ ፡ እምነታቸው ፡ በእስልምና ፡ የተሳሰሩ ፡ የብዙ ፡ ጎሳዎች ፡ መኖሪያዎች ፡ ናቸው ።"[10]

ስለዚህም ፡ "---በደጋው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙት ፡ የሐማሴን ፤ የአክለ ፡ ጉዛይና ፡ የሰራዬ ፡ ቀበሌዎች ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ የተለዩ ፡ 'ሀገሮች ፡' ሲሆኑ ፤ በታሪክ ፡ በጠባይ ፡ በባሕል ፡ እንኳን ፡ ከሌላው ፡ የማይገጥሙ ፡ ናቸው ፤ ሕዝቡም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ ያውቀዋል ።"[11]

---

9. "የኤርትራ ፡ ልማዳዊ ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ከሕዝቡ ፡ ታሪክ ፡ አኗኗርና ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው። የነዚህ ፡ የተያያዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነጥቦች ፡ ተዛምደው ፡ ካልተመረመሩ ፡ ሁኔታው ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ።" አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ላንድ ፡ ቴኒዩር ፡ ኢን ፡ ኤሪትሪያ ፤ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ· ም·) ገጽ ፡ ፩ ።
10. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ሬስስ ፡ ኤንድ ፡ ትራይብስ ፡ አፍ ፡ ኤሪትሪያ ፡ (፲፱፻፴፰ ዓ· ም·) ገጽ ፡ ፩ ።
11. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፴ ።

<u>ምዕራፍ ፡ ፩</u>

<u>በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፡ ስለሚገኙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋምና ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤</u>

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩</u> ፥

<u>ስለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋማቸው ፡-</u>

የኤርትራን ፡ የክርስቲያን ፡ ሕዝቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ከመሬት ፡ ስሪታቸው ፡ ነጥሎ ፡ ማጥናት ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የማይነጣጠሉ ፡ ተደራራቢ ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሆኑ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ ይገባቸዋል ። በቅርቡ ፡ እንደምናመለክተው ፡ ሁሉ ፤ በእነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ "የተመሠረተው ፡" በመሬት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ የሕዝቡ ፡ መብትና ፡ ግዴታም ፡ የሚወሰነው ፡ "መሬት ፡ ባለውና ፡ በሌለው ፡" በሚል ፡ ክፍያ ፡ መሠረት ፡ ነው። ሆኖም ፡ ጉዳዩን ፡ ግልጥ ፡ አድርገን ፡ ለማስረዳት ፡ ቀጥለን ፡ ስለሕዝቡ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ አንዳንድ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦችን ፡ እናመለክታለን ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በትክክል ፡ እንደተገለጠው ፤ "---በኤርትራ ፡ በሚገኙ ፡ ደጋ ፡ አውራጃዎች ፡ (ሐማሴን ፤ አክለ ፡ ጉዛይና ፡ ሰራዬ ፡) ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ የሆኑ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የሀበሻ ፡ ሕዝቦች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ነበራቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ባንድ ፡ በኩል ፤ በየመንደሩ ፡ የሚገኙ ፡ የመንግሥት ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ አቋሞች ፥ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በኤርትራ ፡ 'መንግሥቲ ፡' የሚባለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማዕከላዊ ፡ መንግሥት ፡ (ናቸው) ።[12]"

"ለገበሬው ፡ ሕዝብ ፡" ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የፖለቲካ ፡ አቋሞች ፤ የመንደሩ ፡ (አነስተኛው) እና ፡ የቀበሌው ፡ (ከፍተኛው ፡) ናቸው[13] ። የመጀመሪያው ፡ የሚተዳደረው ፡ በጭቃ[14] ፡ ነው ። ብዙ ፡ መንደሮች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ደግሞ ፡ ኃላፊያቸው ፡ በሆነው ፡ በምስለኔ ፡ ስር ፡ ይተዳደራሉ ።

በብዙዎች ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ጭቃው ፡ ማዕከላዊውን ፡ መንግሥትና ፡ መንደሩን ፡ የሚያገናኝ ፡ ሹም ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ፤ ግብር ፡ ይሰበስባል ፤ የመንግሥትንም ፡ ትእዛዝ ፡ ለሕዝብ ፡ ያስተላልፋል ።[15] የዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ ክርክር ፡ ሰምቶ ፡ መወሰን ፡ የሆነ ፡ ዳኞች ፡ ቢኖሩም ፥ ጭቃው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በዳኝነት ፡ መልክ ፡ አንዳንድ ፡ አነስተኛ ፡ ወንጀሎችን ፡ ይመለከታል ።[16] በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ ጭቃው ፡ በልማድ ፡

---

12. ዲ ፡ ዱንካንሰን ፤ "ስራት ፡ አድከመ ፡ ምልጋ ፤ ኤ ፡ ኔቲቭ ፡ ኮድ ፡ ሎው ፡ አፍ ፡ ኤሪትሪያ" ፤ <u>አፍሪካ</u> ፤ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፩ ።
13. ኤስ ፡ ናዴል ፤ <u>ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኢን ፡ ኤሪትሪያን ፡ ፕላቶ</u> ፡ (፲፱፻፴፮ ፡ ዓ- ም- ፤ ፎቶ ፡ ኮፒ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ፤ ገጽ ፡ ፪ና ፡ ተከታዮቹ ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ <u>አፍሪካ</u> ፤ በሚለው ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ በ፯ኛው ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፳፪ ፤ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ- ም- ታትሞ ፡ ነበር ።
14. ገብረ ፡ ወልድ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፤ "ኢትዮፒያስ ፡ ትራዲሽናል ፡ ሲስተም ፡ አፍ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኤንድ ፡ ታክሴሽን ፤" <u>ኢትዮፒያ ፡ ኦብዘርቨር</u> ፤ ፭ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፬ ዓ- ም-) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፪ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ይወዳድሯል ።
15. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፩ ።
16. ከዚያው ።

ባለው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚያስተላልፉቸውን ፡ ትእዛዞች ፡ መንደረተኞች ፡ ሁሉ እንዲቀበሉ ፡ ይገደዳሉ ።[17]

"የዘር ፡ (ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡) ርስት" በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሕዝቡ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የተመሠረተው ፡ በዝምድና ፡ ላይ ፡ ነው ።[18] መሠረታዊው ፡ አቋም ፡ "እንዳ ፡" ይባላል ፤ በውስጡም ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ተወላጆች ፡ ይገኙበታል ። "በታሪክ ፡ መሠረት ፡ እንግዲህ ፣ እንዳ ፡ ካንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፣ ማለት ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ ተነስቶ ፡ ያደገ ፡ ሲሆን ፣ ከደረጃም ፡ በኋላ ፡ በቁጥር ፡ በጣም ፡ የሚለያዩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይኖሩበታል ። እነዚህ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ የኢኮኖሚና ፡ የዕለታዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም፡ ናቸው ፤ ማለትም ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኙት ፡ አብረው ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፣ አብረው ፡ የሚሠሩና ፡ የጉልበታቸውንም ፡ ፍሬ ፡ የሚካፈሉ ፡ በቁጥር ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ቤተሰብ ፡ አባሎች ፡ (ወላጆችና ፡ ልጆች ፡) ናቸው ።"[19] ምንም፡ እንኳ ፡ ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉት ፡ ጸሐፊ ፡ እንዳ ፡ የመንደርን ፡ የሚመስል ፡ መሪ ፡ ወይም ፡ አለቃ ፡ የለውም ፡[20] ቢሉም ፣ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ እንዳዎች ፡ አለቆች ፡ አሏቸው ።

የሰራዬ ፡ ጭቃ ፣ ባለመሬት ፡ (ባላባት ፡) የሆነ ፣ ጥንትም ፡ አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹ፡ ጭቃ ፡ ከነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ዘር ፡ የወረደ ፡ መሆን ፡ አለበት[21] ። አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹ ፡ ጭቃ ፡ የነበሩ ፡ ሰው ፡ ለጭቅነት ፡ የታጣ ፡ እንደሆነ ፣ ሹመቱ ፡ የሚሰጠው ፡ በውርስ፡ የተላለፈ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ለማንኛውም ፡ ባለመሬት ፡ ነው ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፣ ጭቃ፡ ለመሆን ፣ በውርስ ፡ የተላለፈ ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ መሆን ፡ ያሻል ፤ ምክንያቱም ፡ "ጭቅነት ፡ በውርስ ፡ የተላለፈ ፡ መሬትን ፡ ይመስላልና ።"[22]

እዚህ ፡ ላይ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ "ባለ ርስት" ፣ "ርስት ፡ የሌለው ፡" የሚባሉትን ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ክፍሎች ፡ አንባቢ ፡ መገንዘቡ ፡ አይቀርም ። ይህ ፡ በኅብረ ፡ ሰብእ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ የሚታየው ፡ ልዩነት ፡ "የመንደር ፡ ርስት ፡" ይገኝባቸዋል ፡ በሚባሉት ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥም ፡ ያለ ፡ ነው ።

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ "(እያንዳንዱ ፡) እንዳ ፡ የተሰጠው ፡ የመሬት ፡ መብት ፤ ---በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ጥንት ፡ የነበረውን ፡ የማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ ልዩነት ፡ የሚያስታውስ ፣ የአቋሙ ፡ መሠረትም ፡ የተጣለበት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ልዩነት ፡ መሠረት ፣ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሀገሪቱ ፡ ጥንታውያን ፡ ነዋሪዎች ፡ ተብለው፡ የሚገመቱ ፡ ሰዎች ፡ ሲኖሩ ፣ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ መጦች ፡ ይገኛሉ" ።[23]

---

17. ሥርዓት ፡ አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡ (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰው ፤ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተረጐመው ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ መድኀኔ ፤ ያልታተመ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ) ፣ "የየመንደረተኛው ፡ ግዴታዎች ፡" በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
18. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።
19. ከዚያው ።
20. ከዚያው ።
21. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፣ "ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡" በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
22. ከዚያው ።
23. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፴፰ ። ከጊዜ ፡ ማለፍና ፡ መሬት ፡ የመግዛት ፡ እድልም ፡ ከመኖሩ ፡ ይህ ፡ ልዩነት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄዷል ።

የመጀመሪያዎቹ ፡ ባለርስቶች ፡ ሲሆኑ ፣ የኋለኞቹ ፡ ግን ፡ ርስት ፡ የላቸውም ። ከዚህም፡ ልዩነት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተከትሎ ፡ ይገኛል ።

የባለርስተኞች ፡ ተወላጅ ፡ መሆን ፡ (ሪም ፡ የሚባሉ[24]) ፡ መብቶችንና ፡ ጥቅሞችን ፣ የጎብረ ፡ ሰብአ ፡ መሪ ፡ መሆንንም ፡ ጭምር ፣ ያስጣል ። በአክለ ፡ ጉዛይ ፣ በሰራዬና ፡ በሐማሴን ፡ ውስጥ ፣ ለሽምግልና ፡ ሊመረጡ ፡ የሚችሉት ፡ ባለርስቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። "(ሽምግልነትም ፡) የየመንደሩን ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ያጠቃልላል። ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ ሕዝቡን ፡ በማኅበር ፡ ለማሠራት ፡ ማደራጀትና ፡ ሥራውንም ፡ መቆጣጠር ፤ ለመንደሩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተገቢው ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ መቆጣጠር ፤ የመንደሩን ፡ ማሳዎችና ፡ ግጦሽ ፡ የሚጠብቁ ፡ ዘበኞችን ፡ መሾም ፤ የርስት ፡ ክርክር ፡ ሲነሣ ፡ በእርቅ ፡ አይቶ ፡ የመወሰን ፡ መብት ። እነዚህ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች፡ ከሹመት ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፣ ሹመቱ ፡ በየተራና ፡ ከተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፣ ይበልጡንም ፡ ጊዜ ፡ ባመት ፣ ለየቤተሰቡ ፡ ይተላለፋል ።"[25]

ሆኖም ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ የባለመሬቶች ፡ ወገን ፡ መሆን ፡ "--- ከመሬት ፡ ይልቅ ፡ ዘላቂና ፡ በሌላም ፡ ሰው ፡ ሊወሰዱ ፡ የማይችሉ ፡ መብቶችን ፡ የሚያስጥ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። የዘር ፡ ርስት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይዞታውን ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊያከራይ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ መያዙ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አይረሳም ። በተጨማሪም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚቆይ ፣ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፣ "አዲስ ፡ መጦችን ፡" በዝቅተኛ ፡ አስተያየት ፡ የሚመለከት ፡ የከበርቴዎች ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ ያደርገዋል ።"[26] ስለዚህም ፡ አንዳንዴ ፣ መሬት ፡ ከመያዝ ፡ ይልቅ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ መሆን ፡ ይበልጥ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

"ዝቅተኛ ፡" ወይም ፡ "አዲስ ፡ መጥ ፡" ከሚባሉት ፡ መካከል ፡ በየክርስቲያኑ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ እስላሞች ፡[27] ይገኙበታል ። ሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ ባሮች ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ሰዎች ፣ ቀጥቃጮችና ፡ መለከት ፡ ነፊዎች ፡ እንደ ፡ "ውጭ ፡" ሕዝብ በመቆጠር ፡ መሬትና ፡ ከመሬት ፡ የሚገኙ ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ይነፈጋቸዋል ። ይህንንም ፡ እገዳ ፡ የሰራዬ ፡ ሕግ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በትህትና ፡ ይገልጸዋል ፤ ቀጥቃጮችና፡ መለከት ፡ ነፊዎች ፡ ከግብር ፡[28] "ነፃ" ፡ ናቸው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነትን ፡ ማሳየቱን ፡ ይገነዘቧል። ይህ ፡ አባባል ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል።[29] የሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ በከፊል ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ። "በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ግዛት ፡

---

24. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታረሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።
25. ከዚያው ።
26. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፬ ።
27. በቤገምድር ፤ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ መካራ ፡ የሱስ ፡ በሚባል ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ በዘርና ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ ፈላሻዎች ፡ (ቤተ ፡ እስራኤላውያን) ፡ እና ፡ እስላሞች ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ አይሰጣቸውም ። ደበበ ፡ ወርቁ ፣ ዘ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ሲስተም ፡ ኢን ፡ መካራ ፡ የሱስ ፡ ኮሚውኒቲ ፡ ኤንድ ፡ ኢትስ ፡ ኢፌክትስ ፡ ኦንዘ ፡ አግሪካልቸራል ፡ ሌበር ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ፦ ም፦ ያልታተመ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ፤) ገጽ ፡ ፫ - ፬ ።
28. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ "ባለእጆች" ፣ በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
29. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ (ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተረጐመው ፡ ዮሐንስ ፡ ሃብተ ፡ ሥላሴ ፤ ያልታተመ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ።)

ክልል ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ እያረሰ ፡ ለንጉሥ ፡ ግብር ፡ የማይከፍል ፡ ሰው ፡ ባለመሬት፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ሊሰይም ፡ መብት ፡ የለውም ። ግብር ፡ ሳይከፍል ፡ አርባ ፡ ዓመታ ት ፡ ቢያልፉ ፡ ግን ፤ --- ግብር ፡ ለመክፈል ፡ ለሚችል ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ መሬቱ ፡ ይሰጥ በታል ። ---ሰውየው ፡ ነፃ ፡ ነው ፤ መሬቱ ፡ ግን ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ አይደለም ።”

ይህ ፡ የግብር ፡ ጉዳይ ፤ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ያሳሰበን ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፤ ማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ በየመንደሩ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተጽዕኖ ፡ ምንድነው ? የሚለው ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በቀደም ፡ እንደቀረበው ፡ አስተያየትና ፡ ይህንንም ፡ አስተያ የት ፡ እንደሚደግፉት ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ የማዕከላዊው ፡ መንግ ሥት ፡ ተጽዕኖ ፡ እጅግ ፡ ያነሰ ፡ ነው ። “ጥንቱንም ፡ በነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በየመሪዎቻቸው ፡ ይተዳደሩ፡ ነበር ። ከሚገዙት ፡ ቀበሌ ፡ ያልተወለዱት ፡ የማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ ሹማምንቶች ፡ እንደ ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢ ፡ ብቻ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።”[30]

አስቀድመን ፡ እንደገለጥነው ፤ ማዕከላዊውን ፡ መንግሥት ፡ በየመንደሩ ፡ ይወ ክሉ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የባለመሬት ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ጭቃዎች ፡ ነበሩ ። መሬት ፡ ለማግኘት ፡ ተወላጅነት ፡ ያን ፡ ያህል ፡ አስፈላጊ ፡ በማይሆንበት ፤ “የመንደር ፡ መሬ ት ፡” እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ስሪት ፡ ባለበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥም ፡ እንኳ ፤ ጭቃ ፡ ለመ ሆን ፤ ጥንት ፡ መሬት ፡ ከነበራቸው ፡ ሰዎች ፡ መወለድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ።[31]

የሕዝቡን ፤ ጉዳይ ፡ በኃላፊነት ፡ እየተከታተሉ ፡ የሚያስፈጽሙት ፡ ሰዎች ፤ ከተ ራው ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ መታየታቸው ፡ ባንዳንድ ፡ ለነሱ ፡ ብቻ ፡ በተጠበቀ ፡መብ ታቸው ፡ ይታያል ። በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ ላም ፡ የሚያርድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምላሱን ፡ (ልሳን ፡ ማንቃ ፡) ለጭቃው ፡ መስጠት ፡ አለበት ።[32] በሰራዬም ቢሆን ፡ “ተዝካር ፡ ወይም ፡ ሠርግ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ ለቀበሌው ፡ አለቃ ፤ ለሕግ ፡ ጠባ ቂውና ፡ ለመንደሩ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ እንስራ ፡ ጠላ ፤ አንድ ፡ ድስት ፡ ወጥና ፡ አምስት ፡ እንጀራ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።”[33] ፡ ይህን ፡ በማይፈጽም ፡ ላይ ፡ ተገ ቢው ፡ መቀጫ ፡ ይጣልበታል ።

ዳግመኛም ፡ በሰራዬ፡ ውስጥ ፤ ጭቃው ፡ የየመንደሩን ፡ ሠርገኛ ፡ ለመመረቅ ፡ የቀደ ምትነት ፡ መብት ፡ አለው ፤ ይህም ፡ መብት ፡ ጭቃው ፡ ሁልጊዜ ፤ በተለይም ፡ በሠርግ ጊዜ ፤ ከመንደሩ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ያስገድደዋል ።[34]

ለጭቃዎች ፡ ከሚሰጡት ፡ መብቶች ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ግን ፡ የየመንደሩ ፡ አባል ፡ በመሆን ፡ ከሚያገኙት ፡ መሬት ፡ ሌላ ፤ በጭቅነታቸው ፡ መሬት ፡ ሊያስገኝላቸው ፡ የሚችለው ፡ መብታቸው ፡ ነው ።[35]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐችን ፡ ላንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ በመጥቀሳ ችን ፡ የምንመረምራቸው ፡ ልማድን ፡ አጥብቀው ፡ የሚከተሉ ፡ ሕዝቦች ፡ የየራሳቸው

30. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፹፯ ።
31. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፹፮ ።
32. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፰ ። የአን ቀጽ ፡ ፲፰ ፡ አርእስት ፡ “የመሬት ፡ ግብር” ፡ ማለቱ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ።
33. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፶፩ ።
34. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ “ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች” ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
35. ከናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከናዴል ፤ ጽሑፍ ፡ ከገጽ ፡ ፳—፳፩ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

የሆኑ፡ሕጎች ፡ እንዳሉዋቸው ፡ መገመታችን ፡ ግልጥ ፡ ነው። በአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጡኑ ፣ "ምዕን ፡ መሐዛ ፡" የተባለውን ፣ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ሲከተል፣ በሰራዬ ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ የሚከተለው ፡ "አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡" የተባለውን ፡ (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዬ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰውን ፡) ሕግ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የሐማሴንና ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ አንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ የየራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ አላቸው ።[36] ለምሳሌም ፡ ያሀል ፡ ገሚስ ፡ ጎኑ ፡ በሐማሴን ፡ የቀረው ፡ ደግሞ ፡ በሰራዬ ፡ አውራጃ ፡ የሚገኘው ፡ የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ቀበሌ ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ አለው ።

እነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ኑሮ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ለመቆጣጠር ፡ የታቀዱ ፣ በጣም ፡ ለተሳሰሩ ፡ የቤት ፡ ሰብም ፡ ሆነ ፡ የመንደር ፡ አቋሞች ፡ እጅግ የተስማሙ ፡ ናቸው ።[37] የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፣ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የአስተዳደርን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦችን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አጠቃለው ፡ የያዙ ፡ ሲሆን ፣ በዝርዝር ፡ የተደነገጉ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንቦችም ፡ አሏቸው ።

የሚያስደንቀው ፡ ነገር ፣ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ቤት ፡ ክርስቲያንና ፡ ካህናቶቻቸው ፡ የሚያገኙትን ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ መቆጣጠራቸው ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ መንፈሳዊና ፡ ዓለማዊ ፡ ጉዳዮችን ፡ እንደሚያስተዳድረው ፡ እንደፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሳይሆኑ ፣ የቤት ፡ ክህነት ፡ አባሎችም ፡ ሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባውን ፡ አንዳንድ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ መመሪያ ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የሏቸውም ።

ከላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩት ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነው ።[38] ጥንት ፡ "---በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የየመንደረተኛውን ፡ ጉዳይ ፡ ለመቆጣጠር ፡ አነስተኞቹ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ይገለገሉበት ፡ የነበረው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተገልጦ ፡ ይገኝ ፡ የነበረው ፡ በምሳሌያዊ ፡ አነጋገር ፡ ሲሆን ፡ ---ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በጽሑፍ ፡ እንዳልዋለ ፡ ሕግ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ፣ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለበት ፡ የእያንዳንዱ ፡ ምሳሌያዊ ፡ አነጋገር ፡ ምንጭ ፡ በመታወቁ ፡ ነበር ። "[39]

እነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩበትን ፡ ምክንያት ፡ መገመት ፡ አያዳግትም ። ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ "ስርዓት ፡ አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡" (በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ፡) ስለተባለው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ሲጽፉ ፡ ጥቂቶ

36. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፴፩ ። የእንግሊዝ ፡ የሚሊታሪ ፡ አስተዳደር ፡ እነዚህን ፡ ሕጎች ፡ ኮድስ ፡ (የተቀናጁ ፡ ሕጎች) ፡ በማለት ፡ ይጠራቸዋል ።

37. የነዚህን ፡ ቋሞች ፡ ቍጥር ፡ የሚገልጥ ፡ ሰነድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። ሆኖም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ታቅደው ፡ የነበሩት ፡ በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኙ ፡ ተመሳሳይ ፡ መንደሮች ፡ ከ፪፻ - ፭፻ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚገኙባቸው ፡ ደራሲው ፡ አረጋግጧል ። በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ለአቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ከተደረገ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። በቄስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ እና ፡ ሌሎች፡ ይግባኝ ፡ ባዮችና ፡ በግራዝማች ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፣ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ (የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፹፪/፶፱ ፡ (ያልታተመ) ፣ ፍርድ ፡ ቤቱ ፣ በትግሬ ፡ የሚገኝ ፣ የምንመረምራቸውን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመስል ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ፩፻፹፰ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚኖሩበትና ፣ "የሚተዳደረውም ፡" በሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ መሆኑን ፡ ይገልጣል ።

38. ኤፍ ፡ ራስል ፣ "ኤሪትሪያን ፡ ከስተማሪ ፡ ሎው ፣ " ጆርናል ፡ አፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው ፣ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፣ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም.) ፣ ገጽ ፡ ፩፻፪ ። ከነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩት ፡ ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

39. ዱንካንሰን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፩፻፵፩ ።

ቹን ፡ ምክንያቶች ፡ ገልጠዋቸዋል ። "የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ማደግ ፤ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ (ከ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ካለው ፡ ዘመን) ፡ ወዲህ ፡ የከተማ ፡ ኑሮ መደርጀትና ፡ የኢጣሊያም ፡ ወታደር ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሸነፍ ፡ በኤርትራ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ላይ ፡ ያስከተለው ፡ ውጤት ፡ ሁሉ ፡ ተደምሮ ፡ በደጋው ፡ የሚኖረውን ፡ ሕዝብ ፡ የመንደር ፡ ኑሮ ፡ አቃውሶት ፡ ነበር ። ተስማሚ ፡ ሆነው ፡ ያልተገኙትም ፡ ከሀበሻ ፡ ባህል ጋር ፡ እጅግ ፡ የተወሳሰቡት ፡ ውርስን ፤ የመንደር ፡ ሹመትንና ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ማከፋፈልን ፡ የሚመለከቱት ፡ ልማዳዊ፡ ሕጎች ፡ ነበሩ ። ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ሕዝብ ፡ በሚያውቀውና ፡ በሚቀበለው ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠ ፡ ባለመሆኑ ፡ ክርክርና ፡ ጭቅጭቅ ፡ እጅግ ፡ እየበዛና ፡ ለመወሰንም ፡ እያዳገተ ፡ ሄደ ። አነስተኛው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ የሀበሻው ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ የፈረንጆች ፡ አስተሳሰብና ፡ ባህል ፡ ተቀይጦበት ፡ እንዳይለወጥና ፡ ጨርሶም ፡ እንዳይጠፋ ፡ ራሱን ፡ ሊያስታውቅና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረገው ፡ ሙከራ ፡ ነበር ።"[40]

"አድገና ፡ ተገለባ ፡" (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰው ፡) በጽሑፍ ፡ እንዲሰፍር ፡ ያደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ እርምጃ ፡ የወሰዱበትን ፡ ምክንያት ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ በሕጉ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ገልጠውታል ።[41] ያልተስተካከለ ፡ ትርጉም ፡ ላለመስጠት ፡ ስንል ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያት ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰነዋል ።

"የሁሉ ፡ ፈጣሪና ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ እግዚአብሔር ፡ በስነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚተዳደር ፡ ስለሆነ ፤ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ በስነ ፡ ሥርዓት ፡ ፈጥሮ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ በየቦታው ፡ መድቦ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ እንዲኖሩ ፡ አደረገ ።

እነሆም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጡራን ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ይኖራሉ ።

ይህ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ አክባሪነት ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ ላለው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ተሰጥቷል ፤ (የሕጉ ፡ መግቢያ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የአዳምንና ፡ የሔዋንን ፡ አፈጣጠር ፡ ይተርካል ፡) ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከአዳም ፡ ውድቀት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ድረስ፡ የተጻፈ ፡ ሕግ ፡ ስላልነበረው ፡ ሕሊናው ፡ ባመለከተው ፡ ብቻ ፡ ሲተዳደር ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በጽሑፍ ፡ ባልሰፈረ ፡ ሕግ ፡ ሊተዳደር ፡ አልቻለም ፤ ምክንያቱም ፤ በሕሊና ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ የሰውን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ በቂ ፡ አልነበረምና ፤ ስለ ዚህም ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ ሕግ ፡ በሙሴ ፡ ተጀመረ ። (የሙሴ ፡ ታሪክ ፡ ይቀጥላል)...

ከክርስቶስም ፡ ወዲህ ፤ ለየጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ማስፈለጉን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተረድቶት ፡ ነበር ። ... ቆስጠንጢኖስ ፡ እንኳ ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ያዘጋጁት ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተባለ ፡ ሕግ ፡ ነበረው ።

ሕግ ፡ ማለት ፡ በእግዚአብሔር ፤ መኳንንትና ፡ በተራው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ሰላምና ፡ ስምምነት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ የሚያደርግ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ።

---

40. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፪ ።
41. የአድና ፡ ተገለባ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ (በትግርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፤ ያልታተመ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፤ የዚህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መግቢያና ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ በመተርጎም ፡ ለረዳው ፡ ለመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ለአቶ ፡ ዓለምሰገድ ፡ ተስፋዬ ፡ ደራሲው ፡ ምስጋናውን ፡ ያቀርባል ።)

ይህ ፡ በጽሑፍ ፡ ያሰፈርነው ፡ ሕግ ፤ አባቶቻችን ፡ ያቋቋሙት ፡ በቃል ፡ የነበረው ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፤ አሁን ፡ ለገጠመን ፡ ችግር ፡ እንዲስማማ ፡ በማሰብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ከእውነተኛ ፡ ፍላጐት ፡ የመነጨና ፡ የብዙዎችም ፡ ድጋፍ ፡ የተጨመረበት ፡ ነው ። የተመሠረተውም ፡ ለቅዱሳን ፡ መጻሕፍትና ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ባለን ፡ አክብሮት ፡ ላይ ፡ ነው ።

በስነ ፡ ሥርዓት ፡ ተቀናብሮ ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ ሕግ ፡ አለመኖሩ ፤ የሕግ ፡ አቋማችንን ፡ በሚያሳዝንና ፡ በሚነቀፍ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ጥሎት ፡ ይገኛል ። የጊዜያችንን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ እንድንችል ፤ ሕጋችንን ፡ በጽሑፍ ፡ ማስፈር ፡ እንዳለብን ፡ ተረድተነዋል ። ሌላውም ፡ ዓላማችን ፡ ሕጉ ፤ በተለይም ፡ የማስረጃን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፤ የተለያየ ፡ የግል ፡ ትርጉም ፡ እንዳይሰጠውና ፡ ሕጉም ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። . . .” (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ቃል ፡ የ ጊያነብ ፡ ሁሉ ፡ ቤተክርስቲያንንና ፡ ካህናቶቿ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ተጽዕኖ ፡ በቀላሉ ፡ ይረዳዋል ። ስለ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያንና ፡ ስለ ፡ ካህናቶችዋ ፡ ቀጥለን ፡ ባጭሩ ፡ እንመለከታለን ።

በጽሑፋችን ፡ ውስጥ ፡ በምንነጋገርባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፤ ማለት፡ በሰራዬ ፡ በአክለ ፡ ጉዛይና ፡ በሐማሴን ፤ እንደ ፡ መንደር ፡ ሹማምንት ፡ ሁሉ ፡ ቄሶችም ፡ በሹመታቸው ፡ በሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ፤ ዓለማዊ፡ ጥቅምም ፡ ያገኙበታል ።

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ በሠራዬ ፡ ውስጥ ፡ “---የየመንደሩ ፡ አድባራትና ፡ ካህናቶቻቸው ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ የተለየ ፡ መሬት ፡ አላቸው ።”[42] የመንደር ፡ መሬት ፡ በሚገኝበት ፡ በአንዳንድ ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ቀበሌም ፡ ውስጥ ፡ “---ለየመንደሩ ፡ ካህናት ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ለሕዝቡ ፡ ከሚከፋፈለው ፡ መሬት ፡ የተለየ ፡ ሲሆን ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከሚደረገውም ፡ ክፍያ ፡ ነፃ ፡ ነው ። ”[43]

ካህናት ፡ እነዚህንና ፡ ሌሎችንም ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅሞች ፡ የሚያገኙት ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ የአገናኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አለን ፡ በማለት ፡ ለሚያበረክቱት ፡ አገልግሎት ፡ ነው ። ክርስትና ፡ ማንሳት ፤ የጋብቻና ፡ የቀብር ፡ ስነ ፡ ስርዓት ፡ ማከናወን ፤ ፍትሐት ፡ መፍታትና ፡ የተዝካር ፡ ጸሎት ፡ ማድረስ ፡ ከተለዩ ፡ ተግባሮቻቸው ፡ ጥቂቶቹ ፡ ናቸው ።[44]

ካህናት ፡ ያለ ፡ አቅማቸውን ፡ ሁሉ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲያውሉ ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ሕግ ፡ (ራሳቸውንና ፡ ልጆቻቸውን ፡ በሚመለከት ፡ ክርክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር) ፡ ካህናትን ፡ ጥብቅና ፡ እንዳይቆሙ ፤ ወኪል ፡ እንዳይሆኑና ፡ ጭቅነት ፡ እንዳይሾሙ ፡ ያግዳቸዋል ። “(የነሱን ፡ የሚመስል) ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ስለሌለ ፡ (ካህናት) የክህነት ፡ ሥራቸውን ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ፤ ስለዚህም ፡ በዓለማዊ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ መግባት ፡ አይገባቸውም”[45]--- ፡ የዚህ ፡ እገዳ ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ግልጥ ፡ ነው ፤

---

42. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።
43. ከዚያው ።
44. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ “ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እና ፡ ካህናት” ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
45. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

ካህናት ፡ የተማሩና ፡ ሀሳባቸውንም ፡ በቀላሉ ፡ የመግለጥ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ የኅብረ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ አባል ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ።

ካህናት ፡ የሚያገኙት ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ የግል ፡ እንጂ ፡ ተወራራሽ ፣ ተላላፊ ፡ አይደለም ። "(ዝሙት ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ ሚስቱን ፡ በመፍታት ፡) ማዕረጉን ፡ ያጣ ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ መንደረተኞች ፡ ይረዱኛል ፡ ብሎ ፡ እርዳታቸውን ፡ መጠበቅ ፡ አይገባውም ፤ ምክንያቱም ፡ (ቅዳሴ ፡ መቀደስ ፡) አይቻለውምና ። ---ቅዳሴ ፡ ለመቀደስ ለሚችል ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ግን ፡ መንደረተኛው ፡ አውጣጥቶ ፡ እርዳታ ፡ ሊያደርግለት ፡ ይገባል ። (የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ማዕረጋቸውን ፡ ያጡ ፡ ቀሳውስት ፡ ቅዳሴ ፡ መቀደስ ፡ ባይቻላቸውም ፡) ከሌሎች ፡ ካህናት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ለመዘመር ፣ ለመጸለይ ፣ ለመቆምና ፡ ፍትሐት ፡ ሲደረግም ፡ ለመፍታት ፡ ስለሚችሉ ፣ ለዚሁ ፡ 'የከንፈር ፡ ዋጋ' ፡ ይከፈላቸዋል ።"[46]

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በጨረፍታ ፡ ስለጠቀስናቸው ፡ ሽማግሌ ፡ "ዓዲ ፡" ስለሚባሉት ፡ ሽማግሌዎች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ እንናገራለን ። ቁጥራቸው ፡ ከመንደር ፡ መንደር ፡ የሚለያየው ፡ እነዚህ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በደርግ ፡ በደርግ ፡ በመከፋፈል ፡ "...ለኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ የሚበጀውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይወስናሉ ። ክርክሮችንና ፡ ጠቦችን፡ በእርቅና ፡ በግልግል ፡ መልክ ፡ ይቆርጣሉ ፤ (እተራው) ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ቀርበው ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ሊገደዱ ፡ አይችሉም ። በየመንደሩና ፡ በየተከራካሪው መካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ወሰን ፡ ወስነው ፡ ምልክት ፡ ያስደርጉበታል ።"[47] ባንዳንድ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ የሽማግሌዎች ፡ ደርግ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፣ ከዘመናትም ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ መሬት ፡ ከነበረው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተወላጅ ፡ መሆን፡ አለባቸው ።[48] የተባሉት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በምንመረምራቸው ፡ የመንደር ፡ መሬት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ እንዳላቸው፡ እናመለከታለን ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡

ስለመሬት ፡ ስሪታቸው ፤

በደጋው ፡ የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ እንደሚገኝ ፡ ይነገራል ፤ የግል ፡ ርስት[49] ፡ በቤተ ፡ ሰብ ፡ መሪዎች ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ጨምሮ ፤ የዘር ፡ ርስት ፡ ("በትክክለኛው ፡ አነጋገር ፡ የእንዳ ፡ ርስት---") እና ፡ የመንደር ፡ ርስት[50] ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ አመዳደብ ፡ በግልጥ ፡ የተለያየና ፡ ራሱ

---

46. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ "ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ካህናት" በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
47. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፲፮ ።
48. አስቲኒ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፹፰—፺፬ ። ደራሲው ፡ የተጠቀመባቸውን፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፹፰—፺፬ ፡ ያሉትን ፡ ጥቅሶች ፡ የተረጐመው ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ መድኀኔ ፤ የሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ነበር ።
49. የግል ፡ መሬት ፡ ስሪት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ተስፋፍቶ ፡ እንደሚገኝ ፡ ይነገራል ። ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፣ አግራሪያን ፡ ሪፎርም ፡ ኤ ፡ ፕሮፖዛል ፡ ቱ ፡ ኮንቲሪቢውት ፡ ቱ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ዴቨሎፕሜንት ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (፲፱፻፶፮) ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያልታተመ ፤ በዩኒቨርሲቲው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት፡ የሚገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፭፺፯ ፡ ይመለከቷል ።
50. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፭፭ ።

ንም ፡ የቻለ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ በውርስና ፡ መልሶ ፡ መላልሶ ፡ በመከፋፈል ፣ የዘር ፡ ርስት ፡ የነበረው ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የግል ፡ ርስት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[51]

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ "የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን" ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት፡ ስለሆነ ፣ ስለ ፡ ግል ፡ ርስት ፡ የምናደርገው ፡ ምርምር ፡ አይኖርም ።

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ እንደተገለጠው ፤ "---ከኢትዮጵያ ፡ በስተሰሜናዊ ፡ ምዕራብ፡ ክፍል ፣ ማለትም ፡ ሐማሴን ፣ ሰራዬንና ፡ አክለ ፡ ጉዛይን ፡ ከኤርትራ ፤ የትግሬን ፡ የቤጌ ምድርንና ፡ የጐጃምን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በሙሉ ፤ የላስታንና ፡ የዋግ ፡ አውራጃዎችን ፡ ከወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሚያጠቃልለው ፡ ሀገር ፡ ውስጥ፣ የሚገኘው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የጋርዮሽ ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ ስሪት ፡ (ኮሙናል ፡ ቴንየር) ነው ።"[52] "የኅብረት ፡ ስሪት" (ኮሙናል ፡ ቴንየር) ሲባልም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ባለመብትነት ፡ የግል ፡ አለመሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ሲሆን ፣ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርም ፡ የዘርንና ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪቶችን ፡ ያጠቃልላል ።

በዘርና ፡ በመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ስር ፡ ያሉት ፡ መብቶች ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆኑ፡ ለየብቻ ፡ እንመረምራቸዋለን ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮችን ፡ መጥቀስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ቢገኝበትም ፤ በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሚታየው ፡ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቢገኝም ፡ በአክለ ፡ ጉዛይና ፡ በሐማሴን ፡ ውስጥ፡ በብዛት ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሚታየው ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው[53] ። ሁለተኛም ፤ የዘርንና ፡ የመንደር ፡ ርስትን ፡ የሚያዋህደው ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም ፤ ሁለቱም ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነቶች ፡ መታየት ፡ ያለባቸው ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፣ በተለይም ፡ ተስፋፍቶ ፡ በሚታየው ፡ "የመሬት ፡ ችግር ፡" አንጻር ፡ ነው[54] ። ይህ ፡ የመሬት ፡ ችግር ፡ ነው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የመሬት ፡ ስሪቶች ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ የሚያስችለው።

(ሀ) <u>ስለዘር ፡ ርስት ፤</u>

(፩) <u>አመጣጡ ፤</u>

ጉዳዩን ፡ የመረመሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ሁሉ ፣ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ጥንት ፡ በይዞታ ፡ ብቻ ፡ ከተገኘ ፡ የግል ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ እንደመነጨ ፡ ይናገራሉ ።

ስለዚህም ፡ "--- (የዘር ፡) ርስት መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ታሪክን ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፣ ይህም ፡ ስሪት ፡ ጥንት ፡ አንድ ፡ ሰው ፣ ወይም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፣ ሰው ፡ ያልሰፈረበትን ፡ መሬት ፡ በመያዝ ፡ ከመሠረተውና ፡ ከጊዜ ፡ በኋላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ በመያዝ ፡ ከተለዋወጠው ፣ በግልጽ ፡ የተወሰነ ፡ ትርጉም ፡ ከነበረው ፡ የግል ፡ ባለቤትነት ፡ እንደመጣ ፡ ታሪክ ፡ ያስረዳናል ። ጥንት ፡ መሬቱን ፡

---

51. ከዚያው ።
52. ሎውረንስ ፡ ኤንድ ፡ ማን ፣ "ኮሙናል ፡ ላንድ ፡ ቲኒየር ፡ ኢን ፡ ኢትዮፕያ ፡" <u>ኢትዮፕያ ፡ ኦብዘርቨር</u> ፤ ፱ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቍጥር ፡ ፬ ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፬—፫፻፲፭ ።
53. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፳ ።
54. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፩ ።

የያዘው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባሎች ፡ በተፈጥሮ ፡ ሲባዙ ፣ የመሬቱ ፡ ባለቤትነት ፡ ከግል ፡ ወደጋርዮሽነት ፡ ተለወጠ ።”[55]

ይህ ፡ ለውጥ ፡ የመጣበትን ፡ ሁኔታ ፡ ሲኖር ፡ አስቲኒ ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ይገልጡታል ። “ያንድ ዘር ፡ ወይም ፡ ጎሣ ፡ መሥራች ፡ አባት ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ መሬት ፡ ይይዛል ። ልጆቹም ፡ በወራሽነት ፡ መብታቸው ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲመስላቸው ፡ ያን ፡ መሬት ፡ ቆራርጠው ፡ ይከፋፈሉታል ። በመ ጀመሪያ ፡ አንድ ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ ከመሥራች ፡ አባቱ ፡ ለተወለዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ይከፋፈላል ። ለመሥራች ፡ አባቱ ፡ የመጀመሪያም ፡ ተወ ላጆች ፡ ተከፋፍሎ ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ በመከታተል ፡ (እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ እየተቆ ራረጠ ፡) ለተወላጆች ፡ ይከፋፈላል[56] ።” እንደዚህም ፡ እያለ ፡ ጥንት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ የነበ ረው ፡ መሬት ፡ በተወላጆቹ ፡ መካከል ፡ ተቆራርጦ ፡ ይከፋፈላል ፤ ሲሉ ፡ አስቲኒ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ይደመድማሉ ።

በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ታላቁ ፡ አቋም ፡ የሆነው ፡ እንዳ ፡ (“---በውስጡ ፡ የሚገኙት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ትልልቅ ፡ የግል ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሲሆኑ ፣ እንዳውም ፡ በዚያው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሚታወቅ ፡ ነው ፡ ---”) እንደ ፡ አንድ ፡ ቀበሌ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ፡ ተብ ሏል ። “(በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ) ፡ ዋነኛ ፡ የሆነው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነት ፣ ማለትም ፡ ፍጹም ፡ የሆነው ፡ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ርስት) --- ከእን ዳው ፡ ጋር ፡ የተማሠረ ፡ በመሆኑ ፣ እንዳው ፡ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ ስም ፡ ቢሆንም) ባንድ ፡ ወገን ፡ የተወሰነ ፡ ቀበሌ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። የእንዳ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ በግል ፡ ባለሀብትነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስተዳድረው ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የግለኛ ፡ መብት ፡ ተገኘ ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ እንዳው ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖረው ፡ ጥንት ፡ በይዞታ ፡ ከተገኘው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ ነው ። ይህም ፡ አስተሳሰብ ፡ የመሬት፡ ክርክር ፡ በተነሣ ፡ ቁጥር ፡ በግልጥ ፡ ከመታየቱም ፡ በቀር ፡ እንዳውን ፡ ከሚያስተሳስሩት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ።”[57]

እንዳ ፡ ሲባል ፡ “ተለዋዋጭ” የሆነ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘቧል ። “አንድ እንዳ ፡ ---በግልጽ ፡ ተለይቶ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ክፍልፋዮች ፡ ስላሉት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲለዋወጥ ፡ በሱና ፡ በውስጡም ፡ ባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ማየት ፡ ያዳግታል ። ምክንያቱም ፡ በእንዳው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት፡ ቤተሰቦች ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ እጅግ ፡ ትላልቅ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። በሦስት ፡ ወይም ፡ በአራት ፡ ትውልድ ፡ የሚለያዩ ፡ ተወላጆች ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በመባባል ፡ ተዋህደው ፡ በመገኘት ፡ ከእንዳው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ፣ ወደፊትም ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ እንዳ ፡ ለማቋቋም ፡

:

55. ከዚያው ፣ ገጽ ፡ ፳ ።

56. አስቲኒ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፹፫ ፡ እና ፡ በሚከተሉት ፡ ገጾች ።

57. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፰ ። ከአምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ ከተጠቀሰው ፣ ከገጽ ፡ ፫ ጋር ፡ ያወዳድሯል ። በስህተት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እየተባለ ፡ በሚተረጐመው ፡ እንዳ ፡ በሚባለው ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ የሚ ቆጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሊገኙበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ አጥብቆ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ከእንዳ ፡ በለወይ ፡ በለዛ ፡ (ሐማሴን) ፤ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ እንዳ ፡ ጐመራ ፡ (ሰራዬ) ፤ መልስ ፡ ሰጭ ፡ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ- ም- የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፶፮/፫ ፡ (ያልታተመ) ፤ ዘጠኝ ፡ ትውልድ ፡ ወይም ፡ ከ፩፻፶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ይኖር ፡ ከነበረ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ ነኝ ፡ በሚል ፡ ክርክር ተወላጆች ፡ ከሚካፈሉት ፡ መሬት ፡ ድርሻዬ ፡ ይሰጠኝ ፡ የሚል ፡ ክስ ፡ ከቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

የሚችል ፡ ክፍል ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ።"[58] አንድ ፡ እንዳ ፡ እጅግ ፡ ከበዙ ፡ ቤት ፡ ሰቦች፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ በብዙ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፋፈልና ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ በየ ራሱ ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ይጀምራል ።[59]

(፪) ስለ ቃላት ፡ አገባብ ፤

በምንመረምራቸው ፣ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ በእርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ መብቶችን ፡ ለማመልከት ፡ ሕዝቡ ፡ የሚጠቀምባቸውን ቃላት ፡ አገባብና ፡ ትርጉም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ከአንባቢው ፡ ማስተዋወቅ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው።

በጣም ፡ የሚዘወተረው ፡ ቃል ፡ "ርስቲ" የሚለው ፡ ነው ። "ይህም ፡ ቃል ፡ ረስተ ፡ ከሚለው ፡ ከግዕዙ ፡ ቃል ፡ የመጣ ፡ ነው ። በብዙ ፡ ስሜትና ፡ ትርጉም ፡ ስለሚ ገባ ፡ መሬት ፡ ገብቶ ፡ መያዝን ፣ (የመሬትን ፡ ይዞታንና ፡ ባለቤትነትን ፡) ያመለክታል።"[60] በጠቅላላ ፡ አነጋገርም ፡ ሲገባ ፡ "---ከግል ፡ ባለቤትነት ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ቤት ፡ ሰብ ፡ ባለቤትነት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት"[61] ሁሉ ፡ ያመለክታል ። ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ "ርስቲ" ፡ የሚለው ፡ ቃል "የዘር፡ወይም፡የቤተ፡ሰብ ፡ ርስትን ፡" የሚያመለክት ፡ ተደርጐ ፡ የሚገባ ፡ ሲያስመስሉት ፣ አቶ ፡ አምባዬ ፡ የተባሉ፡ ደራሲ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ ይገልጣሉ። "ቃሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለን፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ የሚያመለክት ፡ አጠቃላይ ፡ ቃል ፡ ነው ። የመብቱ ፡ ዓይነት ፡ ሊለይ ፡ ሲፈልግ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ በቅጽል ፡ መልክ ፡ ይገባል ።"[62]

ስለዚህ ፡ <u>ርስቲ ፡ ዴሳ ፡</u> (የመንደር ፡ ርስት) ፡ <u>ከርስቲ ፡ ጽልሚ ፡</u> (የግላዊ ፡ ርስት) <u>እና ፡ ከርስቲ ፡ ጉልቲ ፡</u> (ከርስት ፡ ጉልት) ይለያል ። እንደ ፡ አቶ ፡ አምባዬም ፡ አስተ ሳሰብ ፡ ርስቲ ፡ የሚያመለክተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ማንኛውንም ፡ መብት ፡ ነው[63] ።

በሰራዬ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፣ ርስቲ ፡ ማለት ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ የተወረሰ ፡ ወይም ፡ ለደም ፡ ዋጋ ፡ የተከፈለ ፡ ወይም ፡ በግዢ ፡ የተገኘ--- ወይም ፡ ጫካን ፡ መንጥሮ ፡ በማ ልማት ፡ የተያዘ ፡ <u>መሬት</u>[64] ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

በንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ፡ ውስጥ ፡ የጠቀስናቸው ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ የሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ርስተኛ ፡ (በነጠላ) ወይም ፡ ርስትኛታት (በብዙ) ተብለው ፡ ይጠራሉ ። የዘር ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበ

---

58. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።
59. ከዚያው ።
60. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፳ ። ከሚቀጥለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ፤ "ርስቲ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በየቀበሌው ፡ ከሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህሎች ፡ ጋር ፡ የተወሳ ሰበ ፡ በመሆኑ ፣ አንድ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ የሚችል ፡ ቃል ፡ አይደለም ። ምናልባትም ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የቅርብ ፡ ተመሳሳዩ ፡ ከጭሰኝነት ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጋር ፡ የሚቃረነው ፡ አሎድ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ።"
61. ዱንካንሰን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፱ ፣ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፮ ። ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፯ ።
62. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፳ ።
63. ከላይ ፡ በጠቀስነው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ አምባዬ ፡ "ንብረት" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ "መብት፡" በሚል ፡ ስሜት ፡ እንዳገቡት ፡ ይገነዘቧል ።
64. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፮ ፡ የተጠቀሰው ፡ "የ<u>ርስቲ ፡</u> ደንቦች" ፡ በሚል፡ አርእስት ፡ ሥር ።

ሌ ፡ ውስጥ ፡ ርስተኛ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻውን ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ ያለውና ፡ መሬት ፡ መያዝም ፡ የሚያስከትላቸውን ፡ መብቶችና ፡ ጥቅሞች ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችል ፡ ነው ። የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ርስተኛ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ተወላጅነቱ ፡ ከጥንት ፡ የባለርስቶች ፡ ወገን ፡ የሆነ፡ ነው ።

(፫) <u>በእርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ ግላዊ ፡ መብቶች ።</u>

የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ባሳየው ፡ ለውጥ ፡ ከሁለት ፡ መልኮች አንዱን ፡ እንደሚይዝ ፡ ታውቋል ። "የጋራ ፡ ባለቤትነት ፡ ተጠብቆ ፡ ይቆይና ፡ እያንዳንዱ ፡ ተወላጅ ፡ የባለአላባ ፡ መብቱን ፡ የሚያስከብርበት ፡ መንገድ ፡ ይፈጠራል ፤ ወይም ፡ ርስቱ ፡ በውርስና ፡ በተወላጆች ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ መከፋፈል ፡ ጥንት ፡ የነበረውን ፡ የግል ፡ ባለቤትነት ፡ መልክ ፡ መልሶ ፡ ይይዛል ።"[65] የመጀመሪያው ፡ እንዲሁ ፡ "ርስቲ" ተብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ "ጽልሚ" ተብሎ ፡ ይጠራል ።

በአንዳንድ ፡ የርስቲ ፡ ስሪት ፡ (ከጽልሚ ፡ ጋር ፡ በተነፃፃሪነት ፡ ሲገባ) በሚገኝባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ ባልና ፡ ሚስትና ፡ ያላገቡ ፡ ልጆቻቸው ፡ የሚገኙበት ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ ያርሳል[66] ። የማሳውም ፡ ስፋት ፡ የሚወሰነው ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ፍላጐት ፡ ነው[67] ። ማሳውም ፡ "ግራት" ማለትም ፡ እርሻ ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ቦታ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል[68] ። የሟች ፡ ተወላጆች ፡ ድርሻ ፡ ለኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆንና ፡ አዲስ ፡ ለተጋቡ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይከፋፈላል ። እዚህ ፡ ላይ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ በውርስ ፡ ሊተላለፍ ፡ ባይችልም ፡ እንኳ ፡ ከኀብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ ድርሻን ፡ የማግኘቱ ፡ መብት ፡ በውርስ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ነው[69] ።

ማሳ ፡ ሊያገኙ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ አግብተው ፡ ትዳር ፡ የያዙ ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በአጠቃላይ ፡ አነጋገር ፡ ሴቶችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ በተላለፈ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ የላቸውም[70] ።

ማንኛውም ፡ ድርሻውን ፡ ማሳ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ሊያርሰው ፡ ሊሸጠው[71] ፡ ወይንም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ለሌላ ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ሊሰጠው ፡ የሚችለው ፡ የእንዳው ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ የመንደሩ ፡ ሰዎች ፡ ማሳውን ፡ ለመግዛት ፡ ወይንም ፡ ለመውሰድ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሳይሆኑ ፡ ሲቀሩ ፡ ነው ።

ጽልሚ[72] ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቤተ፡ ሰብ ፡ የአንድ ፡ የተወሰነና ፡ የታወቀ ፡ ማሳ፡ ባለቤት ፡ ነው ። በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡

65. ናዴል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።
66. የዘር ፡ ርስት ፡ ሲባል ፡ የሚታረስ ፡ መሬት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። "(የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡) <u>ርስቲ</u> ፡ ስፋት፡ የሚታወቀው ፡ የሚታረሰውን ፡ መሬት ፤ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ጫካንና፡ የውሃ ፡ ኩሬንና ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ስፋት ፡ በመደመር ፡ ነው ።" ፡ አስቲኒ ፤ ከላይ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፻፷ ።
67. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፸ ።
68. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፺ ።
69. ከዚያው ።
70. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፭ ።
71. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፺ ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እናትትበታለን ።
72. አቶ ፡ አምባዬ፡ ርስቲ፡ ጽልሚን ፡ "ፍጹም ፡" የግል ፡ ንብረት ፡ በማለት ፡ ገልጸውታል ። አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺ ።

ከአባት ፡ ወገን ፡ በመጣ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ርስትም ፡ በአገቡ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የሚከፋፈለው ፡ በአባትየው ፡ ነው ። ባለመብቶች ፡ ብዙ ፡ በሚሆኑበትም ፡ ጊዜ ፡ ርስቱ ፡ የሚከፋፈለው ፡ አባትየው ፡ በመረጣቸው ፡[73] ሽማግሎች ፡ አማካይነት ፡ ነው ።

በሰራዌ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻውን ፡ የሚያገኘው ፡ በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ "ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ በመሆን ፡ የኢኮኖሚ ፡ ነፃነት" በሚያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።[74] እንዲያውም ፡ ሙሽራው ፡ ሊያገኝ ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ አባቱ ፡ የሠራውን ፡ አንድ ፡ ቤት ፤ የእርሻ ፡ መሣሪያዎችን ፤ ከማግባቱ ፡ በፊት ፡ በእርሻው ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ካስገኘው ፡ ሰብል፡ በተወሰነ ፡ ልክ ፡ ተሰፍሮ ፤ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ እንስሳትንና ፡ ከአባቱ ፡ የቤት ፡ ዕቃዎች ፡ አንድ ፡ ሦስተኛውን ፡ ወይንም ፡ አንድ ፡ አራተኛውን ፡ ጭምር ፡ ነው ።[75]

ሴቶችና ፡ (ጓል) ተወላጆቻቸው ፡ (ደቀ ፡ ጓል) ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ በመጣ ፡ ርስትም፡ ሆነ ፡ ጽልሚ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ድርሻ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ተነፈጉ ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በአእምሮአችን ፡ ይጉላላ ፡ ይሆናል ። ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ የተባሉ ፡ ጸሐፊ ፡ መልስ ፡ ይሆናል ፡ ያሉትን ፡ አንድ ፡ አስተያየት ፡ አቅርበዋል ። "በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚፈጸመው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ (ቃል ፡ ኪዳን) መሠረት ፡ የሴቷ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ለወንዱ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ የሚሰጠው ፡ ጥሎሽ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቿ ፡ ከሚኖርባቸው ፡ ግዴታ ፡ ቤተሰቦቿን ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸዋል ። በሁለቱ ፡ አባቶች ፡ መስማማትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አለመስማማት ፤ ወጣት ፡ ሠርገኞቹ ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ቢሰጣቸውና ፡ የወንድየው ፡ አባት ፡ በሕይወት ፡ እስካለም ፡ ድረስ ፡ በጥሎሹ ፡ ላይ ፡ የይዞታ ፡ መብት ፡ ቢሰጣቸው ፤ ከግዴታ ፡ ነፃ ፡ መውጣታቸው ፡ እንደጸና ፡ የሚቆይ ፡ ነው ።"[76] በተጨማሪም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ እውነተኛ ፡ ትርጉሙ ፤ "ጥሎሽ ፡ ጥሎ ፡ ቤተ ፡ ዘመድን ፡ ነፃ ፡ ማውጣት" መሆኑን ፡ ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ ይናገራሉ ።

ይህም ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚታየው ፡ ሴት ፡ ልጆችንና ፡ ተወላጆቻቸውን ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ የመጣ ፡ እርስትን ፡ አለማካፈል ፡ "ለወንዶች ፡ ልጆች ፡ ውርሳቸውን ፤ ለሴቶች ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ጥሎሻቸውን ፡"[77] በሚለው ፡ ምሳሌያዊ ፡ አነጋገር ፡ ይገለጻል ።

ይህ ፡ እገዳ ፡ በሌለበት ፡ ቀበሌ ፡ ደግሞ ፤ የሴቶች ፡ ልጆችና ፡ የተወላጆቻቸው ፡ መብቶች ፡ አንዳንድ ፡ ወሰን ፡ ይደረግባቸዋል ። ይኸውም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ ሊሸጡ ፡ ወይንም ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ርስትነት ፡ ሊለውጡት ፡ አይችሉም ። በወንዶች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ተመሳሳይ ፡ የመብት ፡ ወሰን ፡ ተጥሎ ፡ አይገኝም ።[78] ሆኖም ፤ (እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር) ከ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ርስቱን ፡ እንዳይሸጥ ፡ ታግዷል ።[79] "ርስትን ፡ መሸጥ ፡ አይቻልም ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አንድ ፡

---

73. አስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፷—፺፬ ።
74. የሰራዌ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፳፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ በ"ኢኮኖሚ ፡ ነፃነት" ፡ ስር።
75. ከዚያው ።
76. ዱንካንሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺፬ ።
77. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፯ ።
78. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
79. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፳ና ፡ ፳፪ ።

001624

ሰው ፡ ድኅነት ፡ ቢሜነው ፤ መሬቱን ፡ ሽጦ ፡ ተወላጆቹን ፡ ርስቲ ፡ እንዳያገኙ ፡ ማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ አይደለምና ። በሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ማንኛውም ፡ የተራበ ፡ ወይም ፡ የተጠማ ፡ ሰው ፡ እህል ፡ እና ፡ ውሀ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ ርስት ፡ መግዛት ፡ የለበትም ። ምክንያቱም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ልጆቹንና ፡ ሚስቱን ፡ ሊረሳ ፡ ብዙ ፡ ስሕተትም ፡ ሊሠራ ፡ ይችላልና ፤”[80] ሲል ፡ ሕጉ ፡ ይደነግጋል ።

ይህ ፡ ርስቲንም ፡ ሆነ ፡ ጽልሚን ፡ የመሸጥ ፡ ጉዳይ ፡ ሌላ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ጉዳይን ፡ ያስታውሳል ። ይኸውም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ የሆነን ፡ ርስት ፡ ይዞታ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእጅ ፡ በማድረግና ፡ ግብሩንም ፡ በመክፈል ፡ ባለቤትነቱን ፡ በይርጋ ፡ የማግኘት ጉዳይ ፡ ነው ።

በሰራዬ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ “ባዕድ” የሆነ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ማሳ ፡ ሊያርስ ፡ የሚችለው ፡ በባለርስቶቹ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ “በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ለሚደርሱ ፡ የነፍስ ፡ ግድያዎች ፣ ዘረፋዎች ፣ ወይም ፡ ቅሚያዎች ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖር ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ ባለርስቶቹ ፡ እንጂ ፡ ባዕዳኑ ፡ ስላልሆኑ ፡ ”[81] ነው ። አስፈላጊው ፡ ፈቃድ ፡ ከተገኘ ፣ ባዕድ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ “ለም ፡ መሬት”፣ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ “ጠፍ ፡ መሬት” የማረስ ፡ መብት ፡ ያገኛል ። (ሕጉ ፡ እዚህ ፡ ላይ፡ በግልጥ፡ ባይናገርም) በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ መሬቱን ፡ ይዞ ፡ ለማቆየት ፡ ሲፈልግ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅና ፡ ማግኘት ፡ ያሻዋል ።

ባዕዳኑ ፡ “ምንም ፡ እንኳን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ እዚያው ፡ ቢኖሩም” በሚያርሱት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ ሊያገኙበት ፡ አይችሉም ።[82] እንዲያውም ፡ በባለርስቶቹ ፡ ፈቃድ ፡ ያገኙት ፡ ማሳ ፡ ከመንደሩ ፡ ወጭ ፡ (ከበረካ) የሚገኝ ፡ በባለ ፡ ርስቶቹም ፡ ታርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ሲሆን ፣ ባዕዳኑ ፡ ዋስትና ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ። ይህን ፡ የያዙትን ፡ ማሳ ፡ ባለርስቶቹ ፡ እራሳቸው ፡ ለማልማት ፡ በሚወስኑበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለቀው ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ይገደዳሉ ።[83]

በርግጥ ፡ አንድ ፡ ባዕድ ፡ አንድን ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ለመግዛትና ፡ ባለርስትም፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። (ርስቱም ፡ ምድሪ ፡ ወርቂ ፣ በገንዘብ ፡ የተገዛ ፣ ተብሎ ፡ ይጠራለታል ።) ሆኖም ፡ ሺያጩ ፡ የሚጸናው ፡ በሀገሩ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ የሚገባቸው ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ እንዳይሸጥ ፡ ለማድረግና ፡ ተስፋ ፡ ለማስቆረጥ ፡ የታቀዱ ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡ ያለባቸው ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ በሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክተው ፡ ይገኛሉ ። ሲኞር ፡ አስቲኒም ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተለው ፡ ባጭሩ ፡ ይገልጿቸዋል ፡-

“አንድ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ የሆነ) ርስት ፡ ሺያጭ ሊጸና ፡ የሚችለው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

---

80. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፰ና ፡ ፳፩ ።
81. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፣ “የውጭ ፡ ሰዎች” ፡ “በሀገር ፡ ተቀማጭ ፡ ስለመሆንና ፡ ሀገርን ፡ ስለመልቀቅ” ፡ በሚል ፡ ስር ።
82. ከዚያው ።
83. ከዚያው ።

፭/ ሽያጩ ፡ በገዢና ፡ በሻጭ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ በተመረጠ ፡ ዳኛ ፡ (የመንደር ፡ ዳኛ) ፊት ፡ ተከናውኖ ፡ እንደሆነ ፤

፮/ ሻጩ ፡ የሚከተሉትን ፡ ነገሮች ፡ በማረጋገጥ ፡ ዋስ ፡ የሚሆነው ፡ (አብዛኛ ውን ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ) ሰው ፡ ለማቅረብ ፡ ይችል ፡ እንደሆነ ፤

ሀ/ ሻጩ ፡ ለሚሸጠው ፡ (ርስት ፡ እርግጠኛው) ባለቤት ፡ መሆኑን ፡

ለ/ በቅድሚያ ፡ ለመግዛት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ተጠይቆ ፡ ሊገዛ ፡ አለ መፍቀዱንና ፡

ሐ/ የሺያጩ ፡ ውል ፡ ወደፊት ፡ የፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ዋጋው ፡ ተመላሽ ፡ መሆ ኑን ፤

፯/ ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ በያመቱ ፡ የሚያበረክተው ፡ የምግብ ፡ ወይም ፡ የጥራጥሬ ልክ ፡ ተገልጾ ፡ እንደሆነ ፤

፰/ ዋሱ ፡ ዋስ ፡ በመሆኑ ፡ በየዓመቱ ፡ የሚከፈለው ፡ የጥራጥሬ ፡ መጠን ፡ ተገ ልጾ ፡ እንደሆነ ፤

፱/ ሁለቱ ወገኖች የሺያጩን ፡ ውል ፡ ሲዋዋሉ ፡ ከዳኛውና ፡ ከዋሱ ፡ ሌላ ፡ ከአ ምስት ፡ ያላነሱ ፡ ምስክሮች ፡ ተገኝተው ፡ እንደሆነ ፤"[84]

ሕፃናት ፡ ምስክር ፡ ለመሆን ፡ ቢችሉም ፤ ሊመሰክሩ ፡ የሚችሉበት ፡ "ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሲሆኑ" ብቻ ፡ ነው ።[85] በአንዳንድ ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ ለመሬት ፡ ሺያጭ ፡ ውል ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑት ፡ ቄስ ፤ እስላምና ፡ ባለእጅ ፡ ናቸው ። የመጨረሻዎቹ ፡ ሁለቱ ፡ በምስክርነት ፡ መገኘት ፡ "በርስት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጥቅም ፡ የሌላቸውን ፤ ሊቃወሙት ፡ የማይቻል ፡ የእውነተኞች ፡ ሰዎችን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ . . ."[86] ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ የሆነን ፡ ርስት ፡ የመሸጥ ፡ ጉዳይ ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ በያመቱ ፡ ሊያከብረው ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ የሚ ያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ይገነዘቧል ። ይህ ፡ ልማድ ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ ሻጩ ፡ የመ ሬቱ ፡ ባለቤት ፡ እንደነበረ ፡ ሲያስታውስ ፡ ይኖራል ።

ለሻጩ ፡ ዘመዶችም ፡ የተደረጉትን ፡ ልዩ ፡ የመከላከያ ፡ ዘዴዎች ፡ እዚህ ፡ ላይ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። አንድ ፡ የሻጭ ፡ ወንድም ፡ ከሌላ ፡ ሀገር ፡ በመኖሩ ፡ ሽያጩን ፡ ሳያውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ "በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የራሱን ፡ ርስት" ፡ ከገዢው ፡ ላይ ፡ ሊያስመልስ ፡ ይችላል ።[87] ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ "ወንድም ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ርስቱ ፡ ሲሸጥ ፤ (በገዢው) ሲታረስና ፡ ሲለማ ፡ እያየ ፡ ሳይቃወም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የማስመለስ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።"[88]

---

84. አስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ ።
85. ከዚያው ።
86. ናዶል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱ ።
87. የሥራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቱ ፡ ደንቦች"፡ በሚለው ፡ ስር ። ይህም ፤ "ርስት ፡ በሺህ ፡ ዓመቱ ፡ ለባለቤቱ፡" ከሚለው ፡ የአማራ ፡ ምሳሌያዊ፡ አነጋገር ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ። "አንድ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡" ሲባልም ፡ "እስከ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ" ለማለት ፡ ነው ።
88. ከዚያው ።

አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ የመሬቱን ፡ ይዞታ ፡ ጥንት ፡ በግዢ ፡ መልክ ፡ በእጁ ፡ ካገባ ፡ በኋላ ፡ በስሙ ፡ በመገበር ፡ በይርጋ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሆነውን[89] ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ፡ ቢባልም ፤ አንድ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ በስሙ ፡ ግብር ፡ በመክፈል ፡ የዘመዶቹ ፡ ድርሻ ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ሊይዝና ፡ ባለ ቤት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ይህም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ተገለጸው ፡ የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሚይዘው ፡ "ቤተ ፡ ሰቡ" ፡ ባለው ፡ መብትና ፡ የዚህም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይዞታ ፡ ከሌለው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ፡አባል ፡ የሚበልጥ ፡ መብት ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ የለውም ፤ ሊኖረውም ፡ አይችልም ።

ሆኖም ፡ በየሥፍራው ፡ የሚገኘውን ፡ የልማድ ፡ ልዩነት ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። በሎጎ ፡ ጭዋ ፤ ከመንደር ፡ ውስጥ ፡ አለመኖር ፡ በርስት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መብትን ፡ እስከ ማሳጣት ፡ ያደርሳል ።[90] ይህንንም ፡ በሚቀጥለው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ እንመለከተዋለን ።

ጽልሚና ፡[91] ርስቲ ፡[92] በሚገኙባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አስሃባ ፡ የተባለ ፡ ስርዓት ፡ ሲሠራበት ፡ ይታያል ። አንዱ ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማው ጥቅምን ፡ ማደላደል ፡ ሲሆን ፤ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ማሣዎች ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ይከፋፈላሉ ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከሌሎች ፡ የሚበልጥ ፡ ማሳ ፡ ይዘው ፡ ሲገኙ ፡ (ለምሳሌ ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ) ወይንም ፡ "ለአዲስ" ጠያቂ ፤ ድርሻ ፡ ለመስጠት ፡ ከሚገኙት ፡ ማሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ማዋጣት ፡ ሲያስፈልግ ፡ (ለምሳሌ ፡ በሰራዬ) ነው ።

(ለ) ስለመንደር ፡ ርስት ፤

፩/ አመጣጡ ፤

"የመንደር ፡ የርስት ፡ ባለቤትነት" እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ፡ የሚገኘው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤ ርስቲ ፡ ከሚባለው ፡ ከዘር ፡ ርስት ፡ ስሪት ፡ የመጣ ፡ ለመሆኑ ፡ ደራሲዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣሉ ።[93] ይህም ፡ አስተያየት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስትን ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ርስት ፡ መለወጥ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ በሚቀበሉት ፡ በሎጎ ፡ ጭዋና ፡[94] በሰራዬ ፡[95] የልማድ ፡ ሕጐች ፡ የተደገፈ ፡ ነው ።

89. ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ርዕስ ፡ ነው ። ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ፤ ዩሱካፕሽን ፡ ኦፍ ፡ ፋሚሊ ፡ ላንድ ፡ አንደር ፡ ኢትዮፕያን ፡ ሎው ፤ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም. ያልታተመ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፤ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።)
90. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፭፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
91. ከዚያው ።
92. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቲ ፡ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ስር ።
93. ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ ። አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፲፫ ፡ ይመለከቷል ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የስሪት ፡ ለውጥ ፡ በትግሬ ፡ ውስጥም ፡ ታይቷል ። ዘገየ ፡ አስፋውና ፡ ጠዓመ፡ በየነ ፤ ሪፖርት ፡ ኦን ፡ ትግሬ ፡ ፕሮቪንስ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፫ - ፬ ።
94. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፭፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
95. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቲ ፡ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ሥር ። ይህ ፡ የመንደር ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ በሐማሴንና ፡ ሰራዬ ፡ "ዴሳ" ፡ ተብሎ ፡ ሲጠራ፤ በአካለ ፡ ጉዛይ ፡ ደግሞ ፡ "ሸኽና" ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ጥንት ፡ ባለርስት ፡ ከነበረ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በመወለዳቸው ፡ ድርሻ ፡ ማሳ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ርስተኛታት ፡ ተብለው ፡ ሲጠሩ ፡ አዲስ ፡ መጭዎቹ ፡ ግን ፡ ማዕከላይ ፡ አልየት ፡ (ሲተረጐም ፡ ባዕዳን ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡) ተብለው ፡ ይጠራሉ።

ይህ ፡ የስራት ፡ ለውጥ ፡ የተደረገበትን ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ፡ ስለማይቻል ፣ ግምት ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ ግድ ፡ ይሆናል ። ሲኞር ፡ አስቲኒ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ የተጀመረው ፡ "የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሜትን" ፡ ለማጠንከርና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖርም ፡ ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡ ነው ፤ ሲሉ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ።[96] ይህም ፡ በመንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ ውስጥ ፡ ለርስተኞታት ፡ የተለየ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስረዳ ፡ ይመስላል ። እንዳጋጣሚ ፡ ሆኖ ፣ ርስተኞታት ፡ የሚለውም ፡ ስያሜ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ ከዘር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ ለመመንጨቱ ፡ አንድ ፡ ድጋፍ ፡ ይሆናል ።

ይህን ፡ የሲኞር ፡ አስቲኒን ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ አጠቃላይ ፡ መግለጫ ፡ አድርጎ ለመቀበል ፡ የሚያስቸግር ፡ አንድ ፡ እንቅፋት ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ አንድ ፡ ባዕድ ፣ ማለትም ፡ የመንደር ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ከመንደሩ ፡ ርስት ፡ ተገቢ ፡ ድርሻውን ፡ ሊያገኝ ፡ መቻሉን ፡ ስናስታውስ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ አቋም ፡ የሆነውን ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ስሜት ፡ የማጠንከሩ ፡ ጉዳይ ፡ ቦታ ፡ እንደሌለው ፡ እንገነዘባለን ። እርግጥ ፡ በሲኞር ፡ አስቲኒ ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፣ በቅርቡ ፡ አንዳንድ ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ዘመዳሞች ፡ በስምምነት ፣ ይተዳደሩበት ፡ የነበረውን ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ስራት ፡ ወደመንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ የለወጡት ፡ ነው ። ከዚህ፡ ላይ ፡ ሳንጠቅሰው ፡ የማናልፈው ፣ ኢጣሊያኖች ፡ ኤርትራን ፡ ይገዙ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ የነበሩትን ፡ የአንዳንድ ፡ ቀበሌ ፡ ስራቶች ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ የለወጡትን ፡ ነው ።[97] እንግዲህ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፣ የዘርን ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ የርስት ፡ ስራት ፡ ሲለውጡት ፡ የነበራቸው ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ ባይታወቅም ፣ የመንደር ፡ የመሬት ፡ ስራት ፡ አሁን ፡ የምንመረምራቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ዋነኛ ፡ የስራት ፡ ዓይነት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

<u>፪/ ስለእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የአከፋፈል ፡ ሥርዓትና ፡ ግለ ፡ ሰቡም ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ የመብት ፡ ዓይነቶች ፤</u>

የመካፈል ፡ መብት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚፈጸመውን ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ የማደላደል ፡ ስርዓትን ፡ የሚያህል ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ምናልባት ፡ አይኖር ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ከዚህ ፡ በየጊዜው ፡ ከሚደረገው ፡ የመሬት ፡ ማከፋፈል ፡ ስርዓት ፡ ይበልጥ ፡ የ"አንድነትን" ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ። የሎጎ ፡ ጭዋን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ በማድረግ ፡ ይህን ፡ ሥርዓት ፡ ቀጥለን ፡ እናስረዳለን ።

የመንደሩን ፡ መሬት ፡ ለመንደረተኞቹ ፡ የማከፋፈሉ ፡ ተግባር ፡ የሚከናወነው ፡ ከያንዳንዱ ፡ <u>ማርቤት</u> ፡ (ቤተሰብ) ፡ በተውጣጡ ፡ በስድስት ፡ አዋቂ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሲሆን ፣ የሚሰየሙት ፣ የሚመረጡትም ፡ በመንደሩ ፡ ዳኛ ፡ ነው ።[98] ሽማግሌዎቹ ፡ በሁለት ፡ ቡድን ፡ ተከፍለው ፡ ተግባራቸውን ፡ ያከናውናሉ ።

---

96. አስቲኒ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፣ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ ።

97. ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሁሉ ፣ ይህ ፡ እርምጃ ፡ የተወሰደው ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ባላቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ሲል ፣ ኢጣሊያኖችን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የማስፈር ፡ እቅድ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ስለነበር ፡ የማስፈሩን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ መሬት ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። የተባለውን ፡ መሬት ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ በኤርትራ ፡ እንዲሁም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፣ የነበረውን ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ሁኔታ ፡ በተሳሳተ ፡ መልክ ፡ በመመልከት ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እር ፡ ፓንክርስት ፡ "ኢታሊያን ፡ ሴትልሜንት ፡ ፖሊሲ ፡ ኢን ፡ ኤርትሪያ ፡ ኤንድ ፡ ኢትስ ፡ ሪፐርከርሽንስ ፡ ፲፰፻፹፱-፲፰፻፺፯" ፡ <u>በስቶን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፔፐርስ ፣ ፩ኛ</u> ፡ እትም ፣ ከገጽ ፡ ፩፻፴፩ ፡ ጀምሮ ፡ ይመለከቷል ።

98. <u>የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ</u> ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፬ ፡ የተጠቀሰው ፣ አንቀጽ ፡ ፲፬ ።

ጊላፎ ፡ (አጣሪዎች) የሚባለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ቡድን ፡ ተግባር ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ የመካፈል ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ መለየትና ፡ ከዚህ ፡ በፊትም፡ ተገቢ ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ መሬት ፡ ይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ ምንም ፡ እንዳይሰጠው ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ አቋሮ ፡ (ጠባቂ ፡) ወይም ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ አቋሮ ፡ መሬት ፡ (የመሬት ፡ ጠባቂ ፡) ተብሎ ፡ ይጠራል ።[99] ክፍያ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቡድን ፡ የመንደሩን ፡ ማሳዎች ፡ በሙሉ ፡ በቁጥጥሩ ፡ ሥር ፡ በማ ድረግ ፡ ሁለት ፡ ነገሮችን ፡ ይፈጽማል ። አንደኛ ፡ "መጠባበቂያ ፡ "የእርሻ ፡ መሬትንና፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ለይቶ ፡ ማስቀመጥ ፤ መጠባበቂያ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ መቀመጡም ፡ የመሬቱ ፡ ክፍያ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ ለሚመጡ ፡ የመንደሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሲሆን ፤ ሌላ ፡ ክፍያ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ የመሬት ፡ ችግር ፡ እንዳይገጥማቸው ፡ ለማድረግ ፡ነው ። ሁለተኛም ፡ የመንደሩን ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ እያደ ረጉ ፡ በሚከፈለው ፡ ሰው ፡ ቁጥር ፡ በማከፋፈል ፡[100] ዕጣ ፡ እያወጡ ፡[101] እያንዳንዱን ፡ ማሳ ፡ ዕጣ ፡ ለወጣለት ፡ ሰው ፡ ማደል ፡ ነው ።

የዚህም ፡ የማሳ ፡ ማከፋፈል ፡ ስም ፡ ዋርየዳ ፡ (ቀጥተኛ ፡ ትርጉሙ ፡ ግመታ) ፡ ሲሆን ፤ የሚፈጸመውም ፡ በየስምንቱ ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። "ክፍያው ፡ በየስ ምንት ፡ ዓመት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ገበሬዎች ፡ የእርሻ ፡ መሬታቸውን በሚገባ ፡ ለማልማት ፡ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ይበቃቸዋልና ፡ ነው ።"[102] ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ማከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ የተዘጋጁ ፡ ማሳዎች ፡ ለሰነፎች ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ። ገበሬው ፡ "የዝ ናሙ ፡ ጊዜ ፡ ሳያልፍበት" የእርሻ ፡ መሬቱን ፡ ለማዘጋጀት ፡ እንዲችል ፡ ዋርየዳ ፡ የሚ ፈጸመው ፡ ከነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ ፳፩ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።"[103]

ለዚህ ፡ ክፍያ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፤ ትዳራቸውን ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ያቋ ቋሙ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ማሳ ፡ ያገኛሉ ፤ የሚለው ፡ ነው ። ይህም ፡ ሕግ ፡ በተለይ ፡ ተፈ ጻሚነት ፡ ያለው ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ለመቋቋም ፡ የፈ ለገ ፡ እንደሆን ፤ በመጀመሪያ ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆነው ፡ ጎጆ ፡ ለራሱ ፡ መሥራት ፡ አለ

---

99. ከዚያው ።

100. "የሚከፋፈለው ፡ ማሳ ፡ ቍጥር ፡ የሚወሰነው ፤ የኢኰኖሚ ፡ ነፃነት ፡ ባገኙት ፡ ሰዎች ፤ ሕጋዊ ፡ ልጆች፡ ባሏቸውና ፡ ባሎቻቸው ፡ በሞቱባቸው ፡ ሴቶች ፤ የአባቶቻቸውን ፡ መኖሪያ ፡ መንደር ፡ ለቀው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ በመመለስ ፡ ኗሪነታቸውን ፡ በዚያው ፡ ባደረጉ ፡ ሴቶችና ፡ ክርስቲ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲ ያገኙ ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ማዕከላይ ፡ አልየት ፡ (ባዕዳን) ፡ ቍጥር ፡ ነው ።" ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ቍጥሮች ፡ የተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ፤ አንድን ፡ ድርሻ ፡ በጭሰኝነት ፡ ወይንም ፡ በሌላ ፡ መልክ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይቻላል ። የሚች ፡ ድርሻ ፡ ግን ፡ ለሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።

101. በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ የዕጣ ፡ ማውጣት ፡ ሥርዓት ፡ የሚታየው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ነው ። የመንደር ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ (እንደተገነዘብነውም ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ የሚታደለው ፡ በዕጣ ፡ ነው፡) በተከፋፋዮቹ ፡ ቁጥር ፡ ልክ ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ ከተሸነሸነ ፡ በኋላ ፡ የመንደሩ ሽማግሌዎች ፡ ትናንሽ ፡ ስንጥሮችን ፡ ሰብስበው ፡ በመያዝ ፡ በየማሳው ፡ ይሰይሟቸዋል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በሁለት ፡ እጆቹ ፡ ለመያዝ ፡ የሚችለውን ፡ ያህል ፡ ከስንጥ ሮቹ ፡ አንስቶ ፡ ከፍ ፡ ያደርግና ፡ "የሐዋርያት ፡ ዕጣ ፤ ለእውነተኛው ፡ ባለቤት ፡ ውጣ፡" ብሎ ፡ በመናገር፡ ለያንዳንዱ ፡ ተካፋይ ፡ አንዳንድ ፡ ስንጥር ፡ ይሰጣል ። እያንዳንዱም ፡ ተካፋይ ፡ ባገኘው ፡ ስንጥር ፡ የተሰ የመውን ፡ ማሳ ፡ ይወስዳል ። በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ- ም- የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ ለነበረው ፡ ለአቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ።

102. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

103. ከዚያው ።

በት ። ጐጆ ፡ ለመሥራትም ፡ የሚችለው ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ በታዎችን ፡ ለማደላ ደል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ሦስቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የፈቀዱለት ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኗሪ ፡ ሆኖ ፡ "ተቋቋ ሚል ፡" ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ "ለራሱ ፡ ቤት ፡ በመሥ ራት ፡ ብቻ ፡" አይደለም ።[104] የቤት ፡ መሥሪያ ፡ በታዎችን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ (እነዚህም ፡ ሽማ ግሌዎች ፡ ዘመን ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ በማደጉ ፡ የውጭ ፡ ሰዎችን ፡ የመቀበል ፡ ፍላጐታቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄዷል ።)"[105] በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ መንደረተኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ። "በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኗሪ ፡ ሆኖ ፡ መቋቋም ፡ ማለት ፡ ጐጆ ፡ ሠርቶ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ከውስጡ ፡ መቀመጥ ፡ አይደ ለም ። ከዚያ ፡ መኖርና ፡ መንደረተኛ ፡ የሚጠበቅበትንም ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባል ። የአንድ ፡ መንደረተኛ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ርስት ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ከመንደሩ ፡ ዳኛ ፡ ወይንም ፡ ከዘመዶቿ ፡ ፈቃድ ፡ ሳታገኝ ፡ ከመንደሩ ፡ መውጣት ፡ የለባትም ።[106]

ይህንንም ፡ ግዴታ ፡ አለማክበር ፡ በዋርየዳ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ በተካፈሉት ፡ ማሳ ፡ ላይ ፡ የተገኘን ፡ መብት ፡ እስከ ፡ ማሳጣት ፡ ያደርሳል ።[107]

ሲኞር ፡ አስቲኒ ፡ እንደገለጡት ፡ "<u>የማዕከላይ ፡ አልየት</u> ፡ (የውጭ ፡ ሰዎች ፡) አቋ ም ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ፡ ነው - - - ። ለብዙ ፡ ትውልድ ፡ ያህል ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የኖሩና ፡ ለብዙ ፡ ዘመናትም ፡ ያህል ፡ የርሻ ፡ መሬት ፡ የያዙ ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ራሳቸውን ፡ ከርስተኞች ፡ (ማለትም ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ ባለርስቶች ፡ ከነበሩ ፡ ሰዎች) ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ አይገምቱም ። ---ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በኋ ላም ፡ እንኳ ፡ ከመንደሩ ፡ የተለየ ፡ አኗኗር ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ።"[108] አስቲኒ ፡ ይህን ፡ ሲናገሩ ፡ የተባሉት ፡ "የውጭ ፡ ሰዎች" በመንደሩ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የመሪነት ፡ ሥል ጣን ፡ እንደሌላቸው ፡ ለማመልከት ፡ ነው ። መዘንጋት ፡ የሌለበት ፡ ለብዙ ፡ ትውልድ ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ የኖረ ፡ "የውጭ ፡ ሰው ፡" ልጅ ፡ እንኳን ፡ ለርሻ ፡ የሚሆን ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ አስቀድሞ ፡ ራሱን ፡ የመንደሩ ፡ ኑዋሪ ፡ አድርጐ ፡ ማቋቋም ፡ እንደሚያስ ፈልገው ፡ ነው ።

ይህ ፡ የመቋቋም ፡ ግዴታ ፡ ግን ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ እጩ ፡ በመሆን ፡ ሊቀርቡ ፡ በሚችሉ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፤ ማለትም ፡ በቅርቡ ፡ የተጋቡ ፡ የመንደሩ ፡ ርስተኞች ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፤ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።[109] የአባቶ

---

104. ሠይፉ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፤ <u>ኮንሶሊዴሽን ፡ ኦፍ ፡ ፍራግሜንትድ ፡ ሆልዲንግስ ፡ ኢን ፡ ከሚውናል ፡ ቴን የር ፡ ኤርያስ</u> ፡ (፲፱፻፷፯ ፤ ያልታተመ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ።
105. ከናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ ከተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።
106. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
107. ከዚያው ።
108. አስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፰-፺፬ ።
109. "አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ የተለየ ፡ የራሱን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በሚያቋቁምበት ፡ ጊዜ ፡ ማሳ ፡ ይሰጠዋል ። ጭቃውና ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ በሚገኙበት ፡ የልጁ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ለመቋቋሚያው ፡ የሚሆነውን ፡ ይሰጡታል ፤ (ያደርጉለታል) ፡" ከሚለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ። የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ልማ ዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፭ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፻፵፪ ።

ቻቸው ፡ "መቋቋም" ፡ ለእነርሱም ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ ይመስላል ።[110] ስለዚህም ፡ ሚስት ፡ ካገቡ ፣ ከመንደሩ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ማሳዎችን ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ። "የውጭ ዎቹም ፡ ሰዎች ፡" ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲሁ ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ይኖርባቸዋል ።

የሴት ፡ ልጅ ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ልጆችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ሁሉ ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ በመሆን ፡ "ሊቋቋሙ ፡" የሚችሉ መሆናቸውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ።[111]

ዋርየዳ ፡ ሲደረግ ፡ መመሪያው ፡ "እኩልነት ፡" እንጂ ፡ ከኢኮኖሚ ፡ የሚገኘው ፡ ሀብትና ፡ ብልጽግና ፡ አይደለም ። "በሂሳብ ፡ ረገድ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ (የርስት ፡) መከፋፈል ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ የመንደሩ ፡ ማሳ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ለምነቱ ፡ በዓይነት ፡ በዓይነቱ ፡ ተሸንሽኖ ፡ ይመደባል ። በብዛት ፡ በሚሠራበት ፡ ስነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የመሬት ፡ አመዳደብ ፡ እናገኛለን ፤ (ለም ፤ ለም ፡ ጠፍና ፡ ጠፍ) ዕጣም ፡ የሚወጣው ፡ ለያንዳንዱ ፡ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፣ ገበሬውም ፡ ከየዓይነቱ ፡ አንዳንድ ፡ ማሳ ፡ ይቀበላል ።"[112]

ይህ ፡ በየጊዜው ፡ የሚደረገው ፡ የርስት ፡ ማከፋፈል ፡ ሥርዓት ፡ የርስት ፡ ሽያጭን ፡ እንደሚያግድ ፡ በትክክል ፡ ከዚህ ፡ በቀደም ፡ ተገልጿል ።[113] ነገር ፡ ግን ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ ሊሸጥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ከመናገር ፡ ይልቅ ፣ ጥንት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስላልተገኘ ፡ የመሬት ፡ ሺያጭ ፡ አይታወቅም ፤ ብሎ ፡ መናገሩ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ።[114] ሆኖም ፡ መሬት ፡ በኪራይ ፡ ሊሰጥ ፡ መቻሉን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ። ለምሳሌም ፡ አንዲት ፡ ከመንደር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የተቀበለች ፡ ሴት ፡[115] ራሷ ፡ ለማረስ ፡ ስለማትችል ፡ "ጉልበትና ፡ በሬ ፡"[116] ላለው ፡ ሰው ፡ በኪራይ ፡ አሳልፋ ፡ ልትሰጥ ፡ ትችላለች ።

ሐ/ <u>በሌሎች ፡ የቤተ ፡ ሰብና ፡ የመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ ግላዊ ፡ መብቶች፤</u>

፩/ <u>በመንገዶች ፣ በቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችና ፣ ለመጠባበቂያ ፡ በተወሰኑ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ መብት ።</u>

የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡[117] የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግም[118] ፡ የትላልቅ ፡ መንገዶችን ፡ (<u>መንገድ ፡ አርብዓ)</u> ፡ ስፋት ፡ ወስኖ ፡ ይደነ

110. ነገር ፡ ግን ፡ የሚከተለውን ፡ ይገነዘቧል ። "(ዱሳ ፡ ወይንም ፡ ሸኽና ፡ ከሚለው ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ውስጥ ፡) ድርሻ ፡ ማሳ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ በመኖር ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ እንደተወላጅነት ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ከግምት ፡ አይገቡም" ። (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ፡ አምኃ ፡ ጽዮን ፡ ዶሚኒኮ ፣ አሎኬሽን ፡ ኦፍ ፡ ኮንሶሊዴትድ ፡ ዩኒትስ ፣ ኢንዲቪጁያል ፡ አርኬሚውናል) ፣ ፲፱፻፷፯ ፣ ያልታተመ ፣ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ገጽ ፡ ፳፰። ጥንት ፡ ባለርስት ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠቅም ፡ ቀደም ፡ ስንል ፡ ተመልክተናል ።

111. ከአምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፲፰ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

112. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፣ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፲፫ ።

113. ላውረንስና ፡ ማን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፭ ።

114. ከቢንቲ ፡ ኢንቺል ፡ "ዱ ፡ አፍሪካን ፡ ሲስተምስ፡ኦፍ፡ላንድ፡ቴንየር፡ሪኳየር፡ኤ፡ስፔሺያል ፡ ተርሚኖሎጂ?" ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው ፣ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ (፲፱፻፷፩) ፣ ከገጽ ፡ ፩፻፴፯-፩፻፴፱ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

115. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

116. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፱ ። "ነዋሪ" ፡ የመሆኑ ፡ ግዴታ ፣ ሁለት ፡ ማሳዎችን ፡ በስውር ፡ በተለያዩ ፡ በሁለት ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ከመያዝ ፡ ማገዱን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ ከሁለት ማሳዎች ፡ አንዱን ፡ ለመሸጥ ፡ ሲኖር ፡ የሚችልን ፡ ምኞት ፡ ይቀንሰዋል ።

117. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰ ፣ "መንገዶችን ፡ የሚመለከቱ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ሥር ።

118. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ አንቀጽ ፡ ፳፮ ።

ግጋል ። መንገዶችን ፡ በሚገባ ፡ ለመያዝና ፡ ለመጠገን ፡ ኀላፊዎቹ ፡ መንደረተኞቹ ፡ ብቻ ፡ ቢሆኑም ፡ የውጭ ፡ ሰውም ፡ ሆነ ፡ መንደረተኛ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ይችላል ።[119] በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ መንገዶችን ፡ ማረስ ፣ ቋጥኝ ፡ ድንጋዮችን ፡ ወይንም ፡ ግንዲላ ዎችን ፡ በመንገዶች ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ ወንጀል ፡ ነው ።[120]

ከመንደር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ ቤት ፡ መሥራትና ፡ ባለቤትም ፡ መሆን ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፣ ቤቶችንና ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ የመቆጣጠሩ ፡ ጉዳይ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ነው።

ስለዚህም ፡ የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎች ፡ አቀማመጥ ፣ ለየሰዉ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቦታ ፡ ልክ ፣ ስለ ፡ አማካይ ፡ የወሰን ፡ አጥሮች ፡ ስለቤት ፡ ውርስና ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ የቤቶች ፡ ፕላን ፡ ሰፋ ፡ ያሉ ፡ ደንቦችን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። "ከስድስት ፡ መደዳ ፡ ቤቶች ፡ በኋላ ፡ መንገድ ፡ መኖር ፡ አለበት ።"[121]

አስፈላጊውን ፡ ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ የሰራ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፣ መቀጫ ፡ ከፍሎ ፡ እንዲለቅ ፡ ይገደዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቤቱን ፡ የሠራው ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ ከሆነ ፡ በርስተኛታት ፡ እንዲለቅ ፡ ሲገደድ ፣ ቤቱ ፡ የተሠራበትን ፡ የጣራ ፡ የማገሩን ፡ እንጨት ፡ ይዞ ፡ ለመሄድ ፡ መብት ፡ አለው ። ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ ቤት ሠርቶ ፡ ወይንም ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ወደሌላ ፡ መንደር ፡ ለመዛወር ፡ ፈልጎ ፡ የሆነ ፡ እን ደሆነ ፡ የጣራ ፡ ማገሩ ፡ እንጨት ፡ ለርስተኛታት ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።[122] የአባ ቱን ፡ ቤት ፡ የሚወርሰው ፡ ልጅ ፡ ከመጀመሪያዋ ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ነው ። "ምክንያቱም ፡ በቤቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነችው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሚስት ፡ ስለሆነች ፡ ከሁለተኛዋ ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ እናቱ ፡ ያልለፋችበትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ።"[123]

አዲስ ፡ የተጋቡ ፡ ሙሽሮች ፡ ለቤት ፡ መሥሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ የሚያገኙት ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ከተቀመጠው ፡ መሬት ፡ ሲሆን ፣ በውስጡም ፡ የርሻ ፡ መሬት ፣ ለመን ደረተኞች ፡ ያልታደለ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታና ፡ ለአደን ፡ የተከለለ ፡ መሬት ፡ ይገኙበታል ። በባለርስተኞቹ ፡ ፈቃድ ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ በኪራይ ፡ መልክ ፡ የሚገኘውን ፡ መሬት ፡ ኪራይ ፡ መንደረተኞቹ ፡ የመከፋፈል ፡ መብት ፡ አላቸው ። በተጨማሪም ፡ ዋርየዳ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ የሚመጡ ፡ አባሎች ፣ ለመጠባበቂያ ፡ ከተቀመጠው ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ የርሻ ፡ ማሳ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አላቸው ።[124]

፪/ በማርና ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ መብት ፤

በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ "ማር ፡ እምን ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ እንደሚውልና ፡ ምን ፡ እንደሚ ደረግ ፡ የሚወሰነው ፡ በየመንደሩ ፡ (ወይንም ፡) ስለመንደሩ ፡ ሆነው ፡ በሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ።"[125] በአንዳንድ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፤ ከመ

---

119. ከዚያው ።
120. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
121. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
122. ከዚያው ።
123. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
124. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፭፯።
125. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "ግጦሽን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ሥር ።

ንደሩ ፡ ውጭ ፡ የሚገኙ ፡ ሰፋፊ ፡ ቦታዎች ፡ ለከብቶች ፡ ግጦሽ ፡ በመከለል ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆን ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ "የተከለከሉ ፡" እና "የተፈቀዱ ፡" በመባል ፡ ተከፋፍለው ፡ ይጠበቃሉ ።[126]

በነዚህ ፡ የግጦሽ ፡ መስኮች ፡ ላይ ፡ እንዲሠማሩ ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ የመንደሩ ፡ ከብቶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

የዘርም ፡ ሆነ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌ ፡ ሁሉ ፡ ዛፎች ፡ በሁለት ክፍል ፡ ተመድበው ፡ ለየብቻቸው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተበጅቶላቸዋል ። ዛፎች ፡ ባለሀብትነታቸው ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የጋርዮሽ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ለእርሻ ፡ ከተመደበለት ፡ ማሳው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚኖርበት ፡ አካባቢ ፡ ዛፍ ፡ ሊተክል ፡ ይችላል ፤ በዛፉም ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ። ስለዚህም ፡ ዛፉን ፡ ቆርጦ ፡ ለፈቀደው ፡ ማዋልና ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ እንዳይነኩት ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ "የጋርዮሽ ፡" በሆኑ ፡ ዛፎች ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ አለው ። እነዚህም ፡ ዛፎች ፡ "ከጫካ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡" የተፈጥሮ፡ ጸጋዎች ፡ ናቸው ። ሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ በጫካ ፡ የሚገኝን ፡ ዛፍ ፡ ለመቁረጥ፡ የጀመረ ፡ ሰው ፡ ዛፉን ፡ በሰላሣ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ቆርጦ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ መብት፡ አለው ፤ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሊቆርጡትና ፡ በፈቀዱትም ፡ ሊያውሉት ፡ ይችላሉ ።[127] በአንዳንድ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የጋርዮሽ ፡ የሆኑ ፡ ዛፎችን ፡ ለመቁረጥ ፡ ፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ያሻል ፤ (ይህ ፡ ለፎርማሊቲ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፤ የጠየቀ ፡ ሁሉ ፡ ይፈቀድለታል ።)[128] አንድን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማሳነጽ ፡ ሲፈለግ ፡ ግን ፤ የማንንም ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበሉ ፡ ዛፍን ፡ ቆርጦ ፡ መውሰድ ፡ ይቻላል ።[129]

፫/ ስለአውድማ

አውድማንና ፡ የእርሻ ፡ ዕቃን ፡ የሚመለከቱ ፡ የሰራዬና ፡[130] የሎጎ ፡ ጭዋ ፡[131] ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እጅግ ፡ ይመሳሰላሉ ።

የእርሻ ፡ መሣሪያዎች ፤ እንስሳትም ፡ ጭምር ፤ በሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ ፍጹም፡ የግል ፡ መብት ፡ ስር ፡ ይገኛሉ ። ሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ የባለቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበል ፡ በእርሻ ፡ መሣሪያዎቹ ፡ የሚጠቀም ፡ ሰውና ፡ የተዋሰውንም ፡ ቀንበር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የማይመልስ ፡ ሁሉ ፡ መቀጫ ፡ ይጣልበታል ።[132]

የአድከመ ፡ ምዕልግና ፡ የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ መሬት ላይ ፡ የተበጀ ፡ አውድማን ፡ የሚገምቱት ፡ እንደባለቤቱ ፡ "የግል ፡ ገንዘብ" ነው ።

---

126. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷፪-፷፫ ።
127. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፴፭-፴፪ ።
128. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷፪ ።
129. ከዚያው ።
130. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "አውድማዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች" ፡ በሚለው ፡ ሥር ።
131. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ እና፡ ፴ ።
132. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፴፬ ።

በእንዲህ ፣ ያለው ፣ አውድማ ፣ ላይ ፣ እህሉን ፣ ሊወቃ ፣ የፈለገ ፣ ሁሉ ፣ የባለቤቱን ፣ ፈቃድ ፣ አስቀድሞ ፣ መቀበል ፣ ይገባዋል ።

በሰራዬ ፣ ልማዳዊ ፣ ሕግ ፣ ስር ፣ "የጋርዮሽ ፣ አውድማ ፣" የሚባልም ፣ አለ ፤ ሆኖም ይህ ፣ የሚታየው ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ ነው ። በየምክንያቱ ፣ የተነሣ ፣ "የራሱ ፣" የሆነ ፣ አውድማ ፣ የሌለው ፣ ሁሉ ፣ መንደረተኞች ፣ በጋርዮሽ ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ ባበጁት ፣ አውድማ ፣ ላይ ፣ እህሉን ፣ ለመውቃት ፣ ይችላል ። እንዲህ ፣ ያለው ፣ አውድማ ፣ አብዛኛውን ፣ ጊዜ ፣ የሚገኘው ፣ የአንድ ፣ ሰው ፣ ሀብት ፣ ባልሆነ ፣ ኮረብታማ ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ ነው ።

እንግዲህ ፣ ከላይ ፣ በመረመርናቸው ፣ ሰፍረው ፣ በእርሻ ፣ በሚተዳደሩ ፣ የኀብረ ፣ ሰብኡ ፣ ክፍሎች ፣ ውስጥ ፣ ማንም ፣ ሰው ፣ ድርሻው ፣ የሆነውን ፣ የዘር ፣ ወይም ፣ የመንደር ፣ ርስት ፣ የሚያርሰው ፣ በራሱ ፣ መሣሪያ ፣ ነው ። አንዳንዴ ፣ ግን ፣ በሌላው ፣ የመንግሥቱ ፣ ግዛት ፣ ክፍል ፣ እንደሚደረገው ፣ ሁሉ ፣ እርሻ ፣ አጨዳ ፣ ወይም ፣ ውቂያ ፣ ሲደርስበት ፣ የጐረቤቶቹንና ፣ የመንደረተኞቹን ፣ እርዳታ ፣ በደቦ ፣ መልክ ፣ መጠየቁ ፣ አይቀርም ።[133]

የኀብረ ፣ ሰብኡ ፣ አባሎች ፣ በሌሎች ፣ የጋራ ፣ መሬቶች ፣ ዓይነት ፣ ማለት ፣ በመንገዶች ፣ በቤት ፣ መሥሪያ ፣ ቦታዎች ፣ በጫካዎች ፣ እና ፣ በግጦሽ ፣ ላይ ፣ ያላቸውን ፣ መብት ፣ መርምረናል ፤ ካደረግነውም ፣ ምርመራ ፣ የየሰዉ ፣ አጠቃቀም ፣ "የግል ፣" መሆኑን ፣ ተገንዝበናል ።

ከዚህ ፣ በፊት ፣ እንደተገለጠው ፣ ከላይ ፣ በመረመርናቸው ፣ የክርስትናን ፣ ሃይማኖት ፣ በሚከተሉ ፣ የኀብረ ፣ ሰብኡ ፣ ክፍሎች ፣ ውስጥ ፣ "አባሎቹ ፣ በመሬት ፣ ሲጠቀሙ ፣ በጋርዮሽ ፣ ነው" ፣ የሚል ፣ የተሳሳተ ፣ አስተያየት ፣ ያላቸው ፣ ሰዎች ፣ የኀብረ ፣ ሰብኡን ፣ የመሬት ፣ ስሪት ፣ ለመግለጥ ፣ ከሚገለገሉባቸው ፣ ስያሜዎች ፣ "ኮሙናል ፣ ሬጅም ፣" የሚለው ፣ ይገኝበታል ። --- "መሬት ፣ በጋርዮሽ ፣ አይታረስም ። እያንዳንዱ ቤት ፣ ሰብ ፣ ወይም ፣ አባል ፣ የራሱ ፣ የሆኑ ፣ ማሳዎች ፣ አሉት ፤ ያርሳቸዋልም ።"[134] በነዚህ ፣ ክፍሎች ፣ ውስጥ ፣ "የጋራ ፣ (የተራድኦ ፣) እርሻ"ን ፣ የሚመስል ፣ ዝግጅት ፣ የሚታየው ፣ አባት ፣ እናትና ፣ (ብዙውን ፣ ጊዜ) ያላገቡ ፣ ልጆቻቸው ፣ በአባትየው ፣ መሪነት ፣ በሚያርሱት ፣ ማሳ ፣ ላይ ፣ ነው ።[135]

መ/ ስለዘርና ፣ ስለመንደር ፣ የመሬት ፣ ስሪት ፣ ጠቃሚነት ፣ እና ፣ ጐጂነት ፣[136]

"የጋርዮሽ ፣ መሬት" (ኮሙናል ፣ ላንድ ፣) በሚለው ፣ ጉዳይ ፣ ላይ ፣ እስከዛሬ ፣ ድረስ ፣ ከተደረሱት ፣ ጽሑፎች ፣ ብዙዎቹ ፣ ስለ ፣ ስሪቱ ፣ ጎጂነት ፣ አመዝነው ፣ ስለሚገኙ ፣ በነዚሁ ፣ እንጀምራለን ።

133. ይህ ፣ እውነት ፣ መሆኑን ፣ ለማረጋገጥ ፣ ደራሲው ፣ (በሰራዬ ፣ ለኖረው) ፣ ለአቶ ፣ ዓለም ፣ ሰገድ ፣ ተስፋዬ ፤ (በሎጐ ፣ ጭዋና ፣ በአክለ ፣ ጉዛይ ፣ ለኖረው) ፣ ለአቶ ፣ ዮሐንስ ፣ ኃብተ ፣ ሥላሴና ፣ (በሐማሴን ፣ ለኖረው) ፣ ለአቶ ፣ ዑቅባ ፣ ሚካኤል ፣ ወልደ ፣ ዮሐንስ ፣ ጠለቅ ፣ ያለ ፣ የቃል ፣ ጥያቄ ፣ አቅርቦ ፣ ነበር ። በተጨማሪም ፣ (በትግሬ ፣ ጠቅላይ ፣ ግዛት ፣ በእንደርታና ፣ በአድዋ ፣ ለኖረው) ፣ ለአቶ ፣ ዮሴፍ ፣ ገብረ ፣ እግዚአብሔር ፣ ጥያቄ ፣ ቀርቦ ፣ ነበር ። የሁሉም ፣ መልስ ፣ የማያወላውል ፣ ተመሳሳይ ፣ ነበር ። (ጥያቄዎቹ ፣ የቀረቡት ፣ በጥቅምት ፣ ወር ፣ ፲፱፻፷ ፣ ዓ- ም- ላይ ፣ ነበር ።)
134. አምባዬ ፣ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፣ በማስታወሻ ፣ ቍጥር ፣ ፱ ፣ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፣ ፲፬ ።
135. ናዴል ፤ ከላይ ፣ በማስታወሻ ፣ ቍጥር ፣ ፲፫ ፣ በተጠቀሰው ፣ ከገጽ ፣ ፶፮ ፣ ካለው ፣ ጋር ፣ ያወዳድሯል ።
136. ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ በጠቅላላ ፣ ላይ ፣ አምኃ ፣ ጽዮን ፣ ዶሚኒክ ፤ ከላይ ፣ በማስታወሻ ፣ ቍጥር ፣ ፩፻፲ ፣ የተጠቀሰውን ፣ ከገጽ ፣ ፴፯-፴፰ ፣ ላይ ፣ ይመለከቷል ።

ከታች ፡ የምንመረምራቸው ፡ "ጎጂ ፡" ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊው ፡ ጥናት ፡ በየ ቦታው ፡ ተደርጎ ፡ ያልተገኙ ፡[137] እና ፡ ይበልጡንም ፡ ጊዜ ፡ የየደራሲውን ፡ ግምት ፡ ያዘሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አንባቢ ፡ ሊገነዘበው ፡ ይገባል ። እርግጠኛ የሆነ ፡ መረጃ ፡ ስለሌለ ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ የምንዘረዝራቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ "ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡" ሲሉ ፡ በምንመረምራቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ሊገኙ ፡ ስለሚችሉት ፡ ነገሮች ፡ በግምት ፡ የሰነዘሩትን ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

በጋርዮሽ ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፡ ተብለው ፡ ከሚገመቱት ፡ ጐጂ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ቀደምትነት ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ በይዞ ታው ፡ ላይ ፡ ዋስትና ፡ ማጣቱ ፡ ነው ።[138] ማሳ ፡ ይዞ ፡ ከሚተዳደር ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ አባል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድርሻውን ፡ ጠይቆ ፡ ሊወስድ ፡ መቻሉ ፡ "የአሁኑ፡ ባለይዞታ--- ማሳውን ፡ ለማሻሻል ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ እንዳይወሰድ ፡ ያደርገ ዋል ።"[139]

አንዱ ፡ ሌላው ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ጐጂ ፡ ነገር ፡ የተቆራረጠ ፡ መሬት ፡[140] የመያዙ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህም ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ጥቅም ፡ በማያስገኝ ፡ ማሳ ፡ መጠ ቀምን ፡ ማስከተሉ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ የኤኮ ኖሚ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ መመሪያ ፡ አለመሆናቸውንና ፡ ሰነፉና ፡ ብርቱ ውም ፡ እኩል ፡ መጠቀማቸውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለመጥቀስ ፡ ይቻላል ።[141] በተጨማ ሪም "--- የአራሹ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ማሳውን ፡ አለማረሱ ---" እና ፡ ይህ ፡ በሚሆን በት ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥም ፡ ሁሉ ፡ ይዞታን ፡ ለማሻሻል፡ ጥረት ፡ እንዳይደረግ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ።[142]

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የታየው ፡ ሌላ ፡ እጅግ ፡ አሳ ሳቢ ፡ የሆነው ፡ ችግር ፡ በመሬት ፡ ምክንያት ፡ ተነስተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀር ቡት ፡ ክሶች ፡ ቁጥር ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ችግር ፡ በየትም ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረገው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከሚነሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስቱ ፡ ያህል ፡ መሬት ፡ ነክ ፡ እንደሆኑ ፡ ተገምቷል ።[143] የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ ተነስተው ፡ የሚገኙት ፡ መሬት ፡ ነክ ፡ ክርክሮች ፡ ግን ፡ ዓይነታቸው ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በመሬት ፡ ክፍያ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ሲሆኑ ፡" ---የከረረ ፡

---

137. "እነዚህ ፡ (ጐጂ ፡ ነገሮች) ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ባላቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ የቱን ያህል ፡ ተስፋፍተው ፡ እንደሚገኙ ፡ እርግጠኛው ፡ ስለማይታወቅ ፡ በግምት ፡ ብቻ ፡ የታለፈ ፡ መሆኑን ማመን ፡ ይገባል ።" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።) ፡ ላውረንስና ፡ ማን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፻፶፲፭ ።
138. ከዚያው ።
139. ከዚያው ።
140. ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷፭-፷፪ ።
141. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፲፴-፲፭ ፡ ጋር ፡ ያወዳድ ሯል ።
142. ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፷፭-፷፪ ።
143. ኤስ ፡ በፍ ፤ ኢ-ኪ-ቱ- ላንድ ሪፎርም ፡ ኢን ፡ ኢትዮፕያ ፤ አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ካዳስትራል ፡ ሰር ቬይ ፡ ኤንድ ፡ ላንድ ፡ ሬጅስትሬሽን ፡ (፲፱ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ፡ ገጽ ፡ ፲ ።

ጠብ ፡ ከሚያስነሱት ፡ ዋነኞቹ---" [144] ናቸው ። እነዚህ ፡ "---የከረሩና ፡ ቶሎ ፡ የማይ ቆረጡ ፡ በርስቲ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ የጠላትነት ፡ መነሾች--" [145] በጊዜው ፡ ኤርትራን ፡ ያስተዳድር ፡ የነበረውን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ ከማሳሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ አካባቢ ፡ መንግሥቱ ፡ ርስቲ ፡ የነበሩትን ፡ ቀበሌዎች ፡ ወደ ፡ ዴሳ ፡ ለመለወጥ ፡ ተገዶ ፡ ነበር ፤ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ቀላል ፡ መፍትሔ ነበር ።

በዚህ ፡ በዘልማድ ፡ "የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡" (ኮሙናል ፡ ቴንዮር ፡) በሚባለው ፡ ስሪት፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ከሚያሳየው ፡ ተቃውሞ ፡ የተነሣ ፡ ማንኛውም ፡ የርስት፡ ምዝገባ ፡ ዓይነት ፡ እንዳይጀመር ፡ እንቅፋት ፡ እንደሆነ ፡ ተገምቷል ።[146] እንዲሁም ፡ "---የእርሻን ፡ ተግባር ፡ ከዘመኑ ፡ ወደኋላ ፡ በቀረ ፡ ደረጃ---" [147] እና ፡ "---ባነሰ ፡ የገንዘብ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ---" [148] ላይ ፡ እንዲቀር ፡ በማድረጉ ፡ ተቃውሞ ፡ ቀርቦበታል ።

በመጨረሻም ፡ ይህ ፡ እስካሁን ፡ የመረመርነው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነት ፡ ሕዝቡን ፡ በአቋምና ፡ በኑሮ ፡ ደረጃ ፡ የሚያከፋፍል ፡ በመሆኑ ፡ ቅሬታን ፡ ሲያስከትል ፤ በእኩልነት ፡ ረገድ ፡ ተሽሎ ፡ የሚታየው ፡የግል ፡ ባለቤትነት ፡ ተመርጦ ፡ ይገኛል ።[149] "የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡ ወደ ፡ ግል ፡ ስሪት ፡ ሊለወጥ ፡ ይገባል ፡" የሚለውን ፡ ሀሳብ ፡ የሚደግፉ ፡ ሁሉ ፤ ዘር ፡ ዞሮ ፡ ይህ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ በማስታወስ ፡ ሲጽናኑ ፡ ይታያሉ ።[150]

የዘርና ፡ የመንደር ፡ ስሪት ፡ ደጋፊዎች ፡ ጥቂት ፡ ይመስላሉ ፤ ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ ስለዚህ ፡ ስሪት ፡ ጠቃሚነት ፡ ሲያትቱ ፤ ርስቲና፡ ዴሳ ፡ "---በሀገራችን ፡ (በእንግሊዝ ፡ ሀገር) የሚገኙትን ፡ የግልና ፡ የጋርዮሽን ፡ ስሪት ፡ ባለጠግነትንና ፡ እኩልነትን ፡ (ሶሻሊዝም ፡ ወይም ፡ ኮሙኒዝምን ፡)---"[151] ይመስላሉ ፤ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ። ሚስተር ፡ ናዴል ፡ አጠንክረው ፡ የሚያመለክቱት ፡ ዴሳ ፡ የሚባለው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ "---እጅግ ፡ በሚለያይበት--" ቀበሌ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑንና ፡ የሚታየውም ፡ "የኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ስሜት ፡ " "--ጊዜያዊ ይዞታ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሚቀራረብ ፡ የኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ክፍል ፡ አባል ፡ ነውና ፡ ተከታዮቹን ፡ በማሰብ ፡ እንዲሠራ ፡ ያደርገዋል ፡" የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ነው ።[152] ስለዚህ ፡ ከላይ ፡ እንደጠቀስነው ፡ ሚስተር ፡ ማንና ፡ ሚስተር ፡ ላውረንስ ፡ እንዳሉት ፡ ሳይሆን ፤ በሚስተር ፡ ናዴል ፡ አስተያየት ፡ "የኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ስሜት" እጅግ ፡ ጠን

---

144. ዱንካንሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፫ ። በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ከሚቀርቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ የሚበልጡትና ፡ አስቸጋሪዎቹም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከቱ ፡ እንደነበሩ ፡ ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ በግምት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አስተያየት ፡ ሰንዝረዋል ።
145. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፲፬ ።
146. ለክቡር ፡ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ- ም- ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፤ አግራሪያን ፡ እስትራክቸር ፡ ኤንድ ፡ አግራሪያን ፡ ሪፎርም ፡ ኢን ፡ ኢትዮፕያ ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ- ም- ፤ ያልታተመ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡) ፡ ከገጽ ፡ ፲፰ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።
147. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፴፮ ።
148. ከዚያው ።
149. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።
150. ላውረንስና ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፩-፫፻፲፯ ፤ ሚስተር ፡ በፍ ፤ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተውን ፡ ሕዝብ ፡ በማስተማር ፤ ይህን ፡ ለውጥ ፡ ማፋጠን ፡ ይቻላል ፡ ሲሉ ፡ ተናግረዋል ። በፍ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ፡
151. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፭ ።
152. ከዚያው ።

ካራ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የዋስትናውን ፡ ችግር ፡ በማቃለል ፡ እያንዳንዱ ፡ ባለይዞታ ፡ የሌሎችን ፡ ጥቅም ፡ በማሰብ ፡ እንዲሠራ ፡ ያደርገዋል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ "የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ወደግል ፡ ስሪት ፡ ሊለወጥ ፡ ይገባዋል ፡" የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ የተቀበለው ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተወሰደውን ፡ እርምጃ ፡ ዘግየት ፡ ብለን ፡ እንመለከተዋለን ። ስለምንመረምረው ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ጠቃሚነትና ፡ ጐጂነት ፡ ከላይ ፡ የተነጋገርንበት ፡ ምክንያት ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በተባለው ፡ ስሪት ፡ ጸንቶ ፡ መቆየት ፡ ቅሬታ ፡ የገባቸው ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፪

ስለቤኒ ፡ አምር ፡ እና ፡ ስለደንከል ፡ ሕዝቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋምና ፡ የመሬት ፡ ስሪት ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋማቸው ፡-

በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙት ፡ ክርስቲያን ፡ ስላልሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ ያለው ፡ መረጃ ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ፡ በመሆኑ ፤ በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የምናደርገው ፡ ምርመራ ፡ የቤኒ ፡ አምርንና ፡ የደንከል ፡ ሕዝቦችን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ይሆናል ፤ በደራሲውም ፡ አስተያየት ፡ እነዚህ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ያቀዳቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ሁኔታ ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው ።

ኤርትራ ፡ በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ስር ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ (በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ. ም. አካባቢ) ፤ ቤኒ ፡ አምር ፡ "---በስተምዕራብና ፡ በደቡባዊ ፡ ምዕራብ ፡ እንዲያውም ፡ (በጠቅላላው) ፡ ኤርትራ ፡ ከሚገኙት ፡ ጐሳዎች ፡ በቁጥር ፡ የላቀ ፡ ነበር ። ---ጎሳውም ፡ ይገኝ ፡ የነበረው ፡ ከአቆርዳት ፡ በስተሰሜን ፤ በምዕራብና ፡ ደባቡዊ ፡ ምዕራብ ፡ ሆኖ ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በመስፋፋት ፡ ከሱዳን ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ (ይገባና) ፡ --- በምሥራቅ ፡ ወደ ፡ (ከረንና ፡ ሰራዬ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ይገኝ፡ነበር ፡) ---"[153] የደንከሌ ፡ ጐሳዎች ፡ ግን ፡ "ደንበኛ ፡ የቆላ ፡ ሰዎች ፡" በመሆን ፡ የኤርትራን ፡ ምሥራቃዊ ፡ ቆላዎች ፡ ይዘው ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።[154]

የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ "ክፍልፋዮች ፡" ወይም ፡ "ቅርንጫፎች" እንደነበሩት ፡ ተነግሯል ።[155] እያንዳንዱ ፡ ክፍልፋይ ፡ የጐሳ ፡ አባልነቱን ፡ ቢያውቅም ፡ የሚጠራው ፡ በየራሱ ፡ ስም ፡ ነበር ። "የቤኒ ፡ አምርን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅርንጫፎች ፡ የሚያስተሳስሩአቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሃይማኖት፡ ቋንቋ ፡ ተመሳሳይ ፡ ባህል ፡ ልማድና ፡ ካንድ ፡ ጐሳ ፡ መወለድ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ስለተባለ ፡ እነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አስተሳስረውት ፡ ይገኛሉ ፤ በግልጽም ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው ፤ ማለት ፡ አይደለም ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ለቅርንጫ

---

153. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፮ ።

154. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።

155. ኤስ ፡ ናዴል ፤ "ኖትስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ቤኒ ፡ አምር ፡ ሶሳይቲ ፤" ሱዳን ፡ ኖትስ ፡ ኤንድ ፡ ሪኮርድስ ፤ ቮልዩም ፳፯ ፤ ፓርት ፡ ዋን ፤ (፲፱፻፵፩) ፡ ገጽ ፡ ፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፮ ፤ ፳፫ ፡ እና ፡ ተከታዮቹን ፡ ይመለከቷል ፡ በተጠቀሰው ጽሑፍ ፡ መሠረት ፤ የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ሀያ ፡ አንድ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አሉት ።

ፎች ፡ በሙሉ ፡ እውነት ፡ ሆነው ፡ አይገኙም ፤ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ በመደራረብ ፡ ግማ ሾቹ ፡ አንዳንዶቹን ፡ የጐሳውን ፡ ቅርንጫፎች ፡ አስተሳስረው ፡ ሲገኙ ፡ ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡ የቀሩትን ፡ አስተሳስረው ፡ ይገኛሉ ።"[156]

የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ የእስልምናን ፡ ሃይማኖት ፡[157] የሚከተል ፡ ሲሆን ፤ ቋንቋ ውም ፡ ትግሬ ፡ ወይም ፡ ቤጃ ፡[158] ነው ። ጥንት ፡ "ከመካከለኛው ፡ አባይ ፡" ፈልሶ ፡ መጥቶ ፡ በቤኒ ፡ አምር ፡ "ሀገር ፡" ይገኙ ፡ ከነበሩት ፡ ጥንታውያን ፡ ነዋሪዎች ፡ በማግ ባት ፤ ዘር ፡ ተክቶ ፡ ተወላጆቹም ፡ ያጋጠማቸውን ፡ ሁሉ ፡ በማሳመን ፡ ካስገበሩት ፡ ወገን ፡ ተወላጅ ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ መሪዎቹ ፡ ወይም ፡ አለቆቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።[159] ስሙን ፡ ለጐሳው ፡ ትቶ ፡ የሄደው ፡ ይህ ፡ "የመካከለኛው ፡ አባይ ፡" ሰው ፡ አምር ፡ ይባ ላል ።[160]

እያንዳንዱ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ቅርንጫፍ ፡ አለቃና ፡ ጐበዝ ፡ ሲኖሩት ፡ እንደፖለ ቲካ ፡ አቋም ፡ የሚገመት ፡ ነው ። ጐሳው ፡ የሚተዳደረው ፡ ዲግላል ፡ በሚባል ፡ አጠቃ ላይ ፡ አለቃ ፡ ሲሆን ፡ ሹመቱም ፡ በውርስ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነው ።

የቢኒ ፡ አምርና ፡ የደንከሌ ፡ ጐሳዎች ፡ የፖለቲካ ፡ አቋም ፡ የተመሠረተው ፡ በኅ ብረ ፡ ሰብኡ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ "የገዢዎች ፡ ወገንና ፡" "የተገዢዎች ፡ ወገን ፡" በሚለው ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ነው ። በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ መሪዎቹ ፡ ናብታብ ፡ ተብለው ፡ ሲጠሩ ፡ ተገዥዎቹ ፡ ደግሞ ፡ የገዥዎቹ ፡ "አረብ ፡" ይባላሉ ፤ ---"ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ንዴስና ፡ የዚህ ፡ ወይም ፡ የዚያ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍል ፡ (ንብረቶ ች) ተብለው ፡ ይጠራሉ ።"[161] በደንከል ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ ገዢዎቹ ፡ አሲማራ ፡ (ቀይ ፡ ሰዎች) ፤ ተገዢዎቹ ፡ አዶይማራ ፡ (ነጮች ፡) ይባላሉ ።

በቀላሉ ፡ ሊገመት ፡ እንደሚቻለው ፤ በሁለቱም ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ኡን ፡ የመምራቱ ፡ መብት ፡ የሚገኘው ፡ በገዢዎቹ ፡ እጅ ፡ ሲሆን ፤ በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፤ የአምር ፡ ተወላጆች ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ነን ፤ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ የሚገም ቱት ፡ እነዚሁ ፡ መሪዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ በገዢና ፡ በተ ገዢ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ምርምር ፡ የሚያሻው ፡ ይመስላል።

ከላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተገዢዎች ፡ የሚገመቱት ፡ እንደ ፡ አምር ፡ ተወላጆች ፡ ሳይሆን ፡ እንደየባለጠጋው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ሚች ፡ "---ትቶት ፡ (እንደሚሄደው ፡)--- ንብረት---" በመቆጠር ፡ ሊወረሱ ፡[162] ወይም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የመጀመሪያ ፡ ወንድ ፡ ልጅዋን ፡ ስት ወልድ ፡ ከአያትየው ፡ እንደስጦታ ፡ ሊሰጡ ፡[163] ይችላሉ ። የተገዢዎች ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ በተገዢነት ፡ ሲቀሩ ፤ ሴቶቹ ፡ በጋብቻ ፡ ለየባሎቻቸው ፡ ገዢዎች ፡ ተገዢ ፡ በመሆን ፡ ይተላለፋሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተገዢዎች ፡ ባሮች ፡ እንዳልሆኑ ፡ ይገነዘቧል ፤

---

156. ከዚያው ።
157. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።
158. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፯ ።
159. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፶፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፭ ።
160. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱ ።
161. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፯ ።
162. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፶፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፰ ።
163. ከዚያው ።

ስለዚህም ፡ እንደባሪያ ፡ ሊሸጡ ፡ አይችሉም ።[164] ባሮች ፡ የሚባሉት ፡ ይበልጡኑ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ናቸው ።

ተገዢው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ዓመታዊ ፡ ግብር ፡[165] ለጌታው ፡ እንዲሰጥና ፡ ጌታውም ፡ ልጅ ፡ ሲወልድ ፡ መታያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይገደዳል ። ጌታውም ፡ በበኩሉ ፡ ተገዢውን ፡ 'እንደ ፡ አባት ፡'[166] በመሆን ፡ ተገቢውን ፡ መከባከብ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ይገደዳል ። ስለዚህ ፡ "--- በጌታና ፡ በተገዢ ፡ መካከል ፡ የሚገኙት ፡ የባህልና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ልዩነቶች ፡ በሁለቱ ፡ መኻል ፡ ኑሮአቸውን ፡ የሚያለያዩ ፡ እንቅፋቶች ፡ ሆነው ፡ አይገኙም ። እንዲያውም ፡ ተገዢው ፡ የጌታውን ፡ መከባከብና ፡ ከውጭ፡ ጠላት ፡ መከላከል ፡ መፈለጉና ፤ የገዢው ፡ አገልግሎትም ፡ ለጌታው ፡ ማስፈለጉ ፡ ሁለቱ ፡ ተባብረው ፡ በአንድነት ፡ እንዲኖሩ ፡ ያደርጋቸዋል ።"[167]

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤

የኅብረ ፡ ሰብእ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ግላዊ ፡ መብት ፡-

እንደሌላው ፡ ዘላን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፤ የሚበዙት ፡ የቤኒ ፡ አምርና ፡ የደንከል ፡ ሰዎች፡ ሲተላለፍ ፡ በመጣላቸው ፡ የጐሳ ፡ መሬት ፡ ድንበራቸው ፡ ውስጥ ፡ ግጦሽ ፡ በመፈለግ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ በመዘዋወር ፡ ይኖራሉ ። የሚያረቡዋቸውም ፡ ግመሎች ፡ ፍየሎች ፡ በጐችና ፡ ሌሎች ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ናቸው ።[168]

በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ ጌታና ፡ ተገዢ ፡ በግጦሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያላቸው መብት ፡ አንድ ፡ ነው ። "የተገዢው ፡ የግጦሽ ፡ መብት ፡ ሙሉና ፡ ፍጹምም ፡ ነው ፤ መብቱ ፡ የተገኘው ፡ ጐሳው ፡ ወይም ፡ ነገዱ ፡ በአንድ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ ካለው ፡ መሠረታዊ ፡ የንብረት ፡ መብት ፡ አይደለም ።"[169]

በደንከል ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ በግጦሽ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገዢዎች ፡ ወይም ፡ "አርነት ፡" የወጡ ፡ ተገዢዎች ብቻ ናቸው ። "ተገዥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከብቶች ፡ ሊኖሩት ፡ ይችላል ፤ የሚያሰማራበት ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ባለቤት ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። መሬትና ፡ ነፃነት ፡ የለሽ ፡ በመሆን ፡ ተገዢዎቹ ፡ ከጌቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ በመዘዋወርና ፡ ለገዢው ፡ 'ክፍል ፡' ሁሉ ፡ በመገበር ፡ የግጦሽ ፡ መብት ፡ ያገኛሉ ።"[170] ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ተገዢ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ቀበሌ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ገዢዎቹን ፡ ማስፈቀድና ፡ "---ለሚቆይበትም ፡ ጊዜ ፡ ለፖለቲካ ፡ ሥልጣናቸው ፡ መገበር ፡ ይኖርበታል ።"[171]

ሰፍሮ ፡ የሚኖርን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከቱ ፡ ጥያቄዎች ፤ በተለይም ፡ የእርሻ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከቱ ፡ እንደ ፡ ውርስ ፤ የመሬት ፡ ሽያጭና ፡ ዝውውር ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ከላይ ፡ ከመረመርናቸው ፡ በሁለቱ ፡ ዘላን ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ እንደሌላቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

---

164. ከዚያው ።
165. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፺፬ ።
166. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፺፰ ።
167. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፻፮ ።
168. ከቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍሎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሰፍረው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፬ ።
169. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፻፪ ።
170. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺፫ ።
171. ከዚያው ።

በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ "ከብትን ፡ አብሮ ፡ ማጋጥ ፡" ያልተለመደ ፡ መሆኑን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መግለጥ ፡ ያስፈልጋል ። "በየቦታው ፡ እጅግ ፡ በመበታተንና ፡ እያንዳንዱም ፡ የየራሱን ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ለመያዝ ፡ በመሽቀዳደም ፡ ስለሚኖሩ ፤ እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ በአንድ ፡ ሥልጣን ፡ ስር ፡ ሊተዳደሩ ፡ አይችሉም ። እንዲያውም ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ እንኳ፣ ከብቶችን ፡ በአንድነት ፡ ለግጦሽ ፡ አያሰማራም ። የጐሳው ፡ ክፍሎችና ፡ ዘመድ ፡ አዝማዶች በጣም ፡ የተራራቀ ፡ ግጦሽ ፡ ሊመርጡ ፡ ይችላሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችና ፡ እረኞች ብቻቸውን ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ ይዘዋወራሉ ። "(አንክሮው የደራሲው ፡ ነው ፡)[172] በጦርነት ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ካልተገናኙ ፡ በተቀር ፡ አንዱ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍልፋይ ፡ ሌሎቹ ፡ የጐሳው ፡ ክፍልፋዮች ፡ የት ፡ እንዳሉ ፡ እንደማያውቅ ፡ ሚስተር ፡ ናደል ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይገልጣሉ ።[173]

ክፍል ፪ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሕብረት ፡ ስለሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የወሰናቸው ፡ ድንጋጌዎች ፤

"ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ የሰዎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፤ ሕጉ ፡ ከወጣላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ልምዳቸውን ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕን ፡ የሚጠብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

እኛ ፡ ያቋቋምነው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ይህን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በተለይም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንና ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ በማሰብ ፡ ነው ።"

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ መግቢያ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ታቅዶ ፡ የነበረውን ፡ የጥንቱን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ አስቀድመን ፡ በመመርመር ፤ በመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለሚያስነሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመነጋገር ፡ አንባቢውን ፡ እናዘጋጃለን ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡

ስለጥንቱ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፤

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ እርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመለከተው ፡ የጥንቱ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በአምስት ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ የተከፋፈሉ ፡ ዘጠና ፡ ሦስት ፡ ቁጥሮች ፡ ነበሩት ። ይህን ፡ ረቂቅ ፡[174] በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ንዑስ ፡ አርእስቶች ፡ መመርመር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

172. ከዚያው ።

173. ናደል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፶፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲ ። ደራሲው ፡ ደንከሎችን ፡ የሚመለከት ፡ ተመሳሳይ ፡ ግልጥ ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ አላጋጠመውም ። የመሬት ፡ ስሪታቸውን ፡ ተመልክቶ ፤ የግጦሽ ፡ "አጠቃቀማቸው" ፡ የግል ፡ ነው ፤ ማለቱ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ።

174. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ረቂቁ ፡ ስላስፈለገበት ፤

በአርቃቂው ፡ አስተያየት ፡ ሊወጣ ፡ በታቀደው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ መጨመር ፡ "አስፈላጊ ፡" ነበር ። "በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የግል፡ ስሪት ፡ ሀብታም ፡ በሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ተስፋፍቶ ፡ ቢገኝም ፤ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የሀገሪቱ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡ በሚመስል ፡ መልክ ፡ ስር ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሁኔታውንም ፡ ስንመለከት ፡ ይህን ፡ መሬት ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ስሪት ፡ መሠረት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ አለመቻሉ ፡ አያጠራጥርም ።"[175] (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ እንደገለጥነው ፡ ሁሉ ፤ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚመለከታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ነበር ። "የመጀመሪያዎቹ ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ በማይከተሉ ፤ በከብት ፡ እርባታ ፡ በሚተዳደሩ ፡ የዘላን ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ክፍሎች ፡ ነበሩ ። ሁለተኛዎቹ ፡ ደግሞ ፡ በየመንደሩ ፡ ሰፍረው ፡ የሚገኙ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነበሩ ። በመካከላቸው ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርም ፡ በዚህ ፡ (የሕጉ ፡) ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጨመሩ ፡ ያቀድናቸውን ፡ ደንቦች ፡ ስንመለከት ፡ ሁቱም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ በአንድ ፡ (የሕጉ ፡) ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ሊተዳደሩ ፡ የማይችሉ ፡ መስለው ፡ አልታዩንም ።"[176]

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ዓላማዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ---"(አንደኛ) በጊዜው ፡ የነበሩትን ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ነፃነት ፡ ለማክበር ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዓላማ ፡ እናክላለን ፤ የየክፍሉን ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ግልጥ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመወሰን ፡ ፍላጐት ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ዓላማ ፡ እናክልበት ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ክፍሎችና ፡ በአሠራራቸው ፡ ላይ ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቁጥጥር ፡ እንዲኖረው ፡ በማድረግ አንዳንድ ፡ የሚታዩባቸውን ፡ በመብት ፡ በሚገባ ፡ አለመጠቀምን ፡ የማስወገድ ፡ ዓላማ። በሰነድ ፡ ቁጥር ፡ ፶፩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከቁጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፺፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ስር ፡ ያቀረብነውን ፡ የቁጥጥር ፡ ዘዴ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስት ፡ ሀሳቦች ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።"[177]

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ ፤ ከኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ በተለይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ መሠረታውያን ፡ ዓላማዎች ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲሄድ ፡ በማድረግ ፡ ባህልን ፡ እንዳለ ፡ ለማቆየት ፡ እንደነበረ ፡[178] እዚህ ፡ ላይ ፡ አጠንክሮ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

---

175. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ፡ (ትርጉም) ።
176. ከዚያው ፡ (ትርጉም) ።
177. ከዚያው ፡ (ትርጉም) ።
178. ከሚከተለው ፡ መግለጫ ፡ እንደምንረዳው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ከነበራቸው ፡ ጠቅላላ፡ አስተሳሰብ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ አይደለም ። "ተቆራኝታ ፡ የምታኖራቸውን ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታውያን ፡ የሆኑ ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ በመጠበቅ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የሕዝቧን ፡ የአኗኗር ፡ ዘዴ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ አጵ ሟን ፡ በፍጹም ፡ መለወጥ ፡ ትፈልጋለች ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፤ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ በተጣራ ፡ አኳኋን ፡ የተዘጋጀ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ቅንጅት ፡ እንዲሆን ፡ ኢትዮጵያ ፡ አትመኝም ። ይልቁንም ፡ የሕብረ ፡ ሰቡን ፡ ጠቅላላ ፡ ለውጥ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ እቅድ ፡ የያዘ ፡ እንዲሆን ፡ ስለምትመኝ ፤ ከሕጉ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ እንዲመሠረት ፡ ለምትመኘው ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ ተስማሚ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦችን ፡ ያዘለ እንዲሆን ፡ ትፈልጋለች ።" ፡ አር ፡ ዳቪድ ፡ "ኤሲቢል ፡ ኮድ ፡ ፎር ፡ ኢትዮጵያ ፤ ኮንሲዴሬሽንስ ፡ ኦን ፡ ዘ ኮዲፊኬሽን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎ ፡ ኢን ፡ አፍሪካን ፡ ካንትሪስ ፡" ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፤ ቮል ፡ ፴፯ ፡ (፲፱፻፷፫) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፫ ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፤ ፪ ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ስላጠቃለላቸው ፡ ጉዳዮች ፤

“የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ቻርተር ፡ (የመተዳደሪያ ፡ ደንብ፡)” የተሰኘው ፡ የረቂቁ ፡ የመጀመሪያው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ (ከቁጥር ፡ ፩—፲፯) “--- በኅብረት ፡ ማልማት ፡”[179] የተባለውን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ይደነግጋል ።

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ቻርተሮች ፡ (መተዳደሪያ ፡ ደንቦች) ሊወጡ ፡ የሚችሉበትን ፡ ሁኔታ ፡ በማሰብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበር ፤ የመጀመሪያው ፡ ደንብ ፡ ማንኛውም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ አባል ፡ ጥያቄ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ የሚዘጋጅ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ነበር ።[180] ይህም ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ይኖርበት ፡ ነበር ። ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ደግሞ ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ የሚገኙበት ፡ ጠ/ግዛት ፡ እንደራሴ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለነዚሁ ፡ ክፍሎች ፡ የሚያድለው ፡ ነበር ።[181] ይህም ፡ እንዲደረግ ፡ ታቅዶ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብዕ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ጠይቆ ፡ ሌሎቹ ፡ አባሎች ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ማስፈጸም ፡ ሲያቅታቸው ፡ ነው ። በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ የታደለው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በኅብረት ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ሊሻሻል ፡ ሲችል ፤ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ እጅ ፡ ከገባ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ነበረበት ።

የያንዳንዱ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፤ በመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱትን ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ ማስፈር ፡ ነበረበት ።[182] እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንጠቅስ ፡ የምንወደው ፡ “የመሬት ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸምና ፡ የኅብረት ፡ አጠቃቀም ፡ ዘዴ ፡” የሚል ፡ ርእስ ፡ ተሰጥቶት ፡ የነበረውን ፡ የረቂቁን ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ መሬት ፡ “እንደተፈጥሮ ፡ ሀብቱና ፡ እንደ፡ የዓይነቱ ፡” በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፤ ሌላውም ፡ የሕብረ፡ሰብኡ ፡ ንብረት ፡ ለጋራ፡ ጥቅም ፡ የሚመደብበትንና ፡ አባሎችም ፡ ሥራ ፡ የሚከፋፈሉበትን ፡ ዘዴ ፡ እያንዳንዱ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ ማመልከት ፡ ነበረበት ።[183]

ሌላው ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ደግሞ ፡ “በንብረት ፡ በኅብረት፡ ስለመጠቀም ፡” የሚል ፡ ርእስ ፡ ተሰጥቶት ፡ የነበረው ፡ ቁጥር ፡ ነው ። በዚህም ፡ ቁጥር ፡

---

179. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፩ ። ይህን ፡ ሐረግ ፡ በሚከተለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ እንመረምረዋለን ።

180. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፫ ።

181. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፬ ።

182. “ቁጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ በመተዳደሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፈው ፡ ቃል ።
የኅብረት ፡ መተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ጉዳዮች ፡ በተለይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።
ሀ/ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ዘመዶች ፤
ለ/ ፡ የኅብረቱ ፡ መብት ፡ የሚዘረጋባቸውን ፡ መሬቶች ፤
ሐ/ ኅብረቱ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ አኳኋንና ፡ ለኅብረቱም ፡ ወኪል ፡ ለመሆን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፤
መ/ የኅብረቱ ፡ መሬቶች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሀብቶች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደሚሠሩና ፡ እንደሚከፋፈሉ፤
ሠ/ የኅብረቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በመሻሻል ፡ የሚለዋወጥበትን ፡ አኳኋን ፤”

183. የረቂቁን ፡ የፈረንሣይኛ ፡ አነጋገር ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የእንግሊዘኛው ፡ ትርጉም ፡ ከገጽ ፡ ፪፳፰ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

መሠረት ፡ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ የተመደበው ፡ ንብረት በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፡ ዘዴ ፡ ከንብረቱም ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬና ፡ ገቢ ፡ ለአባሎቹ ፡ እንዴትና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚከፋፈል ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መተዳደርያ ፡ ደንብ ፡ መግለጽ ፡ ነበረበት ።[184]

ቁጥር ፡ ሺ፱፻፶፭ ፡ በመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ሲወጣ ፡ ከዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የተገደፉት ፡ ሁለት ፡ ቁጥሮች ፡ አዲስ ፡ አባሎችን ፡ መቀበልን ፡ ነባሮችን ፡ ማስወጣትንና ፡[185] መጠባበቂያ ፡ መሬቶችን ፡ ለይቶ ፡ ማኖርን ፡[186] የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ።

ከሁለቱ ፡ ዓይነት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ አንዱም ፡ ሳይኖር ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ደንቡ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ድንጋጌ ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ወይንም ፡ ሕግን ፡ የሚቃረኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይዞ ፡ ሲገኝ ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና፡ ተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚገባን ፡ ነገር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲኖር ፡ የተመረጠበት ፡ ምክንያት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በግልጽ ፡ ለመወሰን ፡ መሆኑንና ፡ ይህም ፡ የረቂቁ ፡ አንዱ ፡ ዓላማ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ።[187]

"የኅብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡" የተሰኘው ፡ የረቂቁ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ (ከቁጥር ፡ ፲፰-፴፮) ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ የቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሃላፊዎች ፡ ወይም ፡ ወኪሎቻቸው ፡ (አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱና ፡ ከተባለው ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ኃላፊ ፡ ጋር ፡ የሚኖሩ ፡ መሆን ፡ ነበረባቸው ፡) የሚገኙበትን ፡ ጉባኤ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ "ከፍተኛው ፡ ክፍል ፡" ያደርገዋል ።[188] ጉባኤው ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ብዛት ፡ ከግምት ፡ ሳይገባ ፡ አንድ ፡ ድምፅ ፡ ብቻ ፡ እንዲሰጠው ፡ ታቅዶ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የግድ ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባ ፡ ደንብ ፡ አልነበረም ። ስለዚህም ፡ ከተፈለገ ፡ እድሜአቸው ፡ ከአስራ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆኑና ፡ "በኅብረቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ" የሆኑ ፡ አባሎች ፡ በሙሉ ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ እንዲሆኑ ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለመደንገግ ፡ ይቻል ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ በደንቡ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ የጉባኤው አባል ፡ ለሆነ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በስሩ ፡ የሚተዳደረውን ፡ የሰው ፡ ብዛት ፡ በመገመት ፡ በዛ ፡ ያለ ፡ የድምጽ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻል ፡ ነበር ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ "---በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ ሲባል ፡ የተደነገጉ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች---"[189] እንዲከበሩ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። በነዚህም ፡ መሠረት ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ምክንያት ፡ በአባሎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዲደረግ ፡ አይፈቀድም

---

184. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቊጥር ፡ ፲፬ ። ረቂቁን ፡ ስንመለከተው ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፶፭ ፡ (መ) ፡ ሥር ፡ የተጠቀሰው ፡ "ሌሎች ፡ ሀብቶች" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ ያልዋሉ ፡ ወይም ፡ ሊውሉ ፡ የማይችሉ ፡ (ለምሳሌ ፡ ደኖችና ፡ ግጦሽ) ፡ መሬቶችን ፡ ከማመልከቱ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የሚጨምረው ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ አይመስልም ።
185. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቊጥር ፡ ፲፭ ።
186. ከዚያው ፡ ቊጥር ፡ ፲፮ ።
187. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፫ ።
188. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቊጥር ፡ ፲፰—፲፱ ።
189. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፫ ። እነዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ፡ እና ፡ ፵፰ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተው ፡ ይገኛሉ ።

ነበር ።[190] ማንኛውም ፡ ቤተሰብ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ እንዳይወከል ፡ ማድረግ ፤ ወይም ደግሞ ፡ ወኪሉን ፡ እንደየፍላጐቱ ፡ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ መንፈግ ፡ አይቻልም ፡ ነበር ።[191]

በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፤[192] የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ከፍተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚከተሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወያየት ፡ በያመቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በተወሰኑ ፡ ቀኖች ፡[193] መሰብሰብ ፡ ነበረበት ። እነዚህም ፡ ጉዳዮች ፡ የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፤[194] አዲስ ፡ አባሎችን ፡ መቀበል ፤[195] ነባር ፡ አባሎችን ፡ ማስወጣት ፤[196] የኀብረቱን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ መሾም ፤ መሻር ፡ መቆጣጠርና ፡[197] ኀብረ ፡ ሰብኡን ፡ ከሌላ ፡ ኀብረ ፡ ሰብእ ፡ ጋር ፡ ማዋሐድ ፤ ኀብረ ፡ ሰብኡን ፡ ማከፋፈልና ፡ ማፍረስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።[198] ውሳኔም ፡ የሚሰጠው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፤[199] ሲሆን ፡ ይህም ፡ ውሳኔ ፡ ሕግን ፡ ወይም ፡ የኀብረ ፡ ሰብኡን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የሚቃረን ፡ ሲሆን ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍ/ቤት ፡ በማመልከት ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችል ፡ ነበር ።[200] ተቀዋሚው ፡ ባቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔው ፡ እንዲሻር ፡ ጠይቆ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሽረው ፡ አለበለዚያም ፡ የፍ/ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለጊዜው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ሊያግደው ፡ ይችል ፡ ነበር ።[201]

የረቂቁ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ (ከቁጥር ፡ ፴፮ - ፵፫) ስለ ፡ ኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ይደነግጋል ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ለተነሳንበት ፡ ዓላማ ፡ አግባብ ፡ ያለውና ፡ የኀብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ክፍል ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ጥሩ ፡ መረጃ ፡ የሚሆነን ፡ ቁጥር ፡ ፴፮ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ በቁጥጥሩ ፡ ሥር ፡ ባለ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ንብረቶቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የማንኛውንም ፡ የግል ፡ ባለንብረት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመስሉ ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተባለው ፡ ክፍል ፡ የኀብረት ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ ፤ በመያዣ ፡ ወይንም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ፡ ነበር ። እነዚህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ከእርሻ ፡ ሚኒስትር ፡ ፈቃድ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[202] እንዲሁም ፡ ኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬቶቹን ፡ ለእርሻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሌላ ፡ በተግባር ፡ ከማዋሉ ፡ በፊት ፡ ተመሳሳይ ፡ ፈቃድ ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ማግኘት ፡ ነበረበት ።[203]

---

190. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቊጥር ፡ ፳፩ ፡ (፪) ።
191. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፪ ፡ (፪) ።
192. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፪ ፡ (፪) ። እነዚህ ፡ በአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸኑ ፤ ከጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ።
193. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፪ ፡ (፩) ።
194. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፫ ።
195. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፬ ።
196. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፮ ።
197. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፳፯ ።
198. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፴፩—፴፫ ።
199. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፴፬ ።
200. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፴፭ ።
201. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፴፮ ።
202. ከዚያው ፤ ቊጥር ፡ ፴፰ ።
203. ከዚያው ፡ ቊጥር ፡ ፴፱ ።

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ከተደረገው ፡ የመብት ፡ ጥበቃ ፡ ጐላ ፡ብሎ ፡ የሚታየው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባልም ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ የውጪ ፡ ሰው ፤ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ በይዞታው ፡ ስር ፡ በማድረግ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ መሬትን ፡ ባለሀብትነትን ፡ በይርጋ ፡ ለማግኘት ፡ አለመቻሉ ነው ።[204]

በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፤ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ውል ፡ እንዲዋዋል ፤ እንዲከስ ፡ ወይም ፡ እንዲከሰስ ፡ መብት ፡ ነበረው ።[205] ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ወቅት ፡ ለሚያደርሱት ፡ ጥፋት ፡ ኅብረቱ ፡ ኃላፊ ፡ እንዲሆንም ፡ ግዴታ ፡ ነበረበት ።[206] ይህ ፡ ኃላፊነት ፡ ሊመነጭ ፡ የሚችለው ፡ ሠራተኞቹም ፡ ሆነ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በማድረጋቸው ፡ ወይም ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ባለማድረጋቸው ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ለሚያስከትሉት ፡ የማይገባ ፡ ብልጽግና ፡ ሁሉ ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ የሚጠየቅ ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ነበር ።[207]

ከዚህ ፡ ልንረዳ ፡ እንደምንችለው ፤ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ "የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ጥቅም ፡ ጊዜ ፡ ጠብቀው ፡ ለማትረፍ ፡ ከማይመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ለመከላከል ፡ ነበር ።"[208] ይህ ፡ ክፍል ፡ የሌሎችን ፡ አገሮች ፡ የአሠራር ፡ ልምድ ፡ በመከተል ፡ ከተውጣጡት ፡ የረቂቁ፡ ክፍሎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። "በ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ምህረቱ ፡ የሶቭየት ፡ ሩሲያ ፡ የእርሻ ፡ ሕግ ፡ ለመመራት ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ ከተገመተ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ ሕግ ፡ በመከተል፡ የተጻፈው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኮልኮዝ ፡ የተባሉት ፡ አቋሞች ፡ እየተስፋፉ ፡ ስለሄዱ ፤ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የሶቭየት ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ባለመዋሉ ፡ ከጥቅም ፡ ውጭ ፡ ሆኗል ።"[209]

የረቂቁ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ (ከቁጥር ፡ ፵፱—፹፪) የሚመለከተው ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያሉትን ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ነበር ።

ማንኛውም ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ባገባ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሰ ፡ ጊዜ ፤ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ነበረው ።[210] አንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ የሚቆየው ፡ የኅብረቱን ፡ አባልነት ፡ ይዞ ፡ እስከ ኖረ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[211] ከአንድ ፡ አባል ፡ ላይ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታው ፡ ሊወሰድበት ፡ የሚችለው ፡ ንብረቱ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜና ፡ ይህንንም ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ የወሰነው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ተሟልቶ ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[212]

---

204. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵ ።
205. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፩ ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬፻፶፩ ፡ (፭) ፡ ጋር ፡ ያነጻጽሯል ።
206. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፪ ፡ (፩) ።
207. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፪ ፡ (፪) ፡ እና ፡ ፫ ። ከፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬፻፶፩ ፡ (፫) ጋር ፡ ያነጻጽሯል ።
208. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ፡ ትርጉም ።
209. ከዚያው ፤ ትርጉም ።
210. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፶፭ ።
211. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ፡ (፩) ።
212. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ፡ (፪) ። በረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ ፶፭—፶፫ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደር ፡ ታቅዶ ፡ የነበረውን ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ መብት ፤ በዝርዝር ፡ ማብራሪያው ፡ ውስጥ ፡ "የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ መብት" ፡ (ድሯ ፡ ዳቢታሲዮን) ፡ የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ። ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱ ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫፻፶፫ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ ጋር ፡ ያነጻጽሯል ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ "በቤት ፡ ውስጥ ፡ የመኖር ፡ መብትን" ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

ለእርሻው ፡ የሚውለው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬት ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ በመከፋ ፈል ፡ ለያንዳንዱ ፡ አባል ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ ወይንም ፡ እንዲሁ ፡ እንዳለ ፡ በተራድዖ ፡ ሊታረስ ፡ ይችል ፡ ነበር ። ካልሆነም ፡ ደግሞ ፡ ለአንዱ ፡ ዓይነት፡ መሬት ፡ "አንድ ፡ ዓይነት ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፤" ለሌላው ፡ ደግሞ ፡ የተለየ ፡ ዘዴ ፡ ሊበጅለት ፡ ይችል ፡ ነበር ። አንድ ፡ አባል ፡ የግሉ ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚችለው ፡ ከዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ላላነሰ ፡ ወይም ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ በሚወሰን ፡ ከዚህ ፡ ለሚረዝም ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።[213]

የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የአባሎችን ፡ "የእኩልነት ፡ መብት ፡" ሲያረጋግጥ ፡ ይህ፡ መብት ፡ ለእርሻ ፡ የሚሆን ፡ መሬት ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበር ፡ ይደ ነግግ ፡ ነበር ።[214] የያንዳንዱም ፡ ሰው ፡ ድርሻ ፡ እኩልነት ፡ የሚወሰነው ፤ የመሬቱን ፡ ዓይነት ፤ አቀማመጥ ፤ ጠቃሚነት ፤ ባለይዞታው ፡ መሬቱን ፡ በሚያርስበት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ጥቅም ፡ በሚያውልበት ፡ ጊዜ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡ ነበር ።[215] ሁኔታው ፡ እየታየ ፡ ለአንድ ፡ አባል ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአ ንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ማሳዎች ፡ ሊመድቡለት ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።[216]

በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ንብረት ፡ "እንዲገለገልበትና ፡ እንዲጠቀምበት ፡ የግል ፡ መብ ት ፡ የተሰጠው ፡ አባል ፡ ሁሉ ፤ አንድ ፡ ባለሀብት ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ሊያደርግ ፡ የተፈ ቀደለትን ፡ ማንኛውንም ፡ የአጠቃቀምና ፡ የግልጋሎት ፡ ሥራ ፡ ሊያከናውንበት ፡ ይችል ፡ (ነበር) ። "[217] በዚህም ፡ መሠረት ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ ተጠያቂ ፡ ለሚሆኑበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባልም ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

አንድ ፡ አባል ፡ በራሱ ፡ ጥረት ፡ ዘርቶ ፡ ያመረተው ፡ ሰብል ፡ ፍጹም ፡ ባለንብ ረት ፡ እንዲሆን ፡ ታቅዶም ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሚሆነው ፤ አባል ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከም ርቱ ፡ ከፍሎ ፡ ከሚሶ ፡ የማይበልጠውን ፡ በዋጋ ፡ ወይም፡ በችሮታ ፡ መልክ ፡ ለኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ሊሰጥ ፡ አልተስማማ ፡ እንደሆነ ፡ ነበር ።[218]

የኅብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ ለማረስ ፡ ወስኖ ፡ እንደሆነ ፤ የያንዳንዱን ፡ አባል ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በግልጽ ፡ እንዲወስን ፡ ይገ ደድ ፡ ነበር ።[219] የተባለው ፡ ስብሰባ ፡ "---መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ በማረስ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው፡ጥቅም፡በተቻለ፡መጠን፡ የየአባሉን ፡ መብት፡የሚያከብር፡እንዲሆን ፡ መደረግ ፡ ነበረበት ።"[220] መገንዘብ ፡ የሚኖርብን ፡ የመሬት ፡ አስተራረሱ ፡ ዘዴ ፡ እንዲወሰን ፡ ታቅዶ ፡ የነበረው ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ።

በተራድዖ ፡ ከታረሰ ፡ መሬት ፡ የሚገኘው ፡ ምርት ፤ በአባሎቹ ፡ መካከል ፡ የሚ ከፋፈለው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፤ ከግማሽ ፡ ሊበልጥ ፡ የማይችል ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ የምርቱ ፡ ክፍያ ፡ ለእርሻው ፡ ሥራ ፡ (ለምሳሌ ፡ ለእርሻ ፡ መሣሪያ ች ፡ መግዣ ፡) እና ፡ ለኅብረ ፡ ሰብኡም ፡ ተግባርን ፡ ማከናወኛ ፡ (ለምሳሌ ፡ የሥራ ፡

---

213. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ።
214. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፬ ፡ (፪) ።
215. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፰ ።
216. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፱ ።
217. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷ ።
218. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፪ ፡ እና ፡ ፷፫ ።
219. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፬ ፡ (፩) ።
220. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፬ ፡ (፫) ።

አስኪያጆች ፡ ደመወዝ ፡ ለመክፈል ፡) የወጣውን ፡ ወጪ ፡ ለመሸፈን ፡ ለኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ይመደባል ።[221] ከዚህ ፡ የተረፈው ፡ ምርት ፡ በእርሻው ፡ ተከፋይ ፡ ለሆኑት ፡ አባሎች ፡ ይከፋፈላል ። የየአባሉም ፡ ድርሻ ፡ የሚወሰነው ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ በሚመዝን ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ ካልተቻለ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ አባል ፡ በእርሻው ፡ ተካፋይ ፡ የሆነበትን ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነበር ።[222] ሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ ምርቱን ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሲሸጥ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜም ፤ እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ከሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ተገቢ ፡ ድርሻውን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።

የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ "መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ ስለማረስ ፡" የተሰኘውን ፡ ደንብ ፡ ባረቀቁበት ፡ ጊዜ ፡ የ "ኮሎክዝ ፡ ሕግ ፡" የተባለውን ፡ የሩሲያን ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ አድርገው ፡ ተጠቅመውበት ፡ እንደነበረ ፡ ይናገራሉ ።[223]

የንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮችን ፡ ይመለከታሉ ። አንደኛው ፤ የኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ ባንድ ፡ ለማንም ፡ ባልተሰጠ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስላላቸው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ነው ። መሠረታዊው ፡ ሕግ ፤ ማንኛውም ፡ አባል ፡ ቢሆን ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የመጠቀምና ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ አለው ፡ የሚለው ፡ ነው ።[224] በዚህም ፡ መሠረት ፤ ልማድ ፤ የመንግሥት ፡ ሕግና ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ደንቦች ፡ በሚፈቅዱት ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ አባል ፡ ለግጦሽ ፡ በተመደበው ፡ የኅብረቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ከብቶቹን ፡ ሊያሰማራ ፡ ከሚካውም ፡ ሥፍራ ፡ ለማገዶ ፡ የሚሆን ፡ እንጨት ፡ ሊለቅም ፡ መብት ፡ ነበረው ።[225] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ከሚሠማሩት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ከሚገኘው ፡ ቆዳ ፡ ከሩብ ፡ የማይበልጠውን ፡ ያህል ፡ የመካፈል ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ሁለተኛው ፡ ይህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያሏቸውን ፡ መብቶች ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ መብቶች ፡ የግል ፡ ነበሩ ፤ ማለትም ፤ የተሰጡት ፡ ለያንዳንዱ ፡ አባልና ፡ አብረውትም ፡ ለሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[226] ሊሸጡ ፡ ወይም ፡ በመያዣነት ፡ ሊሰጡ ፡ አይችሉም ፤[227] ባለመብቶቹ ፡ የሞቱ ፡ እንደሆነ ፡ መብታቸው ፡ ከመሞታቸው ፡ በፊት ፡ አብረዋቸው ፡ ይኖሩ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ይተላለፉሉ ፤[228] እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በሌሉ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መብቶቹ ፡ ለማህበሩ ፡ ተመላሽ ፡ እንዲሆኑ ፡ ታቅዶ ፡ ነበር ።[229]

የመጨረሻ ፡ የሆነው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ (ከቁጥር ፡ ፲፫—፲፰) የሚመለከተው ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ቁጥጥር ፡ ነበር ። በያንዳንዱ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእ

---

221. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፫ ።
222. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፯ ።
223. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፵፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫—፬ ።
224. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፳፱ ።
225. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡ እና ፡ ፳፮ ።
226. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፫ ።
227. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፬ ።
228. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፭ ፡ እና ፡ ፳፯ ።
229. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፯ ።

ርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲከፈት ፡ እና ፡ ይህም ፡ ጽ/ቤት ፡ ከጠ/ ግዛቱ ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። በየቦታው ፡ የሚገኙ ትን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶችን ፡ ለመምራትና ፡ ለማስተባበር ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ክፍል ፡ በእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ሊቋቋም ፡ ታቅዶም ፡ ነበር ።[230]

የያንዳንዱ ፡ ጽ/ቤትም ፡ ተግባር ፡ በጠ/ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የኅብረት የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ መኖር ፡ ማረጋገጥና ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡም ፡ የልማት ፡ ሥራ ውን ፡ የሚያሻሽልበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፈለግ ፡ መርዳት ፡ ነበር ።[231] በተጨማሪም ፡ ኅብረ ሰብኡ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ማግኘቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ የነዚሁ ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባር ፡ ነበር ።[232] አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ እንዲዘጋጅ ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባው ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ጊዜ ፡ አዘጋጅቶ ፡ መስጠት ፡ የተሳነው ፡ እንደሆነ ፤ ወይንም ፡ ኅብረቱ ፡ ደንብ ፡ እንዲ ሰጠው ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፤ ጽ/ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ በመቀበል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተደንግጎ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሚሰጠው ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተዘጋጀ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[233]

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎችን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶቹ ፡ የሚቆጣጠሩት ፡ በጠቅላላ ፡ ስብሰባቸው ፡ በኩል ፡ ነበር። ተመልካች ፡ ለመላክ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጽ/ቤት ፡ ጉባዔ ፡ ከመደረጉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲ ያውቅ ፡ መደረግ ፡ ነበረበት ።[234] በተጨማሪም ፡ ጉባዔው ፡ ተሰብስቦ ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ በት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ውሳኔውን ፡ ለጽ/ ቤቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ነበረበት ። ይህም ፡ የሚደረገው ፡ ውሳኔው ፡ ለጽ/ቤቱ ፡ ይተላለ ፋል ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ ሲኖር ፡ ነው ።[235] ውሳኔው ፡ ሕግን ፡ ወይም ፡ ደንብን ፡ የሚፃ ረር ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፤ ጽ/ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ፍ/ቤት ፡ በመውሰድ ፡ መቃወሚያ ፡ የማቅ ረብ ፡ መብት ፡ ነበረው ።[236]

በመጨረሻም ፤ የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕግን ፡ ሳይተላለፍ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእ ርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ በሚገባ ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችሉ ፡ ብሎ ፡ የሚገምታቸውን ፡ ደንቦችና ፡ እርምጃዎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ለጽ/ቤቶቹ ፡ ለማስተላለፍ፡ አስፈላጊው ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።[237]

<u>ክፍል ፡ ፫ ፤ ረቂቁ ፡ ስለምን ፡ ተቀባይ ፡ እንዳጣ ፤</u>[238]

በመሠረቱ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ሳይቀበል ፡ የቀረ በት ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ ፡ ሳያስበው ፡ የቀድሞ ፡ ልማዱን ፡ በፍጹም ፡ እርግፍ ፡ አድ

---

230. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፹፫ ።
231. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፹፬ ፡ (፪) ።
232. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፹፮ ።
233. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፹፯ ፡ እና ፡ ፹፰ ።
234. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፹፱ ።
235. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺ ።
236. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺፩ ።
237. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺፪ ። ቍጥር ፡ ፺፫ ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስን ፡ ነው ። ለጽ/ቤቱ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚገባውን ፡ በረቂቁ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ ሳያስታውቁ ፡ የሚቀሩ ፡ ዲሬክተሮች ፡ በወንጀለኛነት ፡ ይቀጣሉ ፤ ሲል ፡ ቍጥር ፡ ፺፫ ፡ ይደነግጋል ።
238. የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ያልተቀበለበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስረዳ ፡ ሰነድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። የመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ መክ ፈቻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ፤ "የሚከተለው ፡ ድንጋጌ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥ ር ፡ ፶፩ ፡ ፈንታ ፡ የሚተካ ፡ ነው ።" ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ፡ የምናመለክተው ፡ ሁሉ ፡ ከቃል ፡ ጥያቄ ፡ በተሰበሰበ ፡ መረጃ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ርጐ ፡ እንዲተው ፡ የሚያደርግ ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፡ ነበር ። ረቂቁ ፡ ይህን ፡ ስሜት ፡ ሊፈጥር ፡ የቻለበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ያዘለና ፡ በጣም ፡ ረጅም ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በጉባዔው ፡ ዘንድ ፡ የነበረው ፡ ስጋት ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚመለከታቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ የረቂቁን ፡ ዓላማ ፡ ለመረዳትና ፡ አዳዲሶቹን ፡ ሀሳቦችም ፡ ለመቀበል ፡ አይችሉ ፡ ይሆናል ፡ የሚለው ፡ ነበር ። ሕጉ ፡ ከመዘጋጀቱ ፡ በፊት ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ውሳኔ ፡ በሚያስተላልፉበት ፡ ጊዜ ፡ ይጠቀሙበት ፡ የነበረውን ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዓት ፡ በፍጹም ፡ እንዲለውጡ ፡ የሚያደርጓቸውን ፡ ስለ ፡ "ጉባዔ ፡" እና ፡ ስለ ፡ "እኩልነት" የተረቀቁትን ፡ ቁጥሮች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደመረጃ ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ። በልማድ ፡ መሠረት ፡ ጥቂት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተሰብስበው ፡ በመግባባት ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚያስተላልፉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ውሳኔ ፡ በሚያስተላልፉበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፣ "አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ድምጽ ፡ ይኖረዋል ፡" ወይም ፡ "በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ይወሰናል ፡" በሚሉት ፡ መመሪያት ፡ አለባቸው ፡ ብሎ ፡ ማወጅ ፣ ለተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ልማድም ፡ ሆነ ፡ ባህል ፡ ፍጹም ፡ እንግዳና ፡ ባዕድ ፡ ይሆናል ፤ የሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ሳይኖር ፡ አልቀረም ። ባጭሩ ፣ እንዲገለገልበት ፡ የታቀደው ፡ ሕዝብ ፡ ከረቂቁ ፡ እጅግ ፡ ወደኋላ ፡ የቀረ መስሎ ፡ ስለታየ ፣ ረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ ሳያገኝ ፡ ቀርቷል ።[239] ረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ እንዳያገኝ ፡ ሊያደርጉ ፡ የሚችሉ ፡ ሌሎች ፡ ምክንያቶችም ፡ አይጠፉም ።

በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፣ በያንዳንዱ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ሊቋቋሙ ፡ ታስበው፡ የነበሩትን ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ማቋቋም ፡ ከባድ ፡ ወጪ ፡ ያስከትላል ፣ የሚል ፡ ፍርሐትም ፡ ኖሮ ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ መንግሥት ፡ አስፈላጊውን ፡ ገንዘብና ፡ የሰው ፡ ኃይል ፡ ለማቅረብ ፡ አልተዘጋጀ ፡ ይሆናል ።

ጉዳዩ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ክፍሎች ፡ ብዙዎቹ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦቻቸውን ፡ ለመደንገግ ፡ ረዥም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስድባቸው ፡ ስለሚችል ፣ ረቂቁ ፡ በተለይም ፡ ከክፍል ፡ ፪-፫ ፡ ያሉት ፣ ሳይታሰቡ ፡ በድንገት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸው ፡ አይቀርም፣ የሚል ፡ ሌላ ፡ ፍርሃትም ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ፍርሃት ፣ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ በቂ ፡ ጊዜና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ ጉልህ ፡ የሆኑ ፡ ከልማድ ፡ የራቁ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ከማዘሉ ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ።

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እግብ ፡ ሊያደርስ ፡ ያቀዳቸው ፡ ሁለት ፡ ዓላማዎችን ፡ መሆኑን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ፤ አንደኛ ፡ የልማድን ፡ ጉድለቶችን ፡ ሊያሟላ ፡ ሲሆን ፣ ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደተገለጠው ፣ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በመመሪያት ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ማሟያ ፡ እንዲሆኑ ፡ የታቀዱት ፡ ደንቦች ፡ ሊለወጡ ፡ ወይም ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ ሊደረጉ ፡ የማይችሉ ፣ ማንኛውም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ሊያከብራቸው ፡ የሚገባ ፡ ነበሩ ። ሁለተኛም ፣ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለመደንገግ ፡ ለማይችሉ ፡ ማህበሮች ፡ ረቂቁ ፡ እንደመሸጋገሪያ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ እንዲችል ፡ ሆኖ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ረቂቁን ፡ ላለመቀበል ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሆናሉ ፣ ብሎ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ አያምንም ። እንዲያውም ፡ ረቂቁን ፡ ባለመቀበሉ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ብልህ ፡ ከመሆን ፡ የራቀ ፡ መስሎ፡

---

239. ለክቡር ፡ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። ክቡርነታቸው ፡ የፍትሐ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባል ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፤ የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ላይ፡ ይነጋገሩ ፡ በነበሩበት ፡ ወቅት ፡ የሥራው ፡ ኃላፊ ፡ በመሆን ፡ ተገኝተው ፡ ነበር ።

ታይቶታል ። የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲያስወግዳቸው ፡ የታቀዱትን ፡ ችግሮች ፡ ስንገምት ፣ ረቂቁ ፡ መጠነኛ ፡ ማሻሻያ ፡ ተደርጐበት ፡ ሊቀበሉት ፡ የሚቻል ፡ ይመስለናል ። ይህንንም ፡ የምንለው ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶችን ፡ ተመርኩዘን ፡ ነው ።

የመጀመሪያው ፡ የተመሠረተው ፡ በረቂቁ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ። ይህ ፡ ረቂቅ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ አቀነባብሮ ፡ እንዲይዝ ፡ የታቀደ ፡ ሲሆን ፣ በእርግጥም ፡ እነዚህን ፡ የያዘ ፡ ነበር ። ለረቂቁ ፡ መነሻ ፣ መመሪያና ፡ የሀሳብ ፡ ምንጭ ፡ የሆኑት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ነበሩ ። በመሠረቱ ፡ አርቃቂው ፡ ያበረከቱት ፡ አገልግሎት ፡ እነዚህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ማቀነባበርንና ፡ የዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ መልክ ፡ ማስያዝን ፡ የሚመለከት ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ብለን ፡ እንዳመለከትነውም ፣ እነዚህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ ሲባል ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ አንዳንድ ፡ ለውጦችን ፡ አድርጓል ። በዚህ ፡ ረገድም ፡ ቢሆን ፡ ረቂቁ ፡ አዲስ ፡ የሆኑ ፡ ሀሳቦችን ፡ አመጣ ፣ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ምክንያቱም ፡ ረቂቁ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋላቸው ፣ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በታወጀው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ የነበሩትን ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ስለዚህም ፡ ከሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ልማድን ፡ የተከተለ ፡ ስለነበረ ፣ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በተሰማራው ፣ ባብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ በቀላሉ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኝ ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። ዘላን ፡ በሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድም ፡ እንዲሁ ፡ ተቀባይነት ፡ ባላጣ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ከሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ደንቦች ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ እጅግ ፡ የተወሰኑ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። የረቂቁ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፣ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከት ፡ ስለሆነ ፡ በከብት ፡ እርባታ ፡ ሥራ ፡ በሚተዳደሩ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚፈጠረውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ እምብዛም ፡ የሚረዳ ፡ አልነበረም ። እነዚህን ፡ የኋለኞችን ፡ሰዎች ፡ የሚመለከቱት ፡ የረቂቁ ፡ ደንቦች ፡ (ለምሳሌ ፤ ስለሣር ፡ የተደነገጉት፡) ማንኛውም ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ሕዝብ ፡ ሊቀበላቸው ፡ የማይችሉ ፡ አልነበሩም ።

ዳግመኛም ፣ በሕጉ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ታቅደው ፡ የነበሩት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ "አዲሱን ፡" የኑሮ ፡ ዘዴ ፡ እንዲቀበሉትና ፡ እንዲላመዱት ፡ ለማድረግ ፡ በተለይ ፡ የታቀዱ ፡ ዘዴዎች ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።

ከነዚህም ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ በቁጥር ፡ ፯ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ። አንድ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፣ ደንብ ፡ በሚጠይቅበት ፡ ጊዜ ፡ ማህበሩ ፡ ይህንኑ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ተሰጥቶትታል ። እጅግ ፡ "ባሕል ፡ አክባሪ ፡" ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጥያቄ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታትም ፡ ላይቀርብ ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማህበር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡን ፡ ለመደንገግ ፡ ከቻለ ፡ ደግሞ ፣ ደንቡ ፡ በሥራ ፡ ላይ፡ የሚውለው ፡ ማህበሩ ፡ "በቂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በገመተው"[240] ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ።

ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፣ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚሰጠውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለማጥናት ፡ አግባብ ፡ ላላቸው ፡ ክፍሎች ፡ በቁጥር ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ "የማለማመጃ ፡" ጊዜዎች ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ባይገኙ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጥ ፡ በማድረግ ፡ ረቂቁን ፡ ማሻሻል ፡ ይቻል ፡ ነበር ።

---

240. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።

በተጨማሪም ፡ የገንዘቡና ፡ የሰው ፡ ኃይሉ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ሊሰ
ጠው ፡ ባልተገባም ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ማቋቋም ፡
የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ አልነበረም ። የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ባለ
ማውጣቱ ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተባለ
ውን ፡ ደንብ ፡ ባለመስጠቱ ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡
ሳይኖረው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲተዳደር ፡ ተወስኖ ፡ ነበር ። በዚህም ፡
መሠረት ፡ ጽ/ቤቱን ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ ተሠርዘው ፡ የደንቦች ፡ ምንጭ ፡ ተደ
ፈነ ፡ የሚል ፡ ፍርሃት ፡ ለጊዜው ፡ ሳይፈጠር ፡ ረቂቁን ፡ ለመቀበል ፡ ይቻል ፡ ነበር ።[241]

ረቂቁ ፡ በጉባኤው ፡ ዘንድ ፡ ሙሉ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ ያልቻለበት ፡ ምክን
ያት ፡ ምናልባት ፡ አርቃቂው ፡ በፈረንሣይና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ ሲጠቀሙ ፡
ግልጽ ፡ ባልሆነ ፡ አገባብ ፡ በመሆኑና ፡ በቃላቱም ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ የሚ
ታይ ፡ በመምሰሉ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ለምሳሌ ፡ ከረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፩ (ማለት ፡ ከፍ
ትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፺፱ ፡ ጋር ፡ ከሚመሳሰለው ፡ ቁጥር) አንድ ፡ ሰው ፡
ሊረዳ ፡ የሚችለው ፡ መመሪያ ፡ የሚሰጥ ፡ አንድ ፡ ማዕከላዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያለበት ፡
የመስኮቦችን ፡ ኮልኮዝ ፡ የመሰለ ፡ የተራድዖ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ እንዲጀመር ፡ መታቀ
ዱን ፡ ነው ።[242] አለፍ ፡ ይልና ፡ ደግሞ ፡ "በኅብረት፡ (በተራድዖ፡) ማልማትን ፡" ወይንም፡
ደግሞ ፡ "በግል ፡ ማልማት"ን ፡ የሚፈቅደው ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፺፩ ፡ ይገኛል ። እን
ግዲህ ፡ ቁጥር ፡ ፺፩ ፡ የቍጥር ፡ ፩ን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የሚቃረን ፡ መምሰሉ ፡ ግልጥ ፡
ነው ። ምናልባትም ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ሳይቀበለው ፡
የቀረው ፡ ይህ ፡ በረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ የሚታየው ፡ አለመግባባት ፡ የረቂቁን፡
ዓላማ ፡ በግልጽ ፡ ለማየት ፡ እንዳይችል ፡ ስላደረገው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ኮሚሲዮኑ ፡ ረቂቁን ፡ ሳይቀበል ፡ የቀረበት ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ፡ምክንያት ፡ ኖሮት፡ቢሆ
ንም ፡ የረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ ማጣት ፡ ያልታሰበ ፡ ውጤት ፡ ያስከተለ ፡ ይመስላል ። በመጀመ
ሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ሳይረዱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ፡
ምን ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ለማስተዳደር ፡ እንደታቀዱ ፡ ማወቁ ፡ በጣም ፡ አዳጋች ፡ ነው።

ጊዜ ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ ሕጉ ፡ የሚመለከታቸውም ፡ ክፍሎች ፡ የቁጥር ፡ ሺ፬፻፺፱
እና ፡ የሚከተሉትንም ፡ ቁጥሮች ፡ ዓላማ ፡ ሲረዱ ፡ ረቂቁን ፡ ተመልሶ ፡ ማየት ፡ አስፈ
ላጊ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ። ይልቁንም ፡ ረቂቁ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፺፱እና፡
በሚከተሉት ፡ መሠረት ፡ ሊወጣ ፡ የታቀደው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ጥሩ ፡ ሞዴል ፡
ሊሆን ፡ ስለሚችል ፡ ዓላማዎቹን ፡ ባጭሩ ፡ ቀጥሎ ፡ ማመልከት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ከሕጉ ፡ "የረቀቀውን ፡" ክፍል ፡ ወደጐን ፡ ስንተወው ፡ ዓላማው ፡ እንደሚከተ
ለው ፡ ይሆናል ። ማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ የኅብረ ፡
ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የአባሎቹን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱትን ፡ የራሱን ፡
ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መልክ ፡ እንዲያወጣ ፡ ማድረግ ፤ ይህንን
ንም ፡ በሚያደርግበት ፡ ወቅት ፡ አስነዋሪ ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡
ለእድገት ፡ ይጠቅማሉ ፡ ከሚባሉ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙና ፡

---

241. ሌላው ፡ ምርጫ ፡ ደግሞ ፡ ረቂቁን ፡ ተቀብሎ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ማድረጉ ፡
ነበር ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ማስመዝገብን ፡ የሚመለከተውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ አንቀጽ ፡
ዐሥርን ፡ ያገደውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲ሺ፲፻፳፲ን ፡ ይመለከቷል ።
242. ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሁሉ ፤ በመጨረሻውም ፡ ሆነ ፡ በመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ "የኅብ
ረት ፡ ሥራ ፡" ለሚለው ፡ ሐረግ ፡ ይህ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉሙ ፡ <u>አይደለም</u> ።

ተገቢ ፡ ያልሆኑትን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ለማስቀረት ፡ የታቀዱትን ፡ ግዳጅነት ፡ ያላቸውን ፡ ደንቦች ፡ ማክበር ፡ ይኖርበታል ።

የተባለው ፡ ክፍል ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ የቻለ ፡ እንደሆነ ፡ (ቀደም ፡ ስንል ፡ የመረመርናቸው ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩት ፡ ክፍሎች ፡ በቀላሉ ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚችሉት ፡ ነው ።) ዘመናዊነት ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ የሚታይባቸው ፡ በተለይም ፡ ጉባዔዎችንና ፡ የተራድዖ ፡ እርሻን ፡ ከሚመለከቱት ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አይኖራቸውም ። በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ከንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪—፬ ፡ ያሉትም ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚኖራቸው ፡ የመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ አከራካሪ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ስለአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ድንጋጌ ፡ ሳይኖረው ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ የተደነገገው ፡ ቁጥር ፡ ሕግን ፡ የሚቃረን ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ <u>ብቻ</u> ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ሳያወጣ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ረቂቁ ፡ እንደጊዜያዊ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በመሆን ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረዋል ።

አንድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ክፍል ፡ መሬቱን ፡ በኅብረት ፡ ለማልማት ፡ ቢሻ ፡ ነፃነት ፡ አለው ።[243] ማንኛውም ፡ ክፍል ፡ ቢሆን ፡ መሬቶችን ፡ በኅብረት ፡ (በተራድዖ) ፡ እንዲያለማ ፡ አይገደድም ። እንዲያውም ፡ መሬቶችን ፡ ሸንሽኖ ፡ ለአባሎቹ ፡ በማከፋፈል ፡ በግል ፡ እንዲለሙ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። በመጨረሻም ፡ መሬቶችን ፡ በበለጠ፡ ለማልማት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ "ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡" በሚሠራ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ጽ/ቤት ፡ የተባለው ፡ ክፍል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ማግኘቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የተለየ ፡ ኃላፊነት ፡ ይጣልበታል ።

<u>ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ስለታወጀው ፡ የመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡-</u>

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለአቀማመጡ ፤</u>

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻ ፡ የሚገኙት ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ "በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለመጠቀም ፡ "በሚለው ፡ በአንቀጽ ፡ ፱ ፡ ሥር ፡ ነው ። ስለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ከተደነገገው ፡ ምዕራፍ ፡ ቀደም ፡ ብሎ፡ ስለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረትና ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሀብቶች ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የሚወስኑ ፡ ምዕራፎች ፡ ይገኛሉ ። ከተባለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተከታታይነት ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ "በኅብረት ፡ የመጠቀም ፡" ዘዴዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁለት ፡ ምዕራፎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ሥር ፡ የሚገኘው ፡ "በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡" እና ፡ በምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ሥር የሚገኘው ፡ "የከተማ ፡ ክልል ፡ የሆኑ ፡ ሥፍራዎች ፡" ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ አራቱ ፡ ምዕራፎች ፡ እነዚህ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

243. ይህ ፡ እርምጃ ፡ የተራድዖ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወደፊት ፡ ሊጀመር ፡ እንዲችል ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ መሠረት ፡ ለመጣል ፡ መታቀዱ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ "የኅብረት ፡ ባለሀብትነት" በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሥር ፡ ስላለው ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፤

ስለ ፡ "ኅብረት ፡ ባለሀብትነት ፡" እስካሁን ፡ የተደረሰው ፡ ጽሑፍ ፡ አነስተኛ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የተማታና ፡ ያልተጣራ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የተለዩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ዎችን ፡ ለመግለጽ ፡ በተወሰነ ፡ አገባብ ፡ ሕጉ ፡ የሚጠቀምባቸው ፡ ቃላት ፡ ምርጫ ፡ ሳይደረግ ፡ በዘፈቀደ ፤ የኅብረት ፡ (ኮሙናል ፡) ባለሀብትነትንም ፡ ለማስረዳት ፡ ከጥ ቅም ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ ይገኛሉ ።

አስቀድመን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡[244] የግልና ፡ የኅብረት ፡ ባለሀ ብትነት ፡ ስላላቸው ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ባጭሩ ፡ ምርመራ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኅብረት ፡ (ኮሙናል ፡) ባለሀብትነት ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ምርመራ ፡ እንመለሳለን ። "ትር ጓሜ ፡" የሚል ፡ አርእስት ፡ የተሰጠው ፡ ቁጥር ፡ ሺ፪፻፶፯ ፡ ሀብትነትን ፡ "ሲተረጉም ፡" በግዙፍ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ የሰፋ ፡ መብት ፡ ነው ፡ ይለዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከቁጥር ፡ ሺ፪፻፶፯ ፡ የሀብትነትን ፡ መለኪያ ፡ ለማወቅ ፡ ባንችልም ፤ ቁጥር ፡ ሺ፪፻፶፰ ይህ ንኑ ፡ ቃል ፡ ለባለሀብቱ ፡ በተሰጡት ፡ መብቶች ፡ መሠረት ፡ ተርጉሞት ፡ ይገኛል ። እነዚህም ፤ ባለሀብቱ ፡ በንብረቱ ፡ በመሰለው ፡ መንገድ ፡ ሊገለገልበት ፤ ሊጠቀምበ ትና ፡ ዋጋ ፡ ተቀብሎም ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ ሳይቀበል ፡ በንብረቱ ፡ ሊያዝበት ፡ የመቻሉ ፡ መብት ፡ ናቸው ። በላያቸውም ፡ ገደብ ፡ ተደርጎባቸዋል ።[245] ስለዚህ ፤ በጠቅላላ ፡ አነ ጋገር ፡ ጥንትም ፡ የባለሀብቶች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱትን ፡ ሦስት ፡ መብቶች ፡ ማለት ፤ የመገልገል ፤ የመጠቀምና ፡ የማዘዝን ፡ መብት ፤ ሕጉ ፡ አክብሮ ፡ ይገኛል ።

በተጨማሪም ፤ ሕጉ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፤ ማለትም ፡ ለአንድ ፡ ነገር ፡ ከአ ንድ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎች ፡ ባለሀብት ፡ የሚሆኑበትንም ፤ ሁኔታ ፡ ይደነግጋል ።[246] የጋራ ፡ ሀብትነትም ፤ ጊዜያዊ ፡ ወይም ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የመጀመሪያው ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ከባለሀብቶቹ ፡ ፍላጐት ፡ በሚመ ነጭ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ነው ።[247] በሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለ ሀብትነት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ ላይኖር ፡ ይችላል ።[248]

ጊዜያዊ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያገለግል ፡ በተመደበበት ፡ ዓላማ ፡ መሠረት ፡ በነፃ ፡ ሊገለገልበት ፡ ይች ላል ። በተጨማሪም ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ከንብረቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ፍሬ ፡ ለመካፈል ፡ መብት ፡ አለው ።[249] የጋራ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላ ለፍ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ለማስያዝ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት ፡ ለመለወጥ ፡ ሲፈለግ ፡ ግን ፡ ጊዜያዊ ፡ የሆኑ ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ መስማ ማት ፡ አለባቸው ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ጊዜያዊ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ሀሳቡን ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደሆን ፡ ንብረቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ የተመ

244. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፤ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ እና ፡ ፰ ፡ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ።
245. በተለይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፶፱ ፤ ሺ፪፻፷፩ ፤ እና ፡ ሺ፪፻፷፪ን ፡ ከነተከታዮቹ ፡ ያነጻጽ ሯል ።
246. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፸፪ ፡ (፩) ።
247. ይህን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፸፫ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።
248. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፹፯ ፤ ሺ ፪፻፹፯ ።
249. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፸፫ ።

ደበበትን ፡ ዓላማ ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻልም ።[250] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋ ፈል ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ተመሳሳይ ፡ መብት ፡ የለውም ። ይህም ፡ የተደረገ በት ፡ የባለሀብትነቱን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ አጠቃላይ ፡ መለያ፡ አለው ፤ ይኸውም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ባለሀብትነታቸው ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ በመላ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የያንዳንዱ ፡ ባለሀብት ፡ ድርሻ ፡ ግዙፍ ፡ በመሆን ፡ አይታ ይም ፤ አይዳሰስም ። "የያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለንብረት ፡ ድርሻ ፡ የንብረቱ ፡ ገሚስ ፣ ሲሶ ፣ ሩብ ፡ ወዘተ ፡ እየተባለ ፡ በሂሳብ ፡ ክፍልፋይ ፡ ይገለጣል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ንን ፡ ክፍልፋይ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚታይ ፡ እንደሚዳሰስ ፡ አድርጎ ፣ 'ይኸውና፥ ከንብረቱ ፡ ከዚህ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፤' ብሎ ፡ ማመልከት ፡ አይቻልም ። እያንዳ ንዱ ፡ ክፍልፋይ ፡ በጠቅላላው ፡ በንብረቱና ፡ በእያንዳንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር፡ ነው ።" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)[251] ስለዚህም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡[252] ስለያ ንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ድርሻ ፡ በሚደነግግበት ፡ ጊዜ ፡ ድርሻውን ፡ እንደማይ ታይ ፡ ረቂቅ ፡ መብትና ፡ በያንዳንዱም ፡ የሀብቱ ፡ ቅንጣት ፡ አካል ፡ ላይ ፡ እንደተመ ሠረተ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አጥብቆ ፡ ማሳሰብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ለግል ፡ ባለንብረቶች ፡ የተሰ ጡት ፡ ሦስቱ ፡ ሥልጣኖች ፡ በሕጉ ፡ ሥር ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ እንዲካፈሏቸው ፡ መደ ረጉን ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የሀብታቸውን ፡ የአስተዳ ደር ፡ ሥራ ፡ "በአንድነት ፡" "እንዲመሩት" ፡ ይደነግጋል ።[253]

በክፍል ፡ አንድ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ የጎሣ ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ መሬቶ ችን ፡ ሁኔታ ፡ ሕጉ ፡ በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ሥር ፡ አለመጨመሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በነዚህ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ መብት ፡ ተቀብሎ ፡ አይ ታይምና ።

ከጎሣ ፣ ከዘር ፡ ወይም ፡ ከመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ የግለ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ሁሉ፡ የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ እንዳላቸውና ፡ በድርሻቸውም ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ በግል ፡ የመጠ ቀምና ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ፡ ተመልክተናል ። እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ የየ ራሱን ፡ ድርሻ ፡ እንደፈቀደ ፡ ሊያለማው ፤ ወይም ፡ ለግጦሽ ፡ የሚሆን ፡ ድርሻውን ፡ ባሻው ፡ መንገድ ፡ ሊጠቀምበት ፡ መቻሉንም ፡ ተገንዝበናል ። ማንኛውም ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ አባል ፡ ያቺን ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ያለባለመብቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሊገለገልባት ፡ አይችልም ።

ስለዚህ ፣ ሕጉ ፡ ስለጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ የሚወስናቸው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፣ የመ ንደር ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ግዙፍ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በመከፋፈሉና ፡ እያንዳንዱም ፡ አባል ፡ በድርሻው ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የግል ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ በመሰጠቱ ፡ ለተባለው ፡ ርስት ፡ አግባብ ፡ ሊኖራቸው ፡ አይችልም ።

"አንድ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡" መሬቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንኳ ፡ ጊዜያዊ ፡ የሆኑ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ካላቸው ፡ መብት ፡ እጅግ ፡ የተ

250. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፷፯ ።
251. ጂ ፡ ካርቦኒዬ ፣ ድሯ ፡ ሲቪል ፡ ቶም ፡ ፪ ፡ ሌቢያንዜት ፡ ሌዝ ፡ ኦብሊጋሲዮን ፡ (፲፱፻፶፯) ፡ እ- ኤ- አ- ገጽ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ። (ትርጉም) ።
252. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፶፱ ፣ ፲፪፻፷ ።
253. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፷፩ ።

ለየ ፡ ነው ። አንድ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ ከተስማሙበት ፡ መሬቱን ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊያስተላልፍ ፡ መቻሉን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ተመልክተናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ ደንብ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባ ሎች ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ እምቢ ፡ የማለትን ፡ ነው ። ስለዚህም፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ አንድ ፡ ባዕድ ፡ ወደሆነ ፡ ሰው ፡ መሬታቸው ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማ ድረግ ፡ (ለምሳሌ ፡ በመግዛት) ፡ ባይፈቅዱ ፡ ወይም ፡ (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚሆነው ሁሉ) ፡ ባይችሉ ፡ ባለመሬቱን ፡ ከመሸጥ ፡ የሚያግደው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ከሆነው ፡ ከማንኛውም ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ አንዱም ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁኔታ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ከሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ፡ ፍጹም ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የጋራ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።[254] በሌላ ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ከተቃወመ ፡ የጋራ ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊተላለፍ ፡ አይችልም ።

በጋራ ፡ ባለሀብቶችና ፡ የመንደርና ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የመብት ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊጠቃለል ፡ ይች ላል ፤ ሁለቱም ፡ "ንብረታቸውን ፡" በመሸጥ ፡ ወይም ፡ በማስተላለፍ ፡ ረገድ ፡ ያላቸው፡ መብት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ሌላ ፡ የመብት ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለም ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በዘር ፡ ወይም ፡ በመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ የኅብ ረት ፡ መሰል ፡ መብት ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ መመሪያ ፡ የምናገኘው ፡ ሕጉ ፡ ስለጋራ ፡ ባለ ሀብትነት ፡ ከሚደነግጋቸው ፡ ደንቦች ፡ ሳይሆን ፡ የ"መንደር ፡" እና ፡ የ"የጉሣ ፡" መሬቶችን ፡ ከሚመለከቱት ፡ ከሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻፪ ፡ ካሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ነው ። በነዚ ህም ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የዘር ፤ የጉሣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ መሬቶች ፡ ሁሉ ፡ "የኅ ብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ክፍል ፡" የሚባል ፡ "ማኅበር ፡" የግል ፡ ንብረት ፡ ሆነው ፡ ይቆጠራሉ ። ይህም ፡ "ማኅበር ፡" የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ፡ "ቤተዘመድ" ፤ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፤ "መንደር ፡" እና ፡ የጉሣ ፡ መሬት፡ በሚገኝበትም ፡ "ጉሣ ፡" እየተባለ ፡ የሚጠራ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የዘር ፤ የመንደር ፡ ወይም ፡ የጉሣ ፡ የሆኑ ፡ መሬቶችን ፡ "የኅብረት ፡"[255] ወይም ፡ የጋራ ፡[256] ሀብት ፡

---

254. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፷፯ ።

255. "የኅብረት ፡ የርስት ፡ ስሪት" ፡ የሚያመለክተው ፡ "---አንድ ፡ የተወሰነ ፡ መሬት ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፤ በጉሣ ፤ ወይም ፡ በመንደር ፡ ባለሀብትነት ፡ ሥር ፡---" መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተገልጧል ። ሠይፉ ፡ ተክለማርያም ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፫ ። ይህ ፡ አተረጓጐም ፡ ግልጽና ፡ የተብራራ ፡ አይደለም ።

256. ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌና ፡ ሌሎቹ ፤ ላንድ ፡ ቲኒየር ፡ ሲስተምስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኤንድ ፡ አናሊሲስ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሪፎርምስ ፡ አንደርቴክን ፤ (፲፱፻፷፯ ፡ እ- ኤ- አ- ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፤ ገጽ ፡ ፱ ። በዚህ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ "ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈሉ ፡ የመሬት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች" ፡ ናቸው ፡ ተብለዋል ። የዚህ ፡ አተረጓጐም ፡ አንድ ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ጉድለት ፤ "ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈሉ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በሕጉ ፡ ቃል ፡ ታስቦ ፡ ያልነበረ ፡ ትርጉም ፡ መስጠቱ ፡ ነው ። ከቍጥር ፡ ሺ፪፻፷፯ ፡ ጋር ፡ ያነጻጽሯል ። የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ የጋራ ፡ ባለሀ ብትነትን ፡ ሲገልጹ ፤ የሚሰጧቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ የውሀ ፡ ጉድጓድን ፤ የመንገድንና ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ዎችን ፡ ባለሀብትነት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ በተፈጥሮአቸው ፡ ሊከፋፈሉ ፡ የማይችሉ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

ብሎ ፡ መጥቀስ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊኖረን ፡ የሚችለው ፡ ማንኛውም ፡ ጥርጣሬ ፡ በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ባለሀብትነት ፡ (እና ፡ በመንግሥት ፡ የታወቀ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማህበር ፡) እና ፡ በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መካከል ፡ ያለውን ልዩነት ፡ ለመወሰንና ፡ ያልተብራራም ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ለማብራራት ፡ በታቀደው ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፶፯ ፡ (፪)፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱ ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱት ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ዝርዝር ፡ የተሟላ ፡ አለመሆኑን ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ። የዝርዝሩ ፡ ዓላማ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ለታቀዱት ፡ መሬቶች ፡ ምሳሌ ፡ ለመስጠት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በእንግሊዝኛው ፡ "ቪሌጅ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚገልጸው ፡ የመንደርን ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ "ደሽ ፡" በሚለው ፡ በአማርኛው ፡ ትርጓሜ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ፤ "ጎሣ ፡" የሚለውም ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ የከብት ፡ አርቢ ፡ ክፍሎች ፡ የጎሣ ፡ መሬት ፡ ስሪትን ፡ ነው ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ "ጎሣ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ስሪትን ፡ አያጠቃልልም ።

ከሺ፬፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ሺ፭፻ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ቁጥሮች ፡ በዘር ፡ ርስት ፡ ስሪት ፡ ስር ፡ የሚገኙ ፡ መሬቶችንም ፡ ይመለከታሉ ፡ የምንልበት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉን ። የዘር ፡ (አንዳንድ ፡ የዘር ፡ ሐረጎች ፡ በመቶ ፡ የሚቆጠሩ ፡ አባሎች ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ፤) የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ከመንደር ፡ ወይም ፡ ከጎሣ ፡ መሬቶች ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላሉ ፤ ምክንያቱም ፡ የዘር ፡ ርስትም ፡ እንደ ፡ መንደርና ፡ ጎሣ ፡ ርስት ፡ "የኅብረት ፡" ሀብትነትን ፡ አዝሎ ፡ ስለሚገኝ ፡ ነው ። ሁለተኛም ፤ ሕጉን ፡ ያረቀቁት ፡ ሊቅ ፤ የኅብረት ፡ ስለሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የተረቀቀው ፡ ሕግ ፡ በየ"መንደሩ ፡" ለሚገኙት፡ ለትግሬና ፡ ለኤርትራ ፡ ሕዝቦች ፡[257] የታቀደ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ያትታሉ ። በእነዚህ ፡ ሁለት ፡ ጠ/ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ የመንደርና ፡ የዘር ፡ ስሪት ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ሆነው ፡ በየመንደሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መገኘታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የዘር ፡ ርስትም ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱—፩ሺ፭፻ ባለው ፡ ደንብ ፡ ስር ፡ የሚተዳደር ፡ ነው ። ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ የመጨረሻ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የዘር ፡ ርስትን ፡ "በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡" ስር ፡ ለማስተዳደር፡ እንደሚቻል ፡ የሚፈቅድ ፡ የሚመስለው ፡ የእንግሊዝኛው፡ ቁጥር፡ ፩ሺ፩፻፳፩ ፡ (፩)፡ ከሺ፬፻፹፱ ፡—፩ሺ፭፻ ፡ ያሉትን ፡ ቁጥሮች ፡ የሚቃረን ፡ መምሰሉ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ቁጥሩ ፡ ከአማርኛ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሲተረጐም ፡ በተደረገ ፡ ስህተት ፡ ነው ።[258] በቁጥር ፡ ሺ፩፻፳፳ ፡ የአማርኛ ፡ ቅጂ ፡ ውስጥ ፡ "የጋራ ፡ ባለሀብ

አር ፡ ዳቪድ ፤ ኮማንቴር ፡ ዱ ፡ ቲትር ፤ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ኮፕሪፕሪዬቴ ፤ ደልዩሉፍሩይ ፤ ኤ ፡ ዴዝ ፡ ኦትር ፡ ድሯ ሬል ፡ (ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፵፫) ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፵፰ ፡ (፲፱፻፶፮ ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፤ ገጽ ፡ ፩ ። ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፤ ከላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ በመሬታቸው ፡ ላይ ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ፡ ይናገራሉ ። ላውረንስ ፡ ኤንድ ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፱፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፰ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚገባን ፡ ነገር ፡ መንደረተኞች ፡ በመንደራቸው ፡ መሬት ፤ ቤተ ፡ ዘመዶችም ፡ በቤተ ፡ ዘመዳቸው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ለመግለጽ ፡ "የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይ ፡" በሚል ፡ አነጋገር ፡ መገልገል ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ ነው ። የአላባን ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይን ፡ ቋሚ ፡ ጠባዮች ፡ ከቍጥር ፡ ሺ፫፻፱ ፡ (፩) ፡ እና ፡ ሺ፫፻፳፪ ፡ ይረዷል ።

257. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።

258. የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ከቍጥር ፡ ሺ፩፻፳፩ ፡ (፩) ፡ ሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ደንብ፡ አልነበረውም ። ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፹፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፬።

ትነት ፡” የሚለው ፡ ሐረግ ፡ አይገኝበትም ። ስለዚህ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቁጥር ፡ ሺ፩፻፳፪ ፡ ሊነበብ ፡ የሚገባው ፡ ለጉዳዩ ፡ በቀጥታ ፡ አግባብ ፡ ካላቸው ፡ ከቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ነው ። ከሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻፪ ፡ ያሉት ፡ ቁጥሮች ፡ የዘር ፡ ርስትንም ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲሆን ፤ የዘር ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ “በጋራ ፡ ባለሀብት ነት ፡” ስር ፡ ሊተዳደር ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ አያመለክቱም ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ እርሻ ፡ መሬት ፡ ስላላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፤

በቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻፪ ፡ ባሉት ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፤ የጐሣና ፡ የመንደር ፡ የእርሻ ፡ “ማኅበሮች ፡” ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ? ሕጋዊ ፡ ሰውነታቸው ፡ እንደግል ፡ ማኅበሮች ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ “መንግሥታዊ ፡” አቋሞች ? የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ሙሴ ፡ ዳቪድ ፡ እንዳመለከቱት ፡ ሁሉ ፤ “በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ‘ሰው’ ፡ ወይም ፡ ‘ሰውነት’ ፡ ብለን ፡ ስንናገር ፡ እንደሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ [ናቸው] ፡ ለማለት ፡ ሳይሆን ፡ እንደሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ አላቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱ ፡ ከሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ ነው ።”[259]

እነዚህ ፡ “ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሰዎች ፡” ሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ያሏቸውን ፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደሌሏቸው ፡ መገንዘብ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። የሚሰጧቸው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የተወሰኑና ፡ ለአቋማቸውና ፡ ለታቀዱበትም ፡ ዓላማ ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱትን ፡ ብቻ ፡ ነው ።[260]

አንድ ፡ ከላይ ፡ እንደተጠቀሱት ፡ ያለ ፡ የእርሻ ፡ “ማህበር ፡” ያለውን ፡ ሕጋዊ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ ለመወሰን ፤ የ“ማኅበሩን ፡” መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ መመልከትና፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ “የግል ፡” እና ፡ “ሕዝባዊ ፡” (መንግሥታዊ) ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስላሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ መመራመር ፡ ያሻል ።[261]

የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ከተሰጡዋቸው ፡ መብቶች ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ የሚታየው ፡ የማኅበሩ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዳይወሰድ ፡[262] የሚያግደው ፡ ደንብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መብት ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በዝርዝር ፡ እንነጋገራለን ።

ከተባሉት ፡ ማህበሮች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፤ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ የሕብረት ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመያዝ ፡ አይችሉም ።[263] ለኅብረቱ ፡ መሬት ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለማህበሩ ፡ አባሎች ፡ መተዳደሪያ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የኅብረቱ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች

---

259. አር ፡ ዳቪድ ፤ ኤክስፖዚ ፡ ዴ ፡ ሞቲፍ ፡ ኤ ፡ ኮማንቴር ፡ ዱ ፡ ቲትር ፤ ዴ ፡ ፐርሶን ፡ ሞራል ፡ ኤ ፡ ዴ ፡ ፓትርሚን ፡ ዳፌክታሲዮን ፤ (ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፴፪) ፤ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፴፪፡ (፲፱፻፶፪ ፡ ያልታተመ)፡ (የማይገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፬ ። (ትርጉም) ።
260. ከዚያው ።
261. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ ፬፻፺፫ ፡ እና ፡ ፬፻፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፤ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ።
262. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ (፩) ።
263. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፰ ፡ (፪)ን ፡ ከሺ፬፻፺፩ ፡ (፩) ፡ ጋር ፡ በማናበብ ።

ንም ፡ ለመያዝ ፡ የሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ተመሳሳይ ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድሞ ፡ ማግኘት ፡ ያሻዋል ።[264] ከማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ተንቀሳቃሽም ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ የሕብረቱን ፡ ንብረት ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።[265]

የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባለው ፡ ማህበር ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ከተደረጉት ፡ ገደቦች ፡ በጣም ፡ ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፫ ፡ (፪) ሥር ፡ የተመለከተው ፡ ነው ። አንድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ማህበር ፡ የራሱን ፡ መሬት ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ ፤ መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችለው ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ፈቃድ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባለሀብቱ ፡ መሬቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ በጥብቅ ፡ የሚወስነውን ፡ የዚህን ፡ ድንጋጌ ፡ ትርጉም ፡ በሚገባ ፡ መረዳት ፡ ይጠቅማል ። በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አንድ ፡ ማህበር ፡ የሚኒስቴሩን ፡ ፈቃድ ፡ ካላገኘ ፡ በቀር ፡ መሬቱን ፡ ከፋፍሎ ፡ ለገዛ ፡ አባሎቹ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ (በዋጋም ፡ ሆነ ፡ ያለዋጋ) ፡ እንዳያስተላልፍ ፡ ይከለክለዋል ። ሚኒስቴሩ ፡ ለመፍቀድ ፡ ወይም ፡ ላለመፍቀድ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ገደብ ፡ ያልተበጀለት ፡ በመሆኑ ፤ ባንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ ፍላጎት ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ፍላጎት ፡ መወሰኑ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፶፫ ፡ (፪) ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ የሚያስከትለው ፡ አንዱ ፡ ውጤት ፡ ማህበሮቹ ፡ ባንዳንድ ፡ ምክንያቶች ፡ የማይፈልጉትን ፡ መሬት ፡ ይዘው ፡ እንዲኖሩ ፡ ማስገደዱ ፡ ነው ።

ባገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ላይ ፡ ከተጣሉት ፡ ኃላፊነቶች ፡ መካከል ፤ የማህበሮችን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ የሚመለከቱት ፡ ከበድ ፡ ያሉ ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ ። እያንዳንዱ ፡ ማህበር ፡ እንደየልማዱና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ልማዱን ፡ የሚያሟላ ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስብበታል ።[266] ይህን ፡ ደንብ ፡ ማኅበሩ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ከዓላማዎቹ ፡ አንዱ ፡ የሆነውን ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ሚኒስቴሩ ፡ የተባለው ፡ ደንብ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲያስብበት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።[267]

እነሆ ፤ ባጭሩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፤ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ረቂቅ ፡ አካል ፡ ፈጥሯል ፤ መብቶችን ፡ ሰጥቶታል ፤ ግዴታዎችንም ፡ ጥሎበታል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የአንዱን ፡ "ጥበቃ"ም ፡ ሰጥቶታል ።

ከላይ ፡ እንደተረዳነው ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሌሎች ፡ ማህበሮች ፡ ሁሉ ፡ ያሏቸው ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ይጐድላቸዋል ። ይኸውም ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ በተነሳሱ ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተመሠረቱ ፡ ማህበሮች ፡ አለመሆናቸው ፡ ነው ።[268] እንደተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ የተ

264. ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፰ ፡ (፩) ፡ ተቃራኒውን ፡ ደንብ ፡ በማግኘት ፡ (አኮንትራሪዩ ።)
265. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፮ ፡ (፫) ።
266. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶ ።
267. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፯ ፡ (፩) ።
268. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፬ ።

ባሉት ፡ ማህበሮች ፡ ተመሥርተው ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የተደረገው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በአባሎቹ ፡ ውሳኔ ፡ አንድ ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ማህበር ፡[269] ሊፈርስ ፡ "የሕግ ፡ ሰውነቱንና ፡" ከዚህም ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ መብቶቹንም ፡ እንዲያጣ ፡ ሊደረግ ፡ አይችልም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ ከሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አባሎች ፡ ለማኅበራቸው ፡ ያልሰጡትን ፡ መብት ፡ ሊገፉት ፡ አይችሉምና ።

እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፣ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ (መንግሥታዊ ፡) የሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ናቸው ፡ ሊባል ፡ ይቻላልን ?

እነዚህ ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ናቸው፣ ለሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ተቃውሞ ፣ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡[270] በሚገኙበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ የሚችል ፡ ነው ። ይህ ፡ ክፍል ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮችን ፡ አይጠቅስም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደገለጡት ፡[271] በተባለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዝርዝር ፣ ሕዝባዊ ፡ የሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ አይደለም ። ይህንንም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፣ በተለይም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፮ ፣ በቀላሉ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

በዚህም ፡ መሠረት ፣ በቁጥር ፫፻፺፬—፫፻፺፮ ፡ መሠረት ፡ ሕዝባዊ ፡ የሆነ ፡ የሕግ፡ ሰውነት ፡ ያልተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ወይም የሕዝብ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ ከሆኑና ፡ በአስተዳደር ፡ ሕግም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተለይ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ሊቆጠሩ ፡ ይችላሉ ።[272]

(በቁጥር ፡ ፫፻፺፰ ፡ ሥር ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደጐን ፡ ትተን) ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬—፫፻፺፯ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ብንመረምር፣ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ድርጅቶች ፡ ሁለት ፡ የተለየ ፡ ጠባይ ፡ ያሏቸው ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን ።

አንደኛ ፤ እነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፣ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ቅርንጫፎች ፣ ወይም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋር፡ የተያያዘ ፡ ሕዝባዊ ፡ ተግባር ፡ የሚያከናውኑ ፡ ናቸው ።

ሁለተኛ ፤ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ለተሰጣቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የሕግ ፡ ቃል ፡ አማካይነት ፡ ነው ። ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፣ በተለይም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፯ ፡ አነጋገር ፣ በግልጽ ፡ ሳይደነ

269. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፬ ፡ እና ፡ ፬፻፰ ።
270. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።
271. ዳቪድ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፶፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩ ።
272. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፮ ።

ገግ ፤ ተዘዋዋሪ ፡ በሆነ ፡ የአተረጕጓም ፡ ዘዴ ፡ ለአንድ ፡ ድርጅት ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ተሰጥቷል ፤ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ እንገነዘባለን ።

ከላይ ፡ የተመለከትናቸው ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ካሏቸው ፡ ሁለት ፡ ጠባዮች ፡ ጋር ፡ ስናስተያያቸው ፤ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያሏቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያሏቸው ፡ ድርጅቶች ፡ አይደሉም ። ምክንያቱም ፡ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ሥር ፡ በተለይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የመንግሥት ፡ የግዛት ፡ ክፍሎች ፤ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ሥር ፡ ከተመለከቱት ፡ ሚኒስቴሮች ፤ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አንዱ ፡ አይደሉምና ።

እዚህ ፡ ላይ ፤ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የሕዝብ ፡ "ድርጅቶች ፡" ፡ (ኢስታብሊሽመንትስ) ፡ ናቸውን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሊነሳ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ቃል ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡[273] ትርጉም ፡ አልተገኘለትም ። (አርቃቂው ፡ ስለ ዚህ ፡ ቃል ፡ የተዉት ፡ ማስታወሻ ፡ የለም) ።[274] ይሁንና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እርግጠኛው ፡ የቃሉ ፡ ትርጉም ፡ ተጣርቶ ፡ ባይታወቅም ፡ "ድርጅት ፡" የሚባል ፡ አቋም ፡ ሁሉ ፡ ለጠቅላላው ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ አገልግሎት ፡ የሚያበረክት ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ስምምነት ፡ አለ ።[275]

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የሚያበረክቱት ፡ አንዳችም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የለም ። የተቋቋሙበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ዘመናዊ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ ፍጹም ፡ የግል ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶችን ፡ በበለጠ ፡ ለማልማት ፡ እንዲቻል ፡ በማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ የተቋቋሙበት ፡ በልማድ ፡ "የቤተሰብ፡" "የጕሳ፡" እና ፡ "የመንደር ፡" ሀብት ፡ የነበረው ፡ የግል ፡ መሬት ፡ ባለሀብትነት ፡ ዘመናዊ ፡ መልክ፡ እንዲይዝ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ መሠረት ፡ "ድርጅቶች ፡" ናቸው ፤ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ ብንቀበለው ፡ እንኳ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በግልጽ ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ የሕዝብ ፡ ድርጅቶች ፡ ሊባሉ ፡ አይችሉም ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ የሕዝብም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ ናቸው ፡ ሊባሉ ፡ አይችሉም ። ስለዚህም ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፤ ከሌሎች፡ድርጅቶች ፡ የማይገጥሙ ፤ አንድ ፡ የተለየ ፡ ክፍል ፡ ያላቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በመሆን ፡ በአንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ሥር ፡ የሚተዳደሩ ፤ የመሬት ፡ ባለቤቶች ፡ ለመሆንና ፡ በስምምነትም ፡ ሆነ ፡ በክስ ፡ ላይ ፡ በእንደራሴዎች ፡ የመወከል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

---

273. አ ፡ ማርቲን ፡ ፓኔቲዩ ፤ ኤሌማ ፡ ዳናሊዝ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ዴዜ ፡ ኤታብሊሰማ ፡ ፑብሊክ ፡ አንድሯ ፡ ፍራንሴ ፡ ኤት ፡ አን ፡ ድሯዝ ፡ አንግሌ ፡ (፲፱፻፷፮ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፤ ከገጽ ፡ ፪—፳፫ ፤ "ኤታብሊሰማ ፡ ፑብሊክ" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ የሚተነትኑትን ፡ እና ፡ አ ፡ ላውባዴር ፡ ትሬይቴ ፡ ኤሌማንቴር ፡ ደ ፡ ድሯት ፡ አድሚኒስትራቲፍ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ እ - ኤ - አ) ፤ ገጽ ፡ ፩፻፺፱—፩፻፷፯ን ፡ ያወዳድሯል ።

274. የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ "የሕዝብ ፡ ድርጅት" ፡ የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ በዝርዝር ፡ ማብራሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ በመተርጐም ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ የለም ። ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ የተጠቀ ሰው ።

275. ማርቲን ፡ ፓኔቲየ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፸፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።

የተለየ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ በመሆን ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) እንደተደነገገው ፡ ሁሉ ፡ በይርጋ ፡ መሬታቸውን ፡ ሊነጠቁ ፡ አይችሉም ።[276]

በዚህ ፡ ቁጥር ፡ በአማርኛው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ ባይቻልም ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡[277] ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) የሚከለክለው ፡ አንድ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባል ፡ በይዞታው ፡ ሥር ፡ የሚገኘውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፤ ሐረጌን ፡ መዝገቤ ፡ ልካፈል ፤ የሚል ፡ ሲመጣ ፡ በይርጋ ፡ እንዳያግደው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አንድ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ በይዞታው ፡ የሚገኘውን ፡ የሌሎች ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ አስቀራለሁ ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ፤ ይህ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የሌሎችን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ ይችላል ፤ በማለት ፡ ወስነው ፡ ይገኛሉ ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ የተሳሳተ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ በይርጋ ፡ ሊያገኝ ፡ እንደሚችል ፡ ተደርጎ ፡ ከተተረጎመ ፤ <u>ማንኛውም</u> ፡ ሰው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬቶችን ፡ ጭምር ፤ በይርጋ ፡ እንዳይዝ ፡ የሚከለክለውን ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩)ን ፡ በቀጥታ ፡ የሚቃረን ፡ ይሆናል ። እላይ ፡ የተሰነዘረው ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ትርጉም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ጠቅላላ ፡ መንፈስና ፡ ዓላማ ፡ የሚያፋልስ ፡ ነው ። ይህ ፡ ምዕራፍ ፡ የእንደዚህ ፡ ዓይነቶችን ፡ መሬቶች ፡ ባለቤትነት ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነት ፡ ለሌለው ፡ ረቂቅ ፡ የሕግ ፡ ፍጡር ፡ በመስጠት ፡ መሬቶቹ ፡ በባዕድም ፡ ሆነ ፡ በተወላጅ ፡ በይርጋ ፡ እንዳይያዙበት ፡ የተለየ ፡ መከላከያ ፡ አድርጎላቸዋል ።[278]

በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ስር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ትክክለኛው ፡ ትርጉም ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) የተመለከተውን ፡ ደንብ ፡ የሚያሟላና ፡ የሚደግፍ ፡ ነው ፤ የሚለው ፡ ይመስለናል ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባልም ፡ ሆነ ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ርስት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ አይችልም ፤ በማለቱና ፡ ቃላቱም ፡ በባዕድና ፡ በተወላጅ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሳይፈጥሩ ፡ በደፈናው ፡ በሁለቱም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ በመደንገጋቸው ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ስር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ የቤተዘመድን ፡ መሬት ፡ በሚነካ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ የሚለይ ፤ ደንቡንም ፡ የማይከተል ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) አንድ ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ርስት ፡ ባለቤትነት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ እንደሚፈቅድ ፡ ተደርጎ ፡ ቢተረጎም ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) ጋር ፡ አይፋለስም ፤ የሚል ፡ ክርክር ፡ ማቅረብ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ።

---

276. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) ።

277. ለምሳሌ ፡ የከሳሽን ፡ ተፈሪ ፡ ስብሐት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ስብሐትንና ፡ የተከሳሽን ፡ ባሕታ ፡ ተስፋይንና ፡ ሌሎች ፡ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት) ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ-ም-) ፡ ጉዳይ ፤ <u>ከኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፩ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

278. እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ እንዲያስተውለው ፡ የሚገባው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶችን ፡ ቤተ ፡ ዘመድም ፡ ሆነ ፡ ባዕድ ፡ በይርጋ ፡ ሊይዛቸው ፡ ያለመቻሉን ፡ በግል ፡ ይደነግግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነው ። ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቊጥር ፡ ፴ ። የመጀመሪያው ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ ረቂቅ ፡ የተጠበቀውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመስል ፡ እንዳልነበረው ፡ ስናስታውስ ፤ ለመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቊጥር ፡ አለመጨመሩ ፤ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ሊያሰጠው ፡ አይችልም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ትክክል ፡ አይደለም ። "ስለጠቅላላ ፡ ጉዳይ ፡ የሚወስነውን ፡ ሕግ ፡ ስለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ የሚወስነውን ፡ ሕግ ፡ ይገዛዋል ፡" የሚለውን ፡ የሕግ ፡ መተርጐሚያ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ ተከትለን ፣ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) ይልቅ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) የበላይነት ፡ አለው ፡ ለማለት ፡ ሁለቱም ፡ ቁጥሮች ፡ በተመሳሳይ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ቢሆኑም ፣ የአንዱ ፡ ቁጥር ፡ አፈጻጸም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ውጤት ፡ ሲያደርስ ፡ የሌላው ፡ ቁጥር ፡ አፈጻጸም ፡ ደግሞ ፡ ወደተለየ ፡ ውጤት ፡ እንደሚያደርስ ፡ ማስረዳት ፡ ይኖርብናል ።

ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻል ፡ አይመስለንም ። ምክንያቱም ፡ እላይ ፡ እንዳሳየነው፡ ሁሉ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ አጻጻፍና ፡ የቋንቋ ፡ አገባብ ፣ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) የሚከለክለው ፡ ተወላጅ ፡ ብቻ ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዳይዝ ፡ ነው ፣ ለሚለው ፡ አስተያየት ፡ ድጋፍ ፡ ሊሆን ፡ ስለማይችል ፡ ነው። "ቃል ፡ በቃል ፡" ሲነበብ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) ሥር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ተወላጅም ፡ ባዕድም ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዳይዙ ፡ ይከለክላል ። ስለዚህ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) እና ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) ሥር ፡ በተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ መሀል ፡ አንዳችም ፡ የቃል ፡ አለመስማማት ፡ የለም ።[279]

በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) ስር ፡ በተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ "በተወላጅ ፡ ብቻ ፡" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ ማስገባትና ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዲይዝ ፡ ማድረግ ፣ የተለመደውን ፣ "ሕጉ ፡ ራሱ ፡ ልዩነት ፡ በማይፈጥርበት ፡ ጊዜ ፡ (በትርጉም ፡) ምንም ፡ ልዩነት ፡ መፍጠር ፡ አይገባም ፡" የሚለውን ፡ የሕግ ቃላት ፡ መተርጐሚያ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ መጣስ ፡ ይሆናል ።[280] ሕጉ ፣ ማለትም ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) ሥር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፣ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ስለመያዝ ፡ በባዕድና ፡ በተወላጆች ፡ መሀል ፡ አንዳችም ፡ ልዩነት ፡ አይፈጥርም ። ስለዚህም ፡ ባዕድም ፡ ተወላጅም ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) መሠረት ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ለመያዝ ፡ አይችሉም ፡ ወደሚል ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ መድረስ ፡ ግድ ፡ ይሆንብናል ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፣ መሬትን ፡ "በተራድዖ ፡" እና ፡ በ"ግል" ፡ ለማልማት ፡ ስለተደነገጉት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚለሙበት ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፣ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ፣ ፩ሺ፬፻፺፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፰ ፡ መሀከል ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ ስለሚታየው ፡ የቃል ፡ አለመስማማት ፡ እንመራመራለን ። አስቀድመን ፡ መሬትን ፡ "በኅብረት ፡ ማልማት ፡ (መሥራት)" ፡ ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ እንመለከታለን ። የመጀመሪያውን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅና ፡ ከላይ ፡ በክፍል ፡ ፩ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ልማድ ፡ በመመልከት ፣ የሕጉ ፡ ትርጉም ፡ ሊሆን ፡ በማይችል ፡ አገላለጽ ፡ መጀመር ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ይታየናል ።

"በኅብረት ፡ ማልማት ፡" (ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡) የሚለው ፡ የፈረንሣ

---

279. እርግጥ ፡ አለመስማማት ፡ ያለው ፡ ሊደነገግ ፡ በተፈለገውና ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፫ ፡ (፩) ፡ ግልጽ ፡ ቃላት ፡ መሠረት ፡ በተደነገገው ፡ መካከል ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘቧል ።
280. ኤም ፡ ፕላኒዮልና ፡ ጂ ፡ ሪፔር ፣ ትራቲስ ፡ አን ፡ ዘ ፡ሲቪል ፡ ሎው ፡ (፲፩ኛ ፡ እትም ፣ ፲፱፻፴፰ ፡ እ-ኤ-አ ትርጉም ፣ ሉዊዚያና ፡ እስቴት ፡ ሎው ፡ ኢንስቲቲውት ፣ ፲፱፻፶፱ ፡ እ- ኤ- አ-) ፣ ቮል- ፩ ፣ ክፍል ፡ አንድ ፣ ቍጥር ፡ ፪፻፷፱ ፡ ኤ ።

ይኛው ፡ ሐረግ ፡ በአንድ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ራፖር ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተ ለው ፡ ተተርጉሞ ፡ ይገኛል ።[281]

"መሬትን ፡ በኅብረት ፡ ስለማልማት ፡" (ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡) አን ድን ፡ በይዞታ ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ማሳ ፡ ከብዙ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በተውጣጡ ፡ ሰዎች ፡ ማሳ ረስ ፤ ማንኛውም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ቢሆን ፡ በኅብረት ፡ (በተራድዖ ፡) ከሚታረሰው ፡ መሬት ፡ ጠቅላላ ፡ ስፋት ፡ ውስጥ ፡ በማንኛውም ፡ ማሳ ፡ ላይ ፡ ዘላቂ ፡ መብትም ፡ ሆነ ፡ ኃላፊነት ፡ የሌለው ፡ ሲሆንና ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅችና ፡ በእጅ ፡ የሚሠራ ውን ፡ ሁሉ ፡ በሚያከናውኑት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ የቀጣሪና ፡ የተቀጣሪ ፡ ሳይሆን ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሚታሰብለት ፡ ዋጋ ፡ የሚለካው ፡ በሚያበረክተው ፡ የጉል በት ፡ መዋጮ ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።" (አንክሮው ፡ የደራ ሲው ፡ ነው ።)

"ኤክስፕላይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ ትርጉም ፡ እንደሌለው ፡ በቀላሉ ፡ የምንረዳው ፤ ሕጉ ፡ "የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረትን" ፡ "ንብረት ፡ ማስለቀቅን" ፡ "የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበርን ፡" እና ፡ "የከተማ ፡ ቀበሌዎችን ፡" ሁሉ ፡ "ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡" (የኅብረት ፡ ልማት ፡) በማለት ፡ በኅብረት ፡ የመጠቀሚያ ፡ ዘዴዎች ፡ አድርጎ ፡ በመቀ ጠሩ ፡ ነው ።[282] እነዚህ ፡ ከላይ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ ዘዴዎች ፡ ሁሉ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ "የንብረት ፡ ማልማት ፡" ዘዴ ፡ ውስጥ ፡ ሊመደቡ ፡ የሚችሉ ፡ አይደሉም ።

በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "በኅብረት ፡ መሥራት ፡" የሚለው ፡ የአማርኛው ፡ ሐረግ ፤ በተራድዖ ፡ ማረስ ፡ ወይም ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች እንደሚገኘው ፡ በአንድ ፡ ሰፈ ፡ በሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አቋም ፡ "---ዋና ፡ መሪ ፡ ፡ሥር ፡ ---"[283] እንደሚካሄደው ፡ የመሬት ፡ አስተራረስ ፡ ዘዴ ፡ ያለ ፡ አለመሆ ኑን ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፯ ፡ መካከል ፡ ከሚታየው ፡ አለመስማማት ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ።

በመጀመሪያው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ሐረጎች ፡ "ኤክስፕሏይቴ ፡ ሴሎን ፡ አን ፡ ሞድ ፡ ኮሌክቲቭ ፡" (የሕብረት ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም) ፡[284] "ዩዛዥኤ ፡ ገፑዱሳን ፡ ኧን ፡ ኮሙን ፡" (በጋራ ፡ መጠቀምና ፡ መገልገል)[285] ፤ "አሎቲሰማ ፡ ፕራቫቲፍ ፡ አ ፡ ቤኔፊስ ፡ ዴ ማምበር" ፡ (አባል ፡ ለሆ ነ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ የተሰጠ ፡ የግል ፡ ድርሻ)[286] ፤ "ኩልቱርዝ ፡ ኧን ኮሙን ፡" (የተራ ድዖ ፡ እርሻ)[287] ፡ የሚሉት ፡ ናቸው ።

---

281. ኤፍ ፤ ኤ ፤ ኦ ፤ አይ ፡ ኤል ፤ ኦ ፡ እና ፡ ዩ ፡ ኤ ፡ ኤን ፤ ፕሮግሬስ ፡ ኢን ፡ ላንድ ፡ ሪፎርም ፤ ፎርዝ ፡ ሪፖርት ፤ (፲፱፻፷፮) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፷፮ ።
282. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፯ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ። በተለይም ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ፡ የሚገኙበት ፡ የአንቀጽ ፡ ዘጠኝ ፡ አርዕስት ፡ "በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብ ረት ፡ ስለመጠቀም ፡" ማለቱን ፡ በሚገባ ፡ ይገነዝቧል ።
283. ኤፍ ፡ ኤ ፡ ኦ ፡ እና ፡ ዩ ፡ ኤን ፡ አፍሪካን ፡ አግሪካልቸራል ፡ ዴቬሎፕሜንት ፤ ሪፍሌክሽንስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሚጀር ፡ ላይንስ ፡ ኦፍ ፡ አድቫንስ ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ባርየርስ ፡ ቱ ፡ ፕሮግሬስ ፤ ፩ሺ፱፻፷፮ ፡ እ.ኤ. አ. ገጽ ፡ ፺፱ ።
284. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፩ ።
285. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፤ (ለምሳሌ) ።
286. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፶፬ ፤ (ለምሳሌ) ።
287. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፬ ፤ (ይህንኑ ፡ አርእስት ፡ አዝሎ ፡ ይገኛል ።)

የመጀመሪያው ፡ ሐረግ ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ የኅብረት ፡ በሆነው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ማለትም ፡ በሚታረስ ፡ መሬት ፣ በግጦሽና ፡ በቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፣ ያለውን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ። የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፣ የኅብረት ፡ በሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ "የኅብረት ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፣ መጠቀም" ፡ በሚለው ፡ ላላ ፡ ባለው ፡ ሐረግ ፡ ተገልጧል ፡ ማለት ፡ ነው ።

"በጋራ ፡ መጠቀምና ፡ መገልገል ፡" የሚለው ፡ ሁለተኛው ፡ ሐረግ ፡ የሚያመለክተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለእርሻ ፡ በማይውል ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ነው።

"የግል ፡ እርሻ" ፡ እና ፡ "የተራድኦ ፡ እርሻ" ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፡ የእርሻውን ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ "የተራድዖ ፡ እርሻ" ፡ የሚያመለክተው፡ በማኅበሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ አመራር ፡ ስር ፡ የሚካሄደውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ሲሆን ፣ ተቃራኒውም ፡ በግል ፡ የሚካሄድ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ ሥር ፡ "በኅብረት ፡ መሠራት ፡" የሚለው ፡ አጭር ፡ ሐረግ ፡ የሚገልጸው ፡ የእርሻ ፡ ዘዴን ፡ ሳይሆን ፡ አንድ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ በሆነው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ መሆኑን፡ ይገነዘቧል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ስር ፡ የታቀዱት ፡ "የአሠራር፡ ሁኔታ" ፡ ምርጫዎች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ ሥር ፡ ተተንትነዋል ። በእርሻ ፡ ላይ ፡ ለሚውል ፡ መሬት ፡ የሚያገለግሉት ፡ "የአሠራር ፡ ሁኔታ ፡" ምርጫዎች ፡ የ"ተራድዖ" ፡ እና ፡ የ"ግል" ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፪) ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

"የአሠራሩ ፡ ሁኔታ ፡" የተራድዖ ፡ እርሻ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፣ ይኸው ፡ ዘዴ ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሩያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፣ በግልጽ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።[288] በተጨማሪም ፡ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ በኅብረቱ ፡ መሬቶች ፣ በግጦሽ ፡ መስኮችና ፡ ደኖችም ፡ ጭምር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ መወሰን ፡ ይኖርባቸዋል ።[289]

ነገር ፡ ግን ፡ "የአሠራሩ ፡ ሁኔታ" ፡ የግል ፡ እርሻ ፡ ሲሆን ፡ የማኅበሩ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ በግልጽ ፡ ማመልከትና ፡[290] በማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ በሆነ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አባሎች ፡ ያላቸውን ፡ መብትና ፡ እንዲሁም ፡ ቀድሞ ፡ የተደረጉ ፡ የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ድልድሎች ፡ የሚሻሻሉበትን ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ መወሰን ፡ ያስፈልገዋል ።[291] የተራድኦ ፡ እርሻ ፡ በሚካሄድበት ፡ ቦታ ፣ ይህን ፡ የመሬት ፡ ማከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ መጥቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ እንዲገነዘበው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፣ የሕጉን ፡ ረቂቅ፡ ለተመለከተና ፡ በመረመርናቸውም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ የግጦሽ ፡ መስክም ፡ ሆነ ፡ ለእንጨት ፡ የሚሆን ፡ ጫካ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተቆርሶ ፡ የማይሰጥ፡

288. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፩) ።
289. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፪) ።
290. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) ።
291. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፫) ።

መሆኑን ፡ ላስታውስ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ፡ እና ፡ በከፊል ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፮፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፯ ፡ የተዘረዘሩት ፡ "የአሠራሩ ፡ ሁኔታዎች ፡" የእርሻ ፡ መሬትን ፡ እንጂ ፡ ለምሳሌ ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ አጠቃቀምን ፡ አለመመልከታቸውን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ የሚውልንና ፡ የማይውልን ፡ መሬት ፡ የሚያ ጠቃልል ፡ ሲሆን ፣ ስለኋለኛው ፡ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ ያቀደውም ፣ ለምሳሌ ፡ በአባሎች ፡ በግጦሽ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ሊጣሉ ፡ የሚችሉትን ፡ ገደቦች ፡ ነው ።[292] እን ግዲህ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፮ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፯ ፡ ደግሞ ፡ የእርሻ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከተ ውን ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ደንብ ፡ ለማሟላት ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋምና ፡ ቁጥጥር ፤</u>

በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፣ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስላ ላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምን ፡ እንደደነገገና ፣ ከተደራጁም፡ በኋላ ፡ ስለሚደረግባቸው ፡ ቁጥጥር ፡ የወሰነውን ፡ እንመለከታለን ።

የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ ለጊዜው ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በባሕል ፡ ስር ፡ የሚ ተዳደር ፡ ነው ፤ በመተዳደሪያ ፡ ደንባቸው ፡ ውስጥ ፡ (ለምሳሌ ፡ ያሀል)፡ "ለአስተዳደ ራቸው" ፡ ኣላፊ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ዘርዝረው ፡ እንዲያመለክቱ ፡ አልተገደዱም ።[293] እላይ ፡ እንዳየነውም ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እንዲያወጡ ፡ ለማድረግ ፡ "እንዲያስብበት" ፡[294] እና ፡ ከዚያም ፡ የኅ ብረቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማሻሻል ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመሠረ ተበትን ፡ የፍትኅንና ፡ የሞራልን ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳቦች ፡ በመከተል ፡ ከንገሩ ፡ አካባቢ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ የኅብረቱ ፡ ልማዶች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ለማድረግ ፡[295] እንዲሁ ፡ እንዲያስብበት ፡ ተደርጓል ።

ቀደም ፡ ስንልም ፡ ያመለከትናቸው ፡ የማኅበሮቹ ፡ "ወኪሎች ፡"[296] በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያላቸው ፡ ሥራና ፡ ጥቅም ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ይገባል ። ብዙዎች ፡ ማኅበሮች ፡ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ ያወጣሉ ፡ ቢባልም ፡እንኳ፡ አሁን ፡ የሰነዘርነው ፡ አስተያየት ፡ እውነተኛነት ፡ አይለወጥም ። ይህ ፡ የተባለበ ትም ፡ ምክንያት ፡ ወኪሎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የታቀዱት ፡ የተራድዖ ፡ እርሻን ፡ ለሚከተሉ ፡ ግዴታ ፡ ሊገባላቸው ፡ መብትም ፡ ሊገ ኝላቸው ፡ ለሚችሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ስለሆነ ፣ ነው ።

---

292. በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የታቀደው ፡ የአሠራር ፡ "ዘዴ" ፡ ይህ ፡ ነበር ። ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፸ ፡ እና ፡ ፸፩ ።

293. በቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (ሐ) ፡ ሥር ፡ የታቀዱት ፡ "አስተዳዳሪዎች" ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፤ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተናቸዋል ።

294. አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ እስካሁን ፡ ምን ፡ እንደሰራ ፡ ለማወቅ ፡ አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል፡ ከበደ ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አነጋግረው ፡ ነበር ። ኃ/ ሚካኤል ፡ ከበደ ፡ <u>፱ ፡ ኢምፖ ክት ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኦን ፡ ላንድ ፡ ዶዜጅ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ</u> ፡ (የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨ ርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፣ ያልታተመ) ፡ ገጽ ፡ ፲ ፣ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፷ ፡ ሥር ።

295. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፰ ፡ (፩) ። ከበድ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ መመሪያን ፡ ለመግለጥ ፡ የገቡ ፡ እንጂ ፡ የተወሰነ ፡ ትርጉም ፡ የላቸውም ።

296. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (ሐ) ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ።

ስለዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ በተራድዖ ፡ ካላረሱ ፡ በስተቀር ፤ ወኪሎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕጎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችል ፡ ድርጅት ፡ በሌለበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ ጥቅም ፡ አይሰጡም ።

አንድ ፡ ማኅበር ፡ መሬቶችን ፡ በተራድዖ ፡ ለማሳረስ ፡ ሲወስንና ፡ ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ወኪሎች ፡ ሲመርጥ ፤ ወኪሎቹ ፡ ለፈጸሙት ፡ አድራጎት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ኣላፊነት ፡ ይኖርበታል ፤ እነዚህም ፡ (፩) ወኪሎቹ ፡ የሠሯቸው ፡ ወይም ፡ ሳይፈጽሚቸው ፡ የቀሩት ፡ ተግባሮች ፡ ግዴታዎች ፡ ሲሆኑና ፤ (፪) ኣላፊነትንም ፡ አስከትለው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።[297] እንደዚሁም ፡ ወኪሎቹ ፡ ከፈጸሙት ፡ ተግባር ፡ የተነሳ ፡ ማኅበሩ ፡ ያለአግባብ ፡ በልጽጎ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በሕግ ፡ ይጠየቃል ፤ ብልጽግናው ፡ የተገኘው ፡ ከሥልጣን፡ ውጪ ፡ በተፈጸመ ፡ ሥራ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ለውጥ ፡ አያመጣም ፤ ማኅበሩ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ በልማድ ፡ የሚተዳደር ፡ ቢሆንም ፤ ቁጥጥራቸው ፡ ግን ፡ በሚገባ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተደንግጎ ፡ ይገኛል ።

አንደኛ ፤ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ የግል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ እንዲኖራቸው ፡ ጥረት ፡ ሲያደርግ ፤ ልማዳቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ መልክ ፡ እንዲሆን ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ የሚሻሻልበትን ፡ መንገድ ፡ አጥንቶ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደገለጡት ፤ "(የነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡) የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ የታቀዱት ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ መንገድ ፡ አጥንቶ ፡ ሊያሻሽላቸው ፡ እንደሚችል ፡ ሆነው ፡ ነው ።"[298] እንግዲህ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተጽዕኖ ፡ ይበልጥ ፡ የሚታየው ፤ ልማድ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ተጨማሪ ፡ የሚሆኑ ፡ ደንቦች ፡ ሲያወጣ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ "ተጨማሪ ፡ ደንቦች ፡" በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እያደገ ፤ ትምህርትና ፡ እውቀትም፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ ስለሚገኝና ፤ በልማድም ፡ ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ሊታይበት ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ተጨማሪ ፡ ደንቦች ፡ ሊመለከቱ ፡ የሚችሉት ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ መብትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ የማኅበሮችን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋምና ፡ ከጊዜው ፡ ፍልስፍናና ፡ እምነትም ፡ ጋር ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡንም ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

ስለዚህም ፤ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ "የሕግ ፡ አማካሪ ፡" በመሆን ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲኖራቸውና፡ ሲያስፈልግም ፡ እንዲሻሻል ፡ የሚያደርግላቸው ፡ ስለሆነ ፡ ተጽዕኖው ፡ ታላቅ ፡ ነው።

በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተደነነገገው ፡ ሌላው ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴ፡ በተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ገደብ ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ ቢኖርም ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ካላስፈቀደ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ መሬቶቹን ፡ ለመሸጥ ፤ ለሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፤ በዕዳ ፡ ለማስያዝ ፡ ወይም ፡ ለወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።[299] እንዲሁም ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡

---

297. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፬፻፶፮ ፤ በቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፶፬ ፡ (፫) ።
298. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።
299. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፩ሺ፬፻፶፫ ፡ (፩) ።

የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የኅብረት ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለማስከበር ፡ ሲፈልጉ ፡ አስቀድመው ፡ ማስፈቀድ ፡ አለባቸው ።[300]

ሦስተኛው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ስለማቅረብ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱፡ እና ፡ ፩ሺ፷፯ ፡ በተዘረዘረው ፡ መሠረት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ የቁጥጥር ፡ ዘዴ ፡ ነው ። የኋለኛው ፡ ቁጥር ፡ አርእስት፡ "ፀጥታን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነገሮች ፡" ቢሆንም ፡ የመጀመሪያው ፡ ቁጥር ፡ ቅጥያ ፡ መሆኑ ግልጽ ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱ ፡ መሠረት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ "የኅብረቱ ፡ ፍላጐት" ፡ ተቆርቋሪ ፡ እንደሆነ ፡ ተደርጐ ፡ እንዲገመት ፡ ተደንግጓል ። በተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ አጠገብ ፡ በመገኘት ፡ የዕለት ፡ ተግባራቸውን ፡ ሲያከናውኑ ፡ ሊመለከት ፡ የሚችለው፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልቅ ፡ የተሻሻለ ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግ ፡ መቻሉ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በማኅበሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ የሚያገባው ፡ በመሆኑ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በተሰጠው ፡ የአቤቱታ ፡ መብት ፡ በመጠቀም ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግም ፡ ይችላል ።[301] በቁጥር ፡ ፩ሺ፷፯ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ባይነገርም ፡ ማኅበሩ ፡[302] ወይም ፡ ወኪሎቹ ፡[303] ባሳለፏቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችለው ፡ አቤቱታ ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በኅብረቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ገደብ ፡ ሊደረግበት ፡ ይችላል ። የማኅበሩ ፡ ወኪሎች ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ "ከሥልጣን ፡ በላይ ፡ የሆነ" ፡ ወይም ፡ "የሥነ ፡ ሥርዓትንና ፡ የፍትኅን ፡ ነገር ፡ በመተላለፍ ፡ የተሰጠ ፡" ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ በአእምሮ ፡ ለመገመት ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደመሆኑ ፡ ሁሉ ፡[304] ገደብ ፡ ሊደረግለት ፡ የሚቻል ፡ ወይም ፡ የማይቻል ፡ አቤቱታ ፡ እንዴት ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ለመገመት ፡ አዳጋች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ በአጥጋቢ ፡ ሁኔታ ፡ ሊመለሱ ፡ የሚችሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ መልክ ፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፤ ክርክር ፡ በቀረበበትም ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ከመስጠታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ውሳኔውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የነገሩንም ፡ አዝማሚያና ፡ ሁኔታ ፡ በሚገባ ፡ መመልከት ፡ አለባቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴዎች ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ትርጉም ፡ ያለውና ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ የሚታየውም ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱፡ ስር፡ የተጠቀሰው ፤ በተለይም ፡ ማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ሰው ፡ ሊያቀርበው ፡ የሚችለው ፡ አቤቱታ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ማኅበሩ ፡ ያስተላለፈውን ፡ ውሳኔ ፡ ተቃውሞ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ሲችል ፡ አቤቱታውን ፡ ያላቀረበ ፡ እንደሆነ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አቤቱታውን ፡ ያቀርብለታል ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ያዳግታል ። ይልቁንም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጁ ፤ ሌሎች ፡ እሱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ስለምናውቅ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ አቤቱታዎች ፡ ለማቅረብ ፡ እምብዛም ፡ የሚያስብበት ፡ መስሎ ፡ አይታየንም ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የተባለውን ፡ አቤቱታ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሕጉ ፤ ማለትም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱ ፤ የማያስገድደው ፡ መሆኑንና ፡ የአቤቱታ ፡ ማቅረቡም ፡ ጉዳይ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የግል ፡ ምርጫ ፡ እንደሆነ ፡ መገንዘብ ፡ ይገባናል ።

---

300. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፮ ፡ (፪) ።
301. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱ ።
302. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱ ፡ (፩) ።
303. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፱ ፡ (፪) ።
304. ከዚያው ።

የአንድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፱ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብ ፣ ውሳኔው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ምንጊዜም ፡ ሊከበሩ ፡ ከሚገባቸው ፡ ሊታለፉ ፡ ከማይችሉ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጐች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ መሆ ናቸውን ፡ መግለጥና ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብም ፡ ዝግጁ ፡ መሆን ፡ ይኖርበታል ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ለመጣሱ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። ሆኖም ፡ ሊከ በሩ ፡ የሚገባቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ለመጣሳቸው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅ ረብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ተጣሱ ፡ የሚላቸው ፡ የሕግ ፡ ቃላት ፡ ምንጊዜም ፡ መከበር ፡ ያለባቸው ፡ መሆናቸውን ፡ አስቀድሞ ፡ ማሳየት ፡ አለበት ።

ከሺ፱፻፹፱—ሺ፳፪ ፡ ባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ሥር ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ በወ/ወለተ ፡ ሥላሴ ፡ ገብረ ፡ መድኅንና ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ በባላም/ገብረ ፡ ኪዳን ፡ አብርሃ ፡[305] መሀከል ፡ በቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ ባጭሩ ፡ ገልጿቸዋል ። አንድ ፡ አባል ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅ ረብ ፡ ቢፈልግ ፡ ክሱን ፡ በይግባኙ ፡ ድንጋጌ ፣ ማለትም ፣ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፺፱ ፡ ላይ ፡ መመ ሥረት ፡ ይኖርበታል ፤ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፺፱ ፡ ላይ ፡ ያልተመሠረተ ፡ በመሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ።[306] ከጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ለመ ረዳት ፡ የሚቻለው ፣ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፪ ፡ የግድ ፡ መከበር ፡ ካለባቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ መሆኑን ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ቁጥር ፡ ሲጣስ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፱ ፡ (፩) ፡ ሥር ፡ የተመለከተውን ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ያሳጣል ። በዚህም ፡ መሠ ረት ፣ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ከአባሎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ የተለየ ፡ ሃይማኖት ፡ ይከተላሉ ፣ በማለት ፡ የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ቢከለክላቸው ፣ ውሳኔው ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ የመተዳደ ሪያ ፡ ደንቦች ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ በአባሎች ፡ መሀከል ፡ ልዩነት ፡ እንዳያደርጉ፡ ሲል ፡ የሚደነግገውን ፡ ቁጥር ሺ፱፻፹፪ትን ፡ የሚቃረን ፡ ይሆናል ። እንደ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድም ፣ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፱ ፡ (፩) መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

ቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፪ን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መተርጐም ፡ ትክክል ፡ አይመስልም ። ምክንያቱም ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፺፱ ፡ (፩)ን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፹፪ ፡

305. የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ወ/ወለተ ፡ ሥላሴ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ መልስ ፡ ሰጭና ፡ የባላም ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፡ አብርሃ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፺፱ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፴፩/፺፱ ፡ ያልታተመ) ፡ ጉዳይ ።

306. በይግባኝ ፡ ባይ ፡ በአረጋዊ ፡ ናይዝጊና ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ በአረጋ ፡ መንክር ፡ (ጠ· ን· ነ· ፍ· ፡ ቤት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲፩/፺፱) ፡ (ያልታተመ) ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ተመሳሳይ ፡ ውሳኔ ፡ ተሰ ጥቷል ። በዚህና ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመራርና ፡ ውሳኔ ፡ እጅግ ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።
በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፣ በክቡር ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መዛግብት ፡ እንዲመረምር ተፈቅዶለት ፡ ነበር ። ከሺ፱፻፺፰—ሺ፱፻፺፱ ፡ ዓ· ም· የተከፈቱትን ፡ ፋይሎች ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፣ ከቁ ጥር ፡ ሺ፱፻፹፱ - ሺ፳፪ ፡ ያሉት ፡ ደንቦች ፡ የተጠቀሱባቸው ፡ ሦስት ፡ ጉዳዮች ፡ አጋጥመውታል ። በሦስቱም ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የተመራበት ፡ ሐሳብና ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከላይ ፡ ባጭሩ ፡ ተገልጾአል ። ሦስተኛው ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሳይጠቀስ ፡ የታለፈበት ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቀሩት ፡ በሁለቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የታከለውን ፡ ሐሳብና ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እዚህኛውም ፡ ላይ ፡ መልሶ ፡ ስለሚጠቅሰውና ፡ አዲስ ፡ ነገርም ፡ ስላልጨመረ ፡ ነው ።

አግባብ ፡ የሚኖረው ፡ ተቃውሞ ፡ የቀረበበት ፡ ውሳኔ ፡ በቁጥር ሺ፬፻፺ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ፡ መሠረት ፡ በተደነገገ ፡ ወይም ፡ በሚደነገግ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

የቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፪ን ፡ ድንጋጌ ፡ ጠቃሚነት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ማጋነን ፡ የሚቻል ፡ አይመስለኝም ። የዚህ ፡ ቁጥር ፡ ዓላማ ፡ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርናቸውን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብእን ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ለመደምሰስ ፡ ነው ። ይህ ፡ አቋም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዘመናዊ ፤ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ የሚፃረር ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ልማድን ፡ አቀና ብሮ ፡ የያዘ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ጥንትም ፡ መብት ፡ ያልነበራቸውን ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ከሆኑት ፡ "ሰዎች" ፡ ወይም ፡ "ቤተ ፡ ዘመዶች" ፡ ነጥሎ ፡ ሊለያቸው፡ አይችልም ።[307] በተጨማሪም ፡ እነዚህ ፡ አባሎች ፡ ማኅበሩን ፡ ከማስተዳደርና ፡ ለማኅበሩም ፡ ወኪል ፡ ከመሆን ፡ የሚያግዳቸው ፡ አይኖርም ፤ (ሁለቱም ፡ ተግባሮች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (ሐ) ሥር ፡ ዘላቂ ፡ መልክ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ይገኛል ።) ከሁሉም ፡ የሚበልጠው ፡ መከላከያቸው ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚደለደሉት ፡ በዘር ፤ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ በመመራት ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ።[308] እዚህ ፡ ላይ ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ መሬትን ፡ የማከፋፈል ፡ "እኳኋን" ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ በአንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶችና ፡ በመንደሮች ፡ ዘንድ ፡ መሬት ፡ ከመታደሉ ፡ በፊት ፡ የሚደረገውን ፡ የዕጣ ፡ ማውጣት ፡ ሁኔታንም ፡ ጭምር ፡ ማመልከቱን ፡ ነው ።

ከላይ ፡ ባመለከትናቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፪ ፡ ዘመናዊና ፡ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከትናቸው ፡ ልማዳዊ ፡ የኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ክፍሎችም ፡ ውስጥ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዘልማድ ፡ ተቀዳሚ ፡ በሆነው ፡ እንዲያውም ፡ ምትክ፡ በማይገኝለት ፡ መተዳደሪያቸው ፡ ላይ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑ ፡ መብቶችን ፡ ተነፍገው ፡ ለነበሩት ፡ ወገኖች ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቁጥር ፡ ነው ። "በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መብቶቹንና ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ያለችግር ፡ እንዲገባው ፡ ለማድረግ ፡ አቅደን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገናል ። " ፡ ቀ-ኃ-ሥ ፤ መግቢያ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤

ክፍል ፡ ፫ ፡ መደምደሚያና ፡ አስተያየት ፤

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ መደምደሚያ ፤

ለመደምደሚያ ፡ ያህል ፡ "የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡" በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መሠረተ ፡ ሀሳቦች ፡ በአጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ እናጠቃልላለን ።

307. ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ (ሀ)ንና ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፪ን ፡ ባንድነት ፡ በማንበብ ።
308. ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ)ንና ፡ ሺ፬፻፺፪ትን ፡ በማጣመር ፡

በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፤ የጎብረት ፡ (የደሽ) ፡ የሆኑ ፡ እንደጐሣ ፣ ቤተሰብ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብትነት፡ ለአንድ ፡ "የጎብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ክፍል" ፡ ለተባለ ፡ ማኅበራዊ ፡ አካል ፡ ተሰጥቷል ። ይህም ፡ "ማኅበር" ፡ ቤተሰብ ፤ መንደር ፤ ወይም ፡ ጐሣ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የሕግ ፡ ሰውነት ፡ ስላለውም ፤ ለአባሎቹ ፡ ከተሰጡት ፡ የተለዩ ፤ የራሱ ፡ የሆኑ ፡ የግል ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ አሉት ።

ስለዚህ ፡ ጥንት ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደርንና ፡ የጐሣን ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ለመግለጥ ፡ እንጠቀምበት ፡ የነበረው ፡ "የጎብረት ፡ ባለቤትነት" ፡ የሚለው ፡ ስያሜ ፡ በሕጉ ፡ ሥር ፡ ጊዜው ፡ ያለፈበት ፡ ይመስላል ። የጎብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ የጎብረ ፡ ሰብአ ፡ ክፍል ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ የግል ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚያሳዩትን ፡ ጠባይ ፣ ማለት ፡ በአባሎች ፡ መፈጠርና ፡ መብትም ፡ መሰጠትን ፣ ባለማሳየቱ ፡ ነው ። በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፣ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ማኅበሮች ፡ በሕግ ፡ ተፈጥረው ፡ በአባሎቻቸው ፡ ላይ ፡ የተጫኑ ፡ ቢሆኑም ፡ የሕዝብ ፡ ድርጅቶች ፡ አይደሉም ፤ ምክንያቱም ፡ አንዳችም ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሆኑ ፡ አገልግሎት ፡ ስለማያበረክቱና ፡ ይኸንንም ፡ የመሰለ ፡ "የሕግ ፡ ሰውነት" ፡ በሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ቃል ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፣ የጎብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ ከሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ የማይገጥም ፣ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የተለየ ፡ ክፍል ፡ እንዳላቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ፍጡራን ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠንም ፣ በአባሎቻቸው ፡ ፈቃድ ፡ ሊፈርሱና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብታቸውን ፡ ሊነፈጉ ፡ አይችሉም ።

አንዳንድ ፡ ጥንታውያን ፡ የሆኑ ፣ የቤተ ፡ ሰብ ፣ የመንደርና ፡ የጐሣ ፡ አባሎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ በባሕልና በልማድ ፡ ያልተረጋገጡ ፡ ደንቦችን ፡ ለማጣራት ፡ ያህል ፡ አባሎቹ ፡ የራሳቸውን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በዝርዝር ፡ የሚገልጡበት፡የመተዳደሪያ ፡ ደንብ፡እንዲያወጡ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ይፈቅድላቸዋል ። ይህም ፡ ሲደረግ ፡ በተለይ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ ሥር ፡ የተዘረዘሩትን ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ውስጥ ፡ በግልጥ ፡ ማመልከትና ፡ ደንቡም ፡ ሲጻፍ ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፪ን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ይሁንና ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ "ማኅበሮች" ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያወጣሉ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ የሚያዳግት ፡ በመሆኑና ፡ በአሁኑም ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚወተውት ፡ ድርጅት ፡ ባለ ፡ መኖሩ ፣ የፍ/ብሔሩ ፡ ሕግ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፪ ፡ አማካይነት ፣ በልማድ ፡ ውስጥ ፡ ሊገኙ ፡ የሚችሉትን ፡ የማይገቡ ፡ ደንቦች ፣ በተለይም ፡ የማኅበሩን ፡ የዕለት ፡ ኑሮ ፡ አስተዳደር ፡ የሚመለከቱትን ፤ እንዲወገዱ ፡ አድርጓል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ከማውጣቱ ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ አቋምና ፡ ድርጅት ፡ እንደሚኖረው ፡ ለማወቅ ፡ ቢያዳግትም ፣ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ፡ ደረጃ ፡ አቋም ፡ መሠረት ፣ ከማኅበሩ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ማንም ፡ እንዳይወገድ ፡ ሕጉ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ሕጉ ፡ ከልማድ ፡ ከተለየ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ አስተዋውቆናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

በሕጉ ፡ ሥር ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎች ፣ ማለት ፡ የተራድዖና ፡ የግል ፡ እርሻ ፡ ዘዴዎች ፡ ታቅደዋል ። አንድ ፡ የጎብረት ፡የሆኑ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች፡ያሉት ፡ ክፍል፡ የፈለገውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ፤ ይሁንና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡

ውስጥ ፡ የመረጠውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ በግልጽ ፡ ማስፈር ፡ አለበት ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ እና ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ ሀ/ ሥር ፡ ለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የተሰጡት ፡ መብቶች ፡ ለተራድዖ ፡ እርሻ ፡ ሥራ ፡ እንዳያመቹ ፡ ተደርገው ፡ የተመረጡ ፡ ይመስላሉ ።

በመሠረቱ ፤ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የቁጥጥር፡ ዘዴ ፡ ተደርጎባቸዋል ። አንደኛው ፡ በሥልጣናቸው ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ ገደብ ፡ ነው ። ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፱፻፺፫ ፡ (፪) ፤ ፩ሺ፱፻፺፭ ፡ ሀ/ ፤ ፩ሺ፱፻፺፯ ፤ እና ፡ ፩ሺ፰፻ን ፡ ይመለከቷል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፱ ፡ መሠረት ፡ በአቤቱታ ፡ መልክ ፡ የተጣለው ፡ ገደብ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱ ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴዎች ፡ ይበልጥ ፡ ጠቃሚውና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውልም ፡ የሚችለው ፡ ሁለተኛው ፡ የአቤቱታው ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እስኪያወጡና ፡ በሚገባም ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እስኪችሉ ፡ ድረስ ፡ በሕጉ ፡ የተደረገው ፡ ምርጫ ፡ በኢኮኖሚ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፤ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መፍረድ ፡ አይቻልም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የሕግ ፡ አውጪውን ፡ ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ዓላማዎች ፤ ማለትም ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ማኅበሮቹ ፡ ባሕልና ፡ ልማዳቸውን ፡ ጠብቀው ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚለውን ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ እንዲያገኙ ፡ የሚለውን ፤ ማስተዋል ፡ ይገባዋል ።

የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መኖር ፡ ዋናው ፡ ውጤት፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ በጣም ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሬት ፡ ከተራዎቹ ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ ክልል ፡ ውጪ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርናቸው ፤ ሕግ ፡ አውጭው ፡ አቅዷቸው ፡ የነበሩትን ፡ ክፍሎች ፡ ሊያስረዱ ፡ የሚችሉትን ፡ በኤርትራ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ የሚገኙትን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፤ በቤገምድር ፤ ጐጃም ፤ ሸዋና ፡ ወሎ ፡ የሚገኙ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሚባል ፡ ስሪት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ሥር ፡ የሚተዳደሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ልንገልጥ ፡ እንወዳለን ። በነዚህም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ረቂቅ ፡ ለሆነ ፡ የሕግ ፡ ፍጡር ፡ ተሰጥቷል ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ አስተያየት ፤

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ቁጥሮች ፡ ለብዙዎች ፤ በተለይም ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ እንዲያስፈጽሟቸው ፡ ለታቀዱት ፤ ሰዎች ፤ አንዳችም ፡ ትርጉም ፡ አይሰጡም ። እንዲያውም ፡ አንድ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደፊት ፡ የገሩትንና ፡ የተብራራ ፤ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ የባሕል ፡ ሕግ ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ እንኳን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያወጡ ፡ ያላደረገበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ን ፡ እና ፡ የተታዮቹን ፡ ቁጥሮች ፡ ትርጉምና፡ ዓላማ ፡ በሚገባ ፡ ባለመረዳት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።[309]

